በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የሐረማያ ዩኒቨርሲቲ

የ2009 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ሪፖርት

የሐረማያ ዩኒቨርሲቲ የተመደበለትን በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን እንዲሁም ሂሳቡ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ስርዓት መሠረት መያዙንና የመንግስት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል::

የሂሳብ መግለጫዎችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ሲሆን፤ የሂሳብ መግለጫዎችን ኦዲት በማድረግ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመቤታችን በተሰጠው ስልጣን መሰረት ነው፡፡ በዚሁ መሰረት ዩኒቨርሲቲው የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት እንዲደረግለት በደብዳቤ ቁጥር ሐየ/አስ/ተ/ጉ/ም/5/11/1472/10 በቀን 20/02/2010 ዓ.ም ለመ/ቤታችን ያቀረበውን የሂሳብ ሪፖርት የዓለም አቀፍ የመንግስት ኦዲት ደረጃዎችን እና የዋና ኦዲተር መ/ቤትን የኦዲት ስልት በመከተል ኦዲቱ ተከናውኗል፡፡

የሂሳብ መግለጫዎቹ ጉልህ ከሆኑ መዛባቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል:: አስተያየት ላይ ለመድረስ በሂሳብ መግለጫዎች ላይ ያለውን የመረጃ አቀራረብ አጠቃላይ ብቃት ገምግመናል። ይሁን እንጂ ኦዲቱ በዩኒቨርሲቲው የሚታዩትን የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም። በመሆኑም በዚህ ሪፖርት ላይ ከተመለከቱት በተጨማሪ ሌሎች ድክመቶች ወይም ስህተቶች ሊኖሩ የሚችሉ ከመሆኑም በላይ የሂሣብ ሪፖርቱን ለማዘጋጀት የተዘረጉትን የውስጥ ቁጥጥሮችና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሰረት የሆኑት ዩኒቨርሲቲው ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፣ መዛግብት፣ ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በኦዲት ተደራጊው መ/ቤት ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው፡፡

የሚከተሉት የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት የሂሳብ መግለጫዎች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል፡፡

- የገቢ /የዕርዳታ/ የብድር ሂሳብ ሪፖርት፤
- የመደበኛ ወጪ ሂሳብ ሪፖርት፤
- የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት፤
- የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት፤
- የሂሳብ ሚዛን ሙከራ፤
- የዝውውር ሂሳቦች ሪፖርት፤

<u>**ለኦዲት አስተያየቱ መሰረት የሆኑት ጉዳዮች፣**</u>

የዩኒቨርሲቲው የሂሳብ መግለጫዎች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፤ ደንብና መመሪያን የጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡

1. <u>**ገቢን በተመለከተ፤**</u>

   1. የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በቁጥር ክሂመ-39/4/30 በቀን 30/09/09 የመንግስት የባንክ ሂሳቦችን በተመለከተ በ2009 በጀት ዓመት መጨረሻ የተላለፈ የአፈጻጸም መመሪያ አንቀጽ 3 በፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች እና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ብሎክ በሚደረጉ ሂሳቦች ላይ መደረግ ያለባቸው ተግባራት ውስጥ ባንኩ ብሎክ ያደረጋቸውን ወደ ማዕከላዊ ግምጃ ቤት ፈሰስ የሚደረገውን ሂሳብ ፈሰስ መሆኑን ክትትል ማድረግ እንዲሁም የ2010 በጀት ዓመት የሐምሌ ወር የክፍያ ጥያቄ ሲቀርብ ብሎክ የተደረገው ወደ ማዕከላዊ ግምጃ ቤት የባንክ ሂሳብ ገቢ የተደረገበትን የባንክ አድቫይስ አያይዘው ማቅረብ እንዳለባቸው ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው ፡

      - በልዩ ፈንድ በባንክ ሂሳብ ቁጥር (ሐረማያ ቅርንጫፍ) 1000019938984 ብር 86, 414,656.11 ፤
      - በልዩ ፈንድ በባንክ ሂሳብ ቁጥር (ድሬደዋ ቅርጫፍ) 1000014316896 ብር 59,431,116.03 በድምሩ ብር 145,845,772.14 ብሎክ በማድረግ ወደ ማዕከላዊ ግምጃ ቤት ፈሰስ ያልተደረገ መሆኑ፤

2. . <u>**ወጪን በተመለከተ**</u>

   1. የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ፈቃድ ላላቀረቡ ለማስተርስ ዲግሪ እና ለፒኤች ድግሪ በሚዘጋጅ የጥናት ምርምር ጹሑፍ /Thesis Dissertation Research Examiner

/ እንግዳ ፈታኝ መምህራን ከሚከፈላቸው ክፍያ ላይ 30 ፐርሰንት ቅድመ ታክስ ቀንሶ ብር 79,440.00 ገቢ ማድረግ ሲገባ ከፈታኝ መምህራን ያልተቀነሰና በቀን 28/10/09 ዓ.ም በሂሳብ ማዘዣ ቁጥር 3260/09 ከቅደመ-ታክሱ ብር 32,031.04 አላአግባብ በዩኒቨርሲቲው የተሸፈነ መሆኑ፣

2. ከለጋሽ ድርጅቶች የተገኘ ብር 6,618,783.82 የእርዳታ የገቢ ሂሳብ ዘመናዊ በሆነና በቴክኖሎጂ በተደገፈ የሂሳብ አያያዝ ዘዴ (IBEX) ያልተመዘገበ እና የሂሳብ ሪፖርቱ ተዘጋጅቶ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ያልቀረበ መሆኑ፤
3. ጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ጥር 13/2003 በቁጥር ጠ80-አጠ52/02/13 በተጻፈ ደብዳቤ ከትምህርት ሚኒስቴር የቀረበለትን የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የመምህራን የተሻሻለ የትርፍ ሰዓት ክፍያ በተፈቀደው አግባብ በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል የወጣ የክፍያ ተመን ሳይኖር፡-
   - በዋናው ግቢ ብር 1,995,903.72፣ በህክምና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ በቀን 28/07/09 ዓ.ም በሂሳብ ማዘዣ ቁጥር 741/09 ብር 102,000.00 እንዲሁም በቀን 25/02/09 ዓ.ም በሂሳብ ማዘዣ ቁጥር 176/09 ብር 286,000.00 በድምሩ ብር 388,000.00 በጠቅላላ ብር 2,383,903.72 የሆኖራሪየም ክፍያ የተከፈለ መሆኑ፣
   - በዋናው ግቢ ብር 3,095,460.88 ከውስጥ ገቢ እንዲሁም ብር 346,664.59 ከመደበኛ በጀት እና በአካዳሚክ ምርምር ክላስተር ብር 51,786.56 በድምሩ ብር 3,493,912.03 ለማስተርነት ወይም ለዶክተርነት ዲግሪ በሚዘጋጅ የጥናት ምርምር ጹሑፍ/ Thesis Dissertation Research Supervision/ በተማሪዎች ልክ ለማስተርስ ተማሪዎች ብር 1,000.00 እና 2,000.00 ለረዳት እና ለዋና አማካሪዎች፣ ለፒኤችዲ ተማሪዎች ብር 2,500.00 እና 5,000.00 ወ.ዘ.ተ ለረዳት እና ለዋና አማካሪዎች እንደቅደም ተከተላቸው የክፍያ ተመን ሳይኖር ክፍያው መፈፀሙ፣

   በአጠቃላይ በድምሩ ብር 7,138,516.16 ክፍያዎቹ በመንግስት ወይም በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል የወጣ የክፍያ ተመን ሳይኖር የተከፈሉ መሆኑ፤
4. የሲቪል ሰርቪስ ሚኒሰቴር በቁጥር ሲሰሚ30/ጠ18/22/459 በቀን 16/04/2005 ዓ.ም በኮንትራት /በጊዜያዊ ተቀጥረው የሚገኙ ሰራተኞችን ቋሚ ለማድረግ በወጣው አፈጻጸም መመሪያ መሰረት ዘላቂነት ባለውና በሲቪል ሰርቪስ ሚኒሰቴር በተመደበ የስራ መደብ ላይ በኮንትራት /በጊዜያዊነት ተቀጥረው

የነበሩ ሠራተኞች ቅጥር እንዲቋረጥ ሆኖ በአስቸኳይ እንዲሰናበቱና ከየካቲት 30/2005 ዓ.ም በኋላ ቅጥር እንደማይፈፀም እንዲሁም ቅጥር ፈጽሞ የተገኘ የስራ ሃላፊ በህጉ መሰረት ተጠያቂ እንደሚደረግ በሚገልፀው መሰረት ስለመፈፀሙ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

- በግብርና ልማት ማስተባበሪያ ክፍል የተለያዩ የእርባታ ክፍሎችን ደህንነት ለሚጠብቁ፣ የእንስሳት መኖ ለሚያዘጋጁ እና ለሚንከባከቡ ሰራተኞች በቀን ብር 20 እና 35 በማሰብ በድምሩ ብር 733,600.00፣
- በካምፓስ እና በስልጠና ማዕከል ስር ለሚገኙ ለአስተናጋጅ፣ ጽዳት፣ ስጋ ቤት አራጅ፣ ምግብ አብሳይ፣ እንጀራ ጋጋሪ፣ ስጋ ከታፊ፣ ቦንቦሊኖ ሰራተኛ ወ.ዘ.ተ. ለመሳሰሉት ሰራተኞች በቀን ብር 18፣ 21፣ 26፣ 40፣ 46 በማሰብ በድምሩ ብር 288,430.20 መከፈሉ፣

በጠቅላላ ድምሩ ብር 1,022,030.20 ቀጣይነት እና ዘላቂነት ባላቸው የስራ ዘርፎች ቋሚ የስራ መደብ እንዲሆኑ ጥናት በማድረግ መዋቅር ሚኒስቴር በማስፈቀድ ክፍያውን መፈጸም ሲገባ በቀን ሰራተኝነት የተለያየ የክፍያ ተመን በማድረግ እንዲሁም ለቦታው የሚያስፈልገው የሰው ሃይል በጥናት ባልተደረሰበት ሁኔታ ከፍተኛ የሰው ሃይል በመጠቀም ክፍያው ወጪ ቆጣቢ አሰራርን እና መመሪያን ያልተከተለ መሆኑ፤

5. ዩኒቨርሲቲው በቁጥር ሐዩ/አስ/ተ/ጉ/ም/ና/11/880/09 በቀን 21/04/2009 የትርፍ ሰዓት ጠይቆ ከፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት ሚኒስቴር በቁጥር ፐ/ስ/ሚ47/ጠ13/1/3 በቀን 07/05/2009 ከተፈቀደው በትርፍ ሰዓት ሊከፈላቸው ከሚገባ የስራ መደብ ውጪ በዩኒቨርሲቲ ዋና ግቢ ውስጥ ለሚሰሩ ለጥበቃ ሰራተኞች በድምሩ ብር 3,839,682.93 አለአግባብ የትርፍ ሰዓት ክፍያ ተከፍሎ የተገኘ መሆኑ፤
6. ሰኔ/2002 በወጣው የፌዴራል መንግስት የግዥአፈጻጸም መመሪያ ክፍል 4 አንቀጽ 15.2-15.4 መሠረት በአዋጁና በመመሪያው በተፈቀደው ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር የመንግስት መ/ቤቶች ማናቸውንም ግዥ በግልፅ የጨረታ ዘዴ መፈጸም እንዳለባቸው፣ የመንግስት መ/ቤቶች ከግልፅ ጨረታ ውጭ በሌሎች የግዥ ዘዴዎች ግዥ መፈጸም የሚችሉት በአዋጁና በዚህ መመሪያ የተገለጹት ሁኔታዎች ሲሟሉ ብቻ እንደሆነ እንዲሁም ከግልጽ ጨረታ ውጭ በሌሎች የግዥ ዘዴዎች የሚጠቀም ማናቸውም የመንግሥት መ/ቤት በእነዚህ ዘዴዎች ለመጠቀም የመረጠበትን ምክንያትና ሁኔታዎች የሚገልጽ ሠነድ መያዝ እንዳለበት በሚያዘው መሰረት መፈጸማቸውን

ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በዋናው ግቢ በድምሩ ብር 1,663,844.17 ዕቃ ከመመሪያው ውጪ ግዥው ያለውድድር የተፈጸመ መሆኑ፤

7. የፌደራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የመደበኛና ካፒታል የስራ ማስከጃ ወጪዎች ሲፈጸም ወጪዉ ለሚደረግበት ተግባር በበጀት ዓመቱ የተያዘ ወይም ወጪዉን ለመሸፈን ቀሪ በጀት መኖሩንና ወጪዉ በመስሪያ ቤቱ ዕቅድ ወስጥ የተያዘና በጥሬ ገንዘብ ፍላጎት ላይ የተካተተ መሆኑ ሳይረጋገጥ ወጪ መፈፀም እንደማይገባ መመሪያው ይገልፃል፡፡ በዚህም መሠረት በዩኒቨርሲቲው የሚፈፀሙ ክፍያዎች መመሪያውን የተከተሉ ለመሆኑ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በዩኒቨርሲቲው ለተፈፀሙ የዕቃ እና የአገልግሎት ግዥዎች፣ በዋናው ግቢ ለ2008 በጀት ዓመት ለተፈጸመ ግዥ የሰራተኞች ደንብ ልብስ እና የመጽሃፍት ግዥ በበጀት እጥረት ምክንያት ሳይከፈል የቀረ በማለት በ2009 በጀት ዓመት በድምር ብር 1,052,112.89 ተከፍሎና ተመዝግቦ መገኘቱ፤

8. የውሎ አበል በኢፌድሪ ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር በ29/10/2004 በቁጥር ሲ.ሰ.ሚ.30/ጠ13/40/883 ስለመንግስት ሰራተኞች የአገር ውስጥ የቀን የውሎ አበል አከፋፈል በወጣ መመሪያ መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በዋናው ግቢ ብር 408,718.00፣ በአካዳሚክ ምርምር ክላስተር ብር 225,170.52 እና በእንስሳት ህክምና ኮሌጅ ብር 40,850.00 ብር በድምሩ ብር 674,738.52 የተማሪዎች ምርቃ በዓል ላይ ለየጥበቃ ሠራተኞች ከመደበኛ ስራቸው ውጪ ለሰሩበት የአስተዳደር ስራን በማስተባበር ለሰሩበት፣ ለማስተርስ ድርሳን አስፈፃሚዎች ለአስተባበሩት፣ በተለያዩ የስብሰባ ጊዜ ለአስተባበሩበት፣ በትርፍ ሰዓት ለሰሩ በሚል ሰራተኞቹ ለስራ ጉዳይ ከሚሰሩበት ቦታ ወደ ሌላ ባልሄዱበት ሁኔታ አለአግባብ በውሎ አበል ተመን መሰረት ክፍያ ተፈጽሞ መገኘቱ፤

9. የህንጻ ተቋራጮች እና ዩኒቨርሲቲው በገቡት የውል ስምምነት መሰረት ግንባታው 80% ሲሆነው ህንጻ ተቋራጮቹ የወሰዱትን ቅድሚያ ክፍያ ሙሉ ለሙሉ ተመላሽ ማድረግ እንዳለባቸው ይገልጻል፡፡ በዚሁ መሰረት በግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት በተሰጠን የግንባታዎች ያሉበት ደረጃ መረጃ መሰረት ኦዲት ሲደረግ፡ ደመራ ኢንጅነሪንግ ኮንስትራክሽን የተማሪዎች ማደሪያ ህንጻዎች ግንባታ ተራቋጩ ስራውን 100% አጠናቆ ርክክብ ተፈጽሞ ተማሪዎች እየኖሩበት ሳለ በተቀጽላ ሌጀር ኮድ 0011 ብር

1,293,000.75 የግንባታ ቅድመ ክፍያ በውሉ መሰረት ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤

10. የፌደራል መንግስት የሂሳብ አያያዝና አወቃቀር ስርዓት መመሪያ በግልፅ እንደተቀመጠው በ6412 የሂሳብ መደብ ተመዝግቦ ወጪ ማድረግ የሚቻለው ነፃ የአስተዳደር እና መንግስታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች የሚሰጥ ድጋፍ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ይሁን እንጂ በዋናው ግቢ ከመደበኛ በጀት ብር 499,999.99 እንዲሁም ከውስጥ ገቢ ብር 500,000.00 በድምሩ ብር 949,999.99 ነፃ ላልሆኑ የአስተዳደር እና መንግስታዊ ለሆኑ ድርጅቶች ከውስጥ ገቢና ከመደበኛ በጀት ክፍያ መፈፀሙ፤

11. በድምሩ ብር 1,106,428.89 ከሀረማያ አካባቢ ገበሬ ህብረት ስራ ዩኒየን የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ ሆኖ ሳለ መቀነስ ያለበት ታክስ ያልተቀነሰ እና ለሚመለከተው ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት ገቢ ያልሆነ መሆኑ፤

3. **የተሠብሣቢ ሂሣብ በተመለከተ፤**

- በ4203 የሂሳብ መደብ የሚታይና ለደመወዝ ቅድመ ክፍያና ለውሎ አበል ለተለያዩ ግለሰቦች ተሰጥቶ ሳይሰበሰብ ከአንድ ዓመት እስከ አምስት አመት የቆየ ብር 1,476,464.66 ተሰብሳቢ ሂሳብ መኖሩ፤
- በ4211 የሂሳብ መደብ ለተለያዩ እቃዎች መግዣ በቅድሚያ ክፍያ ወጪ ሆኖ በጊዜ ገደቡ ሳይወራረድ ከአንድ ዓመት በላይ የቆየ ብር 3,883,712.79 መኖሩ፤
- በ4253 የሂሳብ መደብ ላይ የሚታይና ለተለያዩ ድርጅቶችና እቃ አቅራቢዎች ተሰጥቶ ከአራት አመት እስከ አስር ዓመት የቆየ ብር 4,832,924.09 መኖሩ፤
- በ4274 የሂሳብ መደብ ላይ የሚታይ እና ሌሎች በሚለው በቅድሚያ ክፍያ ወጪ ሆኖ በጊዜ ገደቡ ሳይወራረድ ከሁለት አመት እስከ አስር ዓመት የቆየ ብር 34,996,962.20 መኖሩ፤ በጠቅላላ በድምሩ ብር 45,190,063.74 በወቅቱ ሳይወራረድ የቆየ ሂሳብ መገኘቱ፤

4. **የተከፋይ ሂሣብ በተመለከተ፤**

- በ5002 የሂሳብ መደብ የሚታይ ልዩ ልዩ ተከፋይ ሂሳብ ለሚመለከተው አካል ሳይከፈል ከአምስት አመት በላይ የቆየ ብር 2,191,655.67 መኖሩ፤

- ❖ በ5004 የሂሳብ መደብ የሚታይና የደመወዝ ተከፋይ ሂሳብ ለሚመለከተው አካል ሳይከፈል ከአንድ አመት በላይ የቆየ ብር 137,883.60 ሂሳብ መኖሩ፤
- ❖ በ5054 የሂሳብ መደብ የሚታይና ሌሎች ተከፋይ ሂሳቦች ለሚመለከተው አካል ሳይከፈል ከአምስት አመት በላይ የቆየ ብር 538,457.62 ሂሳብ መኖሩ፤ በጠቅላላ በድምሩ ብር 2,867,996.89 በወቅቱ ሳይከፈል የቆየ ሂሳብ መገኘቱ፤

5. **በጀት በተመለከተ፤**

ለካፒታል በጀት ከተደለደለው ብር 108,058,251.10 ውስጥ ብር 99,795,628.90 በ2008 በጀት ዓመት የዞረ በ2009 በጀት ዓመት በመክፈቻ ሂሳብ የተመዘገበ እና የተወራረደ በመሆኑ ልዩነቱ ብር 8,262,622.20 ከበጀት በላይ ስራ ላይ የዋለ መሆኑ ታውቋል፡፡

ከላይ በተገለፁት ጉልህና መሠረታዊ ልዩነቶች የተነሳ በእኛ አስተያየት የዩኒቨርስቲው የሂሳብ መግለጫዎች ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም የተመለከተውን የፋይናንስ አቋም እና የበጀት ዓመቱን የሥራ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በአጥጋቢ ሁኔታ አያሳይም፡፡

<u>**ትኩረት የሚያሻቸው ጉዳዮች፤**</u>

- ❖ በ2008 በጀት ዓመት ከዶሮ እርባታ በአጠቃላይ ከ12,560 ዶሮዎች ብር 1,336,187.50 ገቢ ሲገኝ በ2009 በጀት ዓመት ደግሞ በአጠቃላይ 19,510 ዶሮዎች ብር 870,962.50 ገቢ የተገኘ ሲሆን ከባለፈው በጀት ዓመት ጋር ሲነጻጸር በልዩነት ብር 465,225.00 ገቢው የቀነሰ ከመሆኑ በላይ ከዶሮ እርባታው ጋር በተያያዘ ተገቢውን የውስጥ ቁጥጥር ስርዓቱ ማለትም ቢን ካርዶች፣ የተለያዩ መዝገቦች በትክክል እየተመዘገበ እና እየተረጋገጠ ከወጪ ቀሪው ምን ያህል እንደሆነ ወቅታዊ የሆነ ምዝገባ የሌለው መሆኑ፣
- ❖ በ2008 በጀት ዓመት ከአሳማ እርባታ በአጠቃላይ ከ65 አሳማዎች ብር 158,350.00 ገቢ ሲገኝ በ2009 በጀት ዓመት ደግሞ በአጠቃላይ ከ108 አሳማዎች ብር 105,000.00 ገቢ የተገኘ ሲሆን ከባለፈው በጀት ዓመት ጋር ሲነጻጸር በልዩነት ብር 53,350.00 ገቢው የቀነሰ ከመሆኑ በላይ ከአሳማ እርባታው ጋር በተያያዘ 4 አሳማዎች የህይወት ታሪካቸው ማለትም ክብደታቸው፣ ከተወለዱ ምን ያህል ጊዜ እንደሆናቸው ሳይረጋገጥ የተገዙ መሆኑ፣ ክፍሉ የአሳማዎቹን የሽያጭ ዋጋ በመጨመር አሳማዎቹን የሚገዛቸው የጠፋ ከመሆኑ በላይ አሳማዎቹ ከመጠን በላይ

ክብደት እየጨመሩ ለሽያጭ በማይቀርቡበት ሁኔታ ያሉ መሆናቸውና በክፍሉ ውስጣዊ አሰራር ተገቢውን የሆነ ውሳኔ ወይም እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፣

ሌሎች ጉዳዮች

ምንም እንኳን በሂሳብ መግለጫዎች ላይ ቀጥተኛ ተፅዕኖ ባይኖራቸውም መሠረታዊና ጉልህ የሆኑ የውስጥ ቁጥጥርና የአፈጻጸም ድክመቶች ቀጥለው ተመልክተዋል፡፡

የአላቂ እና የቋሚ እቃዎች የንብረት አያያዝን በተመለከተ፣

የዩኒቨርሲቲው የንብረት አያያዝ፤ አጠባበቅና አጠቃቀም በፌዴራል መንግሥት የንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መሠረት በዩኒቨርስቲው ያለ አገልግሎት በተቀመጡ ቋሚ ንብረቶችና አላቂ ንብረቶች ላይ በመመሪያው መሠረት እርምጃ መውሰዱን እንዲሁም በንብረት ሂሳብ ላይ አግባብ ያለው የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት የተዘረጋ መሆኑን እንዲሁም ለቋሚ ንብረቶች ተገቢው እንክብካቤና አካላዊ ጥበቃ መደረጉን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

- በቋሚ በስቶር ክፍል ተመድበው የሚሰሩ ሰራተኞች ንብረት የመያዝ በሞዴል 19 ገቢ የማደረግና በሞዴል 22 ንብረት ወጪ የማድረግ ሃላፊነቶችን በአንድ ሠራተኛ የሚሠራ መሆኑ፤
- ለቋሚ እቃ የገቢና ወጪ መከታታያ (ስቶክ ካርድ) የማይዘጋጅ መሆኑ፤
- የአላቂ የገቢና ወጪ መከታታያ (ስቶክ ካርድ) ምዝገባ እየተከናወነ ቢሆንም የንብረቱ መነሻ ምዝገባ መሠረቱ የማይታወቅ እና እየተመዘገበ ያለውም ምዝገባው ወጥነት የሌለው መሆኑ፤
- የተለያዩ ለቧንቧ ዝርጋታ የሚያገለግሉ በርከት ያሉ የእቃ መሳሪያዎች እና እንዲሁም ቋሚ እና አላቂ እቃዎች ንብረቱን በማን ወጪ እንደተደረገና ባለቤታቸው የማይታወቅ በተለያየ ቦታ በግቢ ውስጥ ለሚገኙ ኮንቴይነሮች ውስጥ ተከማችቶ የሚገኙ መሆኑ፤
- የተለያዩ የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች በረጅም ጊዜ ግልጋሎት እና በብልሽት ምክንያት ወደ ንብረት ክፍል ተመላሽ በሚሆንበት ጊዜ እና ከጥገና ክፍል አዲስ ዕቃ ወጪ ተደርጎ ለጥገና በሚውልበት ጊዜ ተጠግኖ የተቀየረው ዕቃ አሮጌው ወደ ንብረት ክፍል ተመላሽ በሚደረግበት ጊዜ፤ ቀድሞ የወጣ ዕቃ መሆኑ መለያው ቁጥር ተረጋግጦ ገቢ የማይደረግ መሆኑ፤
- ንብረት (የቋሚና አላቂ) የሚያንቀሳቅሱ (የሚይዙ) ሠራተኞች በተለያየ ምክንያት የሥራ ክፍል ሲቀይሩ ወይም ተቋሙን ሲለቁ ማስረከብ በሚገባቸው ልክ ለማስረከባቸው ያስረከቡት ከወጪ ቀሪ ትክክለኛነት በውስጥ ኦዲት የማይረጋገጥ መሆኑ፤

- የመኪና መለዋወጫ፤ የኤሌክትሪክ እና የቧንቧ ዕቃዎች በዋናው ግምጃ ቤት ንብረቶቹ ገቢ ተደርገው፤ ለሚፈለገው አገልግሎት በሚዘጋጅበት ወቅት በዋናው ግምጃ ቤት ወጪ ተደርጎ በቀጥታ ለሚፈለገው አገልግሎት ማዋል ሲገባ፤ ከዋናው ስቶር ወደ ጊዜያዊ (ሚኒ) ስቶር ገቢ የተደረጉት ንብረቶች ተገቢው ከወጪ ቀሪ ምዝገባ የሚያሳይ ስነ-ስርዓት (Stock card) በሌለበት፤ ንብረቶቹ በየቀኑ ከሚኒ ስቶር ወደ ሚመለከተው የስራ ክፍል ወጪ የሚደረጉ (የሚሰራጩ) በመሆኑም ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች የንብረቶቹ ወጪ ተቋሙ ለተጠቀመበት አገልግሎት የዋለ መሆኑን ለማረጋገጥ አዳጋች መሆኑ፤

<u>የተማሪዎች ምግብ ግምጃ ቤት፤ የመምህራን መዝናኛ ክበብ ግምጃ ቤት እና ሪሶርስ ግምጃ ቤት ፤</u>

- የተማሪዎች የምግብ ግምጃ ቤት ጤፍ ለማስፈጨት የወጣው እና ተፈጭቶ የመጣው የጤፍ ዱቄት ተገቢው መረካከቢያ ጤፉን ለማስፈጨት ከወሰደው አካል ጋር ባለመኖሩ፤ የወሰዱትን ጤፍ እና ፈጭተው የመለሱትን የጤፍ ዱቄት ተመዝኖ ርክክብ የማይደረግ መሆኑ እንዲሁም ዛላ በርበሬ ፤ምስር ክክ ለአበባሪ ሰራተኞቹ በየጊዜ የሚሰጥ ሲሆን ተበጥሮ ካበቃ በኋላ የተሰጣቸው መጠን መልሶ ሲያሰረክቡ ተመዝኖ ርክክብ የማይፈፀም መሆኑ፤

<u>በዋናው ግቢ የተበላሹ ንብረቶችን በተመለከተ</u>

- በወድ ዋጋ የተገዙ አዳዲስ 6 የምርጥ ዘር የማጣሪያ ማሽን ከ12 ዓመት በላይ ያለምንም አግልጋሎት የተቀመጠና የተቀመጠበትም ሁኔታ ጥንቃቄ በጎደለው ሁኔታ መሆኑ፣
- በውድ ዋጋ የተገዛ አዲስ የኑግ ዘር መዝርያ ማሽን ያለ አገልግሎት ለብዙ አመታት የቆየና የተቀመጠበትም ሁኔታ ጥንቃቄ በጎደለው ሁኔታ መሆኑ፣
- ከአስተዳደር ህንፃ ጀርባ የሚገኝ ትልቅ ጄኔሬተር በብልሽት ምክንያት በሚል ያለምንም አገልግሎት የተቀመጠ፣
- በቤተ መፅሐፍት/ዋናው / ውስጥ የሚገኙ 5 ፕሪንተርና የኮፒ ማሽኖች በብልሽት ምክንያት ግልጋሎት የማይሰጡ መሆኑ፣
- አዲስ 3 ግዙፍ የዳቦ መጋገርያ ማሽኖች ያለአገልግሎት የቆሙ፤
- አንድ የልብስ ማጠብያ ማሽን በብልሽት ምክንያት ያለአገልግሎት የቆመ፣
- አንድ የዳቦ መቁረጫ ማሽን በብልሽት ምክንያት ያለአገልግሎት የቆመ፣
- የውሃ ማሞቂያ ማሽን በብልሽት ምክንያት ያለአገልግሎት የቆመ፣
- አግሪካልቸር ላቦራቶሪ ወስጥ በወድ ዋጋ የተገዛ Autoclave /የባክቴሪያ መሳሪያ / ያለአገልግሎት በብልሽት ብዙ አመት የቆመ ማሽን፣

- በብልሽት ምክንያት ያለአገልገሎት የተቀመጡ 2 ፍሪጅ ፣
- Plan science/agronomy laboratory ውስጥ2 Gross champers የማይሰሩ፣

ማዕከላዊ ላብራቶሪ

- በወድ ዋጋ የተገዛ Termowagee የተባለ ማሽን ያለምንም ብልሽት የተቀመጠ ቢሆንም ነገር ግን ለዚህ ክፍል የማይሆንና ለምህንድስና ክፍል የሚሆን ቢሆንም ያለአግባብ በዚህ ክፍል ውስጥ የተቀመጠ፣

ሶይል ኬሚስተሪ ላብራቶሪ

- ሁለት Hud የተባለ የኬሚካል ጭሶችን ወደ ውጪ የሚያስወግድ መሳሪያ ሲሆን በብልሽት ምክንያት የቆመ፤
- Distiller የተባለ የተጣራ ውሃ ማውጫ ሲሆን 600W የሚጠቀም ቢሆንም ነገር ግን የሀይል አቅም አነስተኛ መሆኑ ያለምንም ብልሽት የተቀመጠ፤
- Distiller የአፈር ማጣርያ ማሽን /የናይትሮጂን መስርያ ማሽን ሲሆን በብልሽት ምክንያት አገልግሎት የማይሰጥ፣
- ሁለት ፍሪጅ በብልሽት ምክንት በሚል አገልግሎት የማይሰጥ በመሆኑም ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች የተለያዩ ማሽኖች በተለያዩ ምክንያት ግልጋሎት ላይ እየዋሉ ባለመሆናቸው ዩኒቨርሲቲውን እንዲሁም መንግስትን ላላስፈላጊ ወጪ እየተዳረገው መሆኑ፤

<u>**ተሽከርካሪዎች እና የነዳጅ አጠቃቀምን በተመለከተ**</u>፣

- ቁጥራቸው 20 የሚሆኑ ተሽከርካሪዎች የሚወገዱ በሚል የቆሙ፤
- 17 ተሽከርካሪዎች እያንዳንዳቸው ተጠግነው አገልግሎት ላይ የሚውሉ እና አገልግሎት ላይ የማይውሉ ለመሆናቸው ምንም አይነት ውሳኔ ሳያገኙ የቆሙ ፣
- የሰሌዳ ቁጥር ኢ.ቲ ኮድ 4-01398 መለዋወጫ አልተገኘለትም ያለምንም አገልግሎት የቆመ፤
- በተለያዩ ምክንያቶች የቆሙ በርከት ያሉ ተሽከርካሪዎች ካለመጠለያ የቆሙ መሆኑ፣
- 8 ትራክተሮች በብልሽት ምክንያት የማይሰሩ እና ከነዚህ ውስጥ ሦስቱ ሞተር የሌላቸው መሆኑ፣
- 11 ትራክተሮች የህይወት ታሪካቸውን የሚገልጽ ማህደር የሌላቸው መሆኑና የትራክተሮቹ ብዛት በውል የማይታወቅ መሆኑ፣
- የተለያዩ የትራክተር መለዋወጫ ዕቃዎች እና ጎማ ጥንቃቄ በጎደለው መልኩ የተቀመጡና አብዛኞቹም በአቀማመጥ ምክንያት ሙሉ ለሙሉ የተባላሹ መሆናቸው፣

- 14 ሞተር ሳይክሎች ተበላሽተዋል በሚል የቆሙ እንዲሁም አቀማመጣቸው ጥንቃቄ የጎደለው መሆኑ፣
- ዩኒቨርሲቲው የመኪና ነዳጅ ግዥ ፈጽሞ የተገዛው ነዳጅ ወደ ነዳጅ ማጠራቀሚያው ጉድጓድ ገቢ በሚደረግበት ጊዜ የነዳጅ ማደያ ንብረት ሠራተኛ ነዳጁን በመጠን ምን ያህል እንደተረከበ በፊርማ የሚያረጋግጥበት መሰረታዊ የስቶክ መዛግብቶችን በሞዴል 19 እና ስቶክ ካርድ በመጠቀም አስፈላጊውን ምዝገባ ሙሉ በሙሉ የማይመዘገብ መሆኑ፤
- የነዳጅ ማደያ ሠራተኛ በሞደል 20 በታዘዘበት መሠረት ለተሽከርካሪዎች እና ለተለያየ አገልግሎት ናፍጣና ነዳጅ እየተቀዳ የሚሞላው ህጋዊነት በሚያረጋግጥበት መሰረታዊ የስቶክ መዛግብቶችን ሞዴል 22 እና እስቶክ ካርድ በመጠቀም አስፈላጊውን ምዝገባ ሙሉ በሙሉ የተቀዳ ናፍጣና ነዳጅ የማይመዘገብ በመሆኑ በነዳጅ ማጠራቀሚያው ጉድጓድ እንዲሁም በርሜል ውስጥ ያለው ከወጪ ቀሪ ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፤
- ሠራተኛው በአግባቡ ለሥራ የሚያስፈልጉ ሠነዶች ማለትም የነዳጅ ማዘዣው ሞ/20 በአግባቡ ተይዘው የተቀመጡ ባለመሆኑ በዓመቱ ወጪ የሆነውን ናፍጣ እና ነዳጅ ትክክል ለመሆኑ ማነጻጸር ያልተቻለና ቢሮ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች ያልተሟሉለት በመሆኑ ከናፍታና ከነዳጁ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሰነዶች በአግባብነት ያልተያዙ መሆኑ፤
- ጀኔሬተሮቹን ለማንቀሳቀስ በሰዓት ወይም በቀን የሚያስፈልገው የነዳጅ መጠን ጥናት ተደርጎ መጠኑ ባለመወሰኑ የመቆጣጠሪያ ስልት የሌለ መሆኑ፤
- የጀኔሬተር ኦፕሬተር የሥራ ክፍል ሠራተኞች /ኦፕሬተሮች/ ለማሽኖቹ የሚያስፈልገውን ነዳጅ በነዳጅ መጠየቂያ ቅጽ ላይ በመሙላት በሚመለከተው የሥራ ክፍል ኃላፊ የሚረጋገጥበት ሥርዓት የሌለ መሆኑ፤
- ለጀኔሬተሮች የዋለው የነዳጅ ፍጆታ ብዛትና የገንዘብ መጠን የሚገልጽ በማስረጃ የተደገፈ ሪፖርት ለማኔጅመንቱ ወይም ለሚመለከተው የስራ ሂደት የማይቀርብ በመሆኑም ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች ለነዳጅ የወጣው ወጪ ተቋሙ ለተጠቀመበት አገልግሎት የዋለ መሆኑን ለማረጋገጥ አዳጋች መሆኑ

መድሃኒትና ለመድሃኒት አገልግሎት የሚውሉ መሳሪያዎች አያያዝ እና አጠባበቅ ፣

በህክምና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ

- ከሆስፒታሉ የመድሃኒት መጋዘን ወደ ተለያዩ አገልግሎት መስጫ እና ማደያ ክፍሎች ከመሰራጨቱ በፊት ከሚሰጡት አገልግሎት አኳያ የመድሃኒትና ህክምና

ኮሚቴ ለየክፍሎቹ በሚያዘጋጀው መዘርዝር መሰረት አለመሆኑ እና ይህ አሰራር በሆስፒታሉ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፣

- ሆስፒታሉ የመድሃኒት ቆጠራ በሚያደርግበት ወቅት የቆጠራው ውጤት ከመድሃኒት መቆጣጠሪያ መዝገቦች እና ከሂሳብ ሪፖርት ጋር ያልተገናዘበ መሆኑ፣
- በመድሃኒት ማደያ ክፍሎች የመድሃኒት ክምችት እና እንቅስቃሴን ለመከታተልና ለመቆጣጠር የሚያስችል ቢን ካርድ፣ስቶክ ካርድ ወይም ዘመናዊ ሶፍትዌር በመጠቀም ያልተቆራረጠ ወቅታዊ ምዝገባ የማይደረግ መሆኑ፣
- የአገልግሎት ጊዚያቸው ያለፈባቸው መድኃኒቶች እንዲሁም ተብላሽተው የተቀመጡ የህክምና መገልገያ መሳሪያዎች በአንድ የንብረት ክፍል ውስጥ ከመቀመጣቸው በተጨማሪ መሳሪያዎቹ ተጠግነው አገልግሎት ሊሰጡ እንደሚችሉና እንደማይችሉ በባለሙያ ሳይለይና ሳይረጋገጥ ለረዥም ጊዜ የተቀመጡ መሆኑ፣
- የሆስፒታሉ ፋርማሲ ክፍል በቁጥር 2/2071/51/2 በቀን 19/10/2009 ለኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድሃኒትና የጤና እንክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን ድሬዳዋ ቅርንጫፍ ብዛት ያላቸው የአገልግሎት ጊዜያቸው ያለፈባቸው መድኃኒቶች እንዲወገዱ ቢጠይቅም ሳይወገዱ ከሶስት ዓመት በላይ የቆዩ መሆኑ፣
- በላብራቶሪ ክፍል ውስጥ አዲስ ራዲዩ ሜትር በሪኤጀንት ግዥ ምክንያት ከሁለት ወር በላይ ፣ ማይንድ ድራይ ለኬሚስትሪ ስራ የሚያገለግል አንድ ዓመት፣ ሁማልላይት ፕላስ ስምንት ወር ፣ ጂን ኤክስፐርት ሁለት ወር ፣ ሁለት ፍሪጆች ከአንድ ዓመት በላይ አገልግሎት ሳይሰጡ የቆዩ መሆኑ፤

<u>**በዋናው ግቢ**</u>

- በዋና ስቶር `መድሃኒት ስቶር ክፍል ተመድቦ የሚሰራ ሰራተኛ ንብረት የመያዝ፣ ገቢና ወጪ በሞደል 19 እና 22 የማድረግ ሃላፊነቶችን በተደራቢነት የሚሰራ መሆኑ፤
- ከዋናው የመድኃኒት ስቶር መድኃኒት ወጪ ሆኖ ወደ መድኃኒት ማደያው (Dispensary room) የገባው መድሃኒት፤ ለመውጣቱ /ለመሰራጨቱ/ ማረጋገጫ የፕሪስክሪፕሽን ወረቀት ቢኖርም ከዋናው የመድኃኒት ስቶር የወጣው መድኃኒት እና በፕሪስክሪፕሽን ወረቀት ላይ የተመዘገበው መድኃኒት ተገናዝቦ ከወጪ ቀሪ መከታታያ (ስቶክ ካርድ) እና ቢን ካርድ ምዝገባ የማይከናወን ከመሆኑም በተጨማሪ መድኃኒቱ ተሰራጭቶ ሥራ ላይ የዋለው መድኃኒት ምን ያህል እንደ ተሰራጨ በአይነት እና በገንዘብ መጠን ተዘጋጅቶ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት የማይደረግ መሆኑ፡

በ2008 በጀት ዓመት ኦዲት ሪፖርት በተሰጠው አስተያየት ላይ እርምጃ ያልተወሰደባቸው ጉዳዮች፤

- የውል ግዴታውን ካልፈጸመ አንድ መምህር ብር 111,168.00 ግንቦት 9/2006 ለተቋሙ እንዲከፍል የተወሰነ ሲሆን ገንዘቡ ከባለጉዳዩ ተመላሽ ተደርጎ ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፤
- የመኖሪያ ቤት ለተሰጣቸው መምህራን በበጀት ዓመቱ (2008ዓ.ም) አላግባብ ብር 158,200.00 የቤት አበል የተከፈለና ገንዘቡ ተመላሽ ያልሆነ መሆኑ፤
- ውጭ አገር ትምህርታቸውን ለሚከታተሉ አካዳሚክ ባለሙያዎች ግማሽ ደመወዝ መከፈል ሲገባው በበጀት ዓመቱ ሙሉ ደመወዝ በመከፈሉ በድምሩ ብር 246,996.00 አላግባብ በብልጫ የተከፈለ የደመወዝ ተመላሽ ያልሆነ መሆኑ፣
- ለተለያዩ ኮሚቴዎች ላስተባበሩበት፣ ለተሳተፉ ሰራተኞች ማትጊያ በሚል በድምሩ ብር 589,908.61 አለአግባብ ተከፍሎ ተመላሽ ያልሆነ መሆኑ፣
- በተከታታይ ትምህርት መርሃ-ግብር ላስተማሩ መምህራን በአስተዳደር ካውንስል በተወሰነው ተመን መሰረት በበጀት ዓመቱ ብር 1,822,579.00 በመመሪያው ከተፈቀደው ተመን በላይ ለአካዳሚክ ባለሙያዎቹ ከውስጥ ገቢ ክፍያ የተፈፀመ መሆኑ፤
- ለድህረ ምረቃ (Msc and Phd) ተማሪዎች ፈተና ለፈተኑበት/ለገመገሙበት (Internal and External Examiner/Session) እና የማማከር አገልግሎት ለሰጡበት (Supervision) በጥቅሉ የHonorarium ክፍያ በሚል እንደ ትምህርት ደረጃው ከሚመለከተው አካል የጸደቀ የክፍያ ተመን ሬት ሳይኖረው በአስተዳደር ካውንስል በተወሰነው ተመን መሰረት በድምሩ ብር 1,418,020.00 ክፍያ የተፈፀመ መሆኑ፤
- በዩኒቨርሲቲው ህንፃ ግንባታ ሥራ ላይ ከተሰማሩት የስራ ተቋራጮች መካከል፤ ባቢሌ የምርምር ማዕከል ግንባታ ላይ የተሰማራው የሥራ ተቋራጭ (ተስፋዬ አስፈሪ) ብር 304,051.45፤ ጉርሱም የምርምር ማዕከል ግንባታ ላይ የተሰማራው የሥራ ተቋራጭ (ዳዊት ግርማይ) ብር 1,838,862.40፤ የማባዣ ክፍል ግንባታ ላይ የተሰማራው የሥራ ተቋራጭ (ተክለሐይማኖት አስገዶም) ብር 668,635.00 እና የእንስሳት ህክምናና ቄራ ግንባታ ላይ የተሰማራው የስራ ተቋራጭ (ኮባልት) ብር 450,590.60፤ በድምሩ ብር 3,262,139.45 የወሰዱት የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ እያለባቸው ውለታቸው የተቋረጠ መሆኑ፤
- በጤና ሳይንስ ኮሌጅ በአገራዊ ስልጠና ላይ ለተሳተፉ 624 ሠራተኞች ለተከፈለው የምሣ አበል ብር 154,853.25 እና የማህበረሰብ አቀፍ ትምህርት ክፍል የተግባር ልምምድ ከሚያደርጉ ከየጤና ተቋማት የተወጣጡ የምርምር ዘዴ ሥልጠና ለወሰዱ

አሰልጣኞችና ለ44 ተሳታፊዎች ለተከፈለው ብር 76,437.00፤ በድምሩ ለብር 231,290.25 ተሳታፊዎቹ በትክክል ስልጠና ላይ መሳተፋቸውን የሚያመለክት የሥራ መከታተያ (Attendance Sheet) ያልቀረበ መሆኑ፤

- ❖ በዩኒቨርሲቲው በህንፃ ግንባታ ሥራ ላይ የተሰማሩ 4 የስራ ተቋራጮች (መላ ኢንጂነሪንግ፤ ደመራ ኢንጂነሪንግ፤ ጉሌድ ኮንስትራክሽንና እምነቴ እንዳሻው ኮንስትራክሽን) ለብር 17,672,437.04 የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና ያላቀረቡ እና ብር 14,964,325.86 የቅድሚያ ክፍያ የሚፈለግባቸው 3 የስራ ተቋራጮች (ጫላ ኮንስትራክሽን፤ ኤም ኮንስትራክሽንና ሳፍኮን ኮንስትራክሽን) ደግሞ ያቀረቡት ዋስትና ያልታደሰ /ጊዜው ያለፈበት/ መሆኑ፤
- ❖ ወደተለያዩ ተቋማት ለትምህርት ተልከው በገቡት ውለታ መሰረት ባለመፈፀማቸው የሚፈለግባቸው የገንዘብ መጠን ገና ያልታወቀና ክስ ያልተመሰረተባቸው በበጀት ዓመቱ (2008) ብዛት 46፤ ከ1992 እስከ 2007 ብዛት 92 በድምሩ 128 የፍትሐ ብሄር ጉዳዮች ለህግ አገልግሎት የተመሩ ቢሆንም ያለምንም እርምጃ የሚገኙ መሆኑ፤
- ❖ የዩኒቨርሲቲው የስራ ክፍሎች ስራቸውን ለማከናወንና ተፈላጊውን ውጤት ለማስገኘት ለተሰጣቸው መደበኛ የስልክ መስመሮች ወርሃዊ ተመን ያልወጣላቸው (የአጠቃቀም ቁጥጥር የማይደረግ) መሆኑ፤
- ❖ 4 ተሽከርካሪዎች የሠሌዳ ቁጥር የሌላቸው መሆኑ፤የተቋሙ ተሽከርካሪዎች የተሟላ የህይወት ታሪክ ማህደር የሌላቸው መሆኑ፤
- ❖ አሮጌ ተመላሽ የመለዋወጫ ዕቃዎች መረካከቢያ የሌለ መሆኑ፤የመለዋወጫ ዕቃ ግምጃ ቤት ሠራተኛ ከግንቦት 1/2005 ጀምሮ ወደ ሌላ ሥራ ሲመደቡ በእጃቸው ያለው ንብረት እስካሁን ርክክብ ያልተፈፀመ መሆኑ፤
- ❖ የምግብ ዕቃዎች የንብረት ገቢና ወጪ ደረሰኞች (ሞ/19) እና ሞ/22) የመያዝ፤ የማዘጋጀት፤ ስቶር ሳይኖራቸው ንብረቶቹን የመረከብና በሞዴል 22 ለምግብ ዕቃ የክምችት ግምጃ ቤት ሠራተኛ የማስተላለፍ ሥራ በአንድ ሠራተኛ የሚከናወን መሆኑ፤
- ❖ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የምግብ ጥሬ ዕቃዎች ቆጠራ እየተደረገ ከወጪ ቀሪ ትክክለኝነት እንዲረጋገጥ ያልተደረገ መሆኑ፤
- ❖ የአተር ክክ፤ ድፍንና የተከካ ምስር ከምግብ ክምችት ግምጃ ቤት ለዝግጅት (ለማበጠር ሲተላለፍ) ርክክብ በጽሁፍ ወጪ የሚደረግበት አሠራር ካለመኖሩም በተጨማሪ ከተዘጋጀም (ከተበጠረ) በኋላ ተመልሶ ወደ ክምችት ግምጃ ቤት ሠራተኛዋ ሲተላለፍ እየተመዘነ ርክክብ ሳይፈጸም በቀጥታ ለአገልግሎት (ለወጥ ቤት) እየተጠየቀ ወጪ የሚደረግ መሆኑ፤

- 5 ትልልቅ ዳቦ መጋገሪያ ማሽኖች አገልግሎት መስጠት የሚችሉ መሆን አለመሆናቸው በትክክል የማይታወቅ በተለያዩ ክፍሎች የሚገኙ መሆኑ፤
- የበሰሉም ሆነ ያልበሰሉ የምግብ ዕቃዎች ርክክብ ወቅት የተማሪዎች ተወካይ የሚገኙ ለመሆኑ ማረጋገጫ ያልቀረበ መሆኑ፤
- በግዢና በዕርዳታ የሚመጡ መድሃኒቶችና የህክምና ዕቃዎች በማዕከላዊ ግምጃ ቤት ከሙያው ጋር አግባብ በሌላቸው ሠራተኛ የንብረት ገቢና ወጪ (ሞ/19 እና ሞ/22) የሚዘጋጅላቸው መሆኑ፤
- ለመድሃኒቶችና ሌሎች አላቂ የህክምና ዕቃዎች በግምጃ ቤቱ ባለሙያ ከሚጠበቅ ቢን ካርድ በስተቀር የገቢና ወጪ መከታተያ የሌለ መሆኑ፤
- በዋናው ግቢ የመድሃኒት ማደያ (Dispencery room) የተረከቡትና ያደሉትን የሚያመለክት ምዝገባ ካለመኖሩም በተጨማሪ የሥራ ክፍሉ 4ቱም ባለሙያዎች (ድረጊስት) በፈረቃ ሲቀያየሩ የመድሃኒት መጥፋት ወይም መጉደል ቢከሰት በጋራ (በተናጠል) ሊጠየቁበት የሚያስችል አሠራር የሌለ ከመሆኑም በላይ ባለሙያዎቹ በተለያየ ምክንያት ሲለቁ ከወጪ ቀሪ የማይረጋገጥ መሆኑ፤
- የዩኒቨርስቲው የዋናው የመድሃኒት ግምጃ ቤት ሠራተኛ (ባለሙያ) ከታህሳስ 1/2008 ጀምሮ ለውጥ ሲደረግ በወቅቱ በግምጃ ቤት የነበረውን ርክክብ የተፈጸመ ቢሆንም አስረካቢዋ ያስረከቡት ከወጪ ቀሪ ማስረከብ በሚገባቸው ልክ ለማስረከባቸው ትክክለኛነቱ ያልተረጋገጠ ከመሆኑም በተጨማሪ የቴክኖሎጂ ካምፓስ ድረጊስቶች (ባለሙያዎች) በተለያየ ምክንያት ሲቀያየሩ ርክክብ የማይፈጸም መሆኑ፤ (ለምሳሌ፡- አሁን ወደ ዋናው መድሃኒት ስቶር የተዛወሩና ተረካቢዋ (ድረጊስት ዝናሽ በቀለ ሳያስረክቡ የለቀቁ መሆኑ)፤
- የተቋሙ ሠራተኞችና ቤተሰቦቻቸው በተማሪዎች ክሊኒክ የጹቤ አገልግሎት እንዲያገኙ የተወሰነበት የጽሁፍ ማስረጃ ካለመቅረቡም በተጨማሪ የተለያየ የሥራ ክፍል ሠራተኞች የህክምና አገልግሎት ያገኙበት ብር 4,801.00 ያልተሰበሰበ መሆኑ፤
- የቴክኖሎጂና የቨተርነሪ ካምፓሶች የተማሪዎች ክሊኒክ ከዋናው ካምፓስ መድሃኒት ስቶር ድረጊስቶቹ (ባለሙያዎቹ) ጠይቀው ሲወስዱ አስቀድሞ ከወሰዱት መድኃኒት የቀረ መኖር አለመኖሩን ወይም ሙሉ በሙሉ በሥራ ላይ መዋሉ ሣይረጋገጥ እየተፈቀደ የሚሰጥ መሆኑ፤
- በቴክኖሎጂና ቨተርነሪ ካምፓሶች ድራጊስት ባለመኖሩ ባለሙያዎቹ የሚያስፈልጋቸው መድሃኒት ከዋናው መድሃኒት ግምጃ ቤት እየጠየቁ በመውሰድ መድሃኒቱን የመያዝ፣ ህክምናውን የማከናወን፤ መድህኒት የማዘዝና የማደሉ ሥራዎች በባለሙያዎቹ የሚከናወን መሆኑ፤

- መድሃኒቶች በአንድ ወጥ የሚጠበቁበት በቂ ስቶርና መደርደሪያ (ሼልፍ) ባለመኖሩ ለመድሃኒት መጠበቂያነት ባልተሰሩ በተለያዩ ቦታዎች ለብልሽት በሚዳርግ መልኩ በወለል ላይ ተደራርበው የተቀመጡ ከመሆኑም በተጨማሪ በንግድ ማዕከል የሚገኘው የመድሃኒት ስቶር በሮቹ (ግሪል ያልተደረጉ) መስታወት በመሆናቸው ለንብረት መጠበቂያነት ሊውል የማይችል መሆኑ፤
- በግዢና በዕርዳታ የሚመጡ መድሃኒቶችና የህክምና ዕቃዎች በማዕከላዊ ግምጃ ቤት ከሙያው ጋር አግባብ በሌላቸው ሠራተኛ የንብረት ገቢና ወጪ (ሞ/19 እና ሞ/22) የሚዘጋጅላቸው መሆኑ፤
- ከቀድሞ የመጽሃፍት ግምጃ ቤት ሠራተኛ ርክክብ የተፈፀመ ቢሆንም ማስረከብ በሚገባቸው ልክ ለማስረከባቸው ትክክለኛነቱ ያልተረጋገጠ ከመሆኑም በተጨማሪ መጽሃፍት የሚፈለግባቸው መምህራን የትውስት ካርድ (ሰነድ) በኃላፊነት የተረከባቸው ሳይኖር በመጽሃፍት ግምጃ ቤት የተቀመጡ መሆኑ፤
- በኮሌጁ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ መጽሃፍቱ የሚገኙበት ሁኔታ ለማረጋገጥ ቆጠራ ያልተደረገ መሆኑ፤(በመጽሃፍት ግምጃ ቤት፤ በሰርኩሌሽንና በስታክ የሚገኙ)፤
- ዋና ግቢ
- በተለያዩ የሥራ ክፍሎች ለቢሮዎች፤ ለተማሪዎች ዶርምና ለመማሪያ ክፍሎች፤ ለመምህራን መኖሪያና ለእንግዳ ማረፊያ ቤቶች፤ ለምግብ ቤቶች፤ ለላይብራሪ አገልግሎት መስጫ ወጪ ለተደረጉ ቋሚ ንብረቶች የተሟላ መለያ ቁጥር ያልተሰጠ መሆኑ፤
- በ2005 በአቅራቢዎች ለናሙና የቀረቡ ብዛታቸው በትክክል ያልታወቀ ባለመደገፊያ ወንበሮች፤ በመመሪያው መሰረት ከ6 ወራት በላይ ያስቆጠሩ ቢሆንም ወደ ተቋሙ ገቢ ያልተደረጉ መሆኑ፤
- የተለያዩ አሮጌ የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች በአንድ ትልቅ ግምጃ ቤት ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፤
- ለአላቂ ዕቃ ገቢና ወጪ መከታተያ ስቶክ ካርድ ቢኖርም ምዝገባው ከወጪ ቀሪ መነሻ ያላደረገ ከመሆኑም በተጨማሪ የአንዱ በጀት ዓመት ከሌላው በጀት ዓመት በአግባቡ ተለይቶ የማይመዘገብ መሆኑ፤
- በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የገቢና የወጪ መከታተያ ስቶክ ካርዶች በቆጠራ ኮሚቴም ሆነ በውስጥ ኦዲት የማይዘጉ መሆኑ፤
- የመለዋወጫ ዕቃ ገቢና ወጪ መከታተያ ስቶክ ካርድ ቢኖርም ምዝገባው ከወጪ ቀሪ መነሻ ያላደረገ ከመሆኑም በተጨማሪ የተሟላ ምዝገባ የሌለ መሆኑ፤

- ከተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ መ/ቤቶችና ድርጅቶች በዕርዳታ የተገኙ መድኃኒቶችና ህክምና የህክምና መገልገያዎች ዋጋቸው ሣይታወቅ ገቢ የሚደረጉ መሆኑ፤
- ድራጊስት በፈረቃ ሲቀያየሩ በተናጠል ወይም በጋራ ሊጠየቁበት የሚያስችል አሠራር የሌለ መሆኑ ታውቋል፡፡

<u>የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት</u>

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የሐረማያ ዩኒቨርሲቲ

የ2009 በጀት ዓመት ኦዲት የሥራ አመራር ሪፖርት

መግቢያ ፣

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም ድጋሚ በወጣው የማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የሐረማያ ዩኒቨርሲቲ የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ላይ የኦዲት አስተያየታችንን ለመስጠት ያስችለን ዘንድ የዩኒቨርሲቲውን ሂሳብ ኦዲት አድርገናል፡፡

የዚህ ሪፖርት ዓላማ በኦዲታችን ወቅት የተገኙትን የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እና ሌሎች ግድፈቶች የዩኒቨርሲቲው የበላይ አመራር አካላት እንዲያውቁትና ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ ምላሽ እንዲሰጡበት ለማስቻል ነው፡፡

የኦዲቱ ወሰንና ኃላፊነት ፣

ኦዲቱ የተከናወነው ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡ ኦዲታችን፡-

- በሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩት አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረጋቸው ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎች መመዘንን ፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆናቸውን ኦዲት ማድረግን ይጨምራል፡፡

ቀጥለው በተመለከቱት የኦዲት ግኝቶች ላይ የማሻሻያ ሃሳቦችን ለመስጠት በሂሳብ መግለጫዎች ላይ ያለውን የመረጃ አቀራረብ አጠቃላይ ብቃት ገምግመናል፡፡ ይሁን እንጂ ኦዲቱ በሐረማያ ዩኒቨርሲቲ የሚታዩትን የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም፡፡

የሂሳብ መግለጫዎቹን የማዘጋጀት ኃላፊነት የሐረማያ ዩኒቨርሲቲ ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ መግለጫዎችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች ከዚህ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

1. **የጥሬ ገንዘብ እና ባንክ ሂሳብ ፣**

1.1 **በበጀት ዓመቱ መጨረሻ (ሰኔ 30/2009ዓ.ም) ፈሰስ ያልተደረገ የባንክ ሂሳብ ፤**

1.1.1 **ግኝት**

የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በቁጥር ክሂመ-39/4/30 በቀን 30/09/09 የመንግስት የባንክ ሂሳቦችን በተመለከተ በ2009 በጀት ዓመት መጨረሻ የተላለፈ የአፈጻጸም መመሪያ አንቀጽ 3 በፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች እና በከፍተኛ ተቋማት ብሎክ በሚደረጉ ሂሳቦች ላይ መደረግ ያለባቸው ተግባራት ውስጥ ባንኩ ብሎክ ያደረጋቸውን ወደ ማዕከላዊ ግምጃ ቤት ፈሰስ የሚደረገውን ሂሳብ ፈሰስ መሆኑን ክትትል ማድረግ እንዲሁም የ2010 በጀት ዓመት የሐምሌ ወር የክፍያ ጥያቄ ሲቀርብ ብሎክ የተደረገው ወደ ማዕከላዊ ግምጃ ቤት የባንክ ሂሳብ ገቢ የተደረገበትን የባንክ አድቫይስ አያይዘው ማቅረብ እንዳለባቸው ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው ፤

- በልዩ ፈንድ በባንክ ሂሳብ ቁጥር (ሐረማያ ቅርንጫፍ) 1000019938984 ብር 86, 414,656.11 ፣
- በልዩ ፈንድ በባንክ ሂሳብ ቁጥር (ድሬደዋ ቅርንጫፍ) 1000014316896 ብር 59,431,116.03 በድምሩ ብር 145,845,772.14 ዩኒቨርሲቲው በቁጥር ሐረ/አስ/ተ/ጉ/ም/ና/1264/09 በቀን 26/10/2009 ዓ.ም ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ለፊንቅሌ እና ለሐረማያ ቅርንጫፍ ብሎክ እንዲደረግ ደብዳቤ ቢጽፍም ባንኩ ብሎክ ማድረጉን ወደ ማዕከላዊ ግምጃ ቤት ፈሰስ የሚደረገውን ሂሳብ ፈሰስ መሆኑን እንዲሁም ወደ ማዕከላዊ ግምጃ ቤት የባንክ ሂሳብ ገቢ የተደረገበትን የባንክ አድቫይስ መቅረቡን ክትትል በማድረግ ማረጋገጥ ሲኖርበት ዩኒቨርሲተው በመመሪያው የተሰጠውን ተግባር ባለመፈፀሙ በባንክ መግለጫ መሰረት ሰኔ 30/2009 ከወጪ ቀሪ የተመለከተ መሆኑና ገንዘቡም ፈሰስ አለመደረጉን በኦዲቱ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

1.1.2 **ስጋት ፣**

ዩኒቨርሲቲው መመሪያ ከመጣሱም በተጨማሪ የተጠቀሰውን ገንዘብ በፈሰስ ሂሳብ ሪፖርት አለማሳየቱ ተመላሽ መሆን የነበረበት ሂሳብ በዩኒቨርሲቲው እንዲያዝ ያደርጋል፡፡

1.1.3 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u> ፣

ዩኒቨርሲቲው የተጠቀሰውን የገንዘብ መጠን ለሚመለከተው አካል ፈሰስ በማድረግ ሪፖርት ሊያቀርብ ይገባል፡፡ ለወደፊቱ ብሎክ በሚደረጉ የባንክ ሂሳቦች ላይ ዩኒቨርሲተው በመመሪያው የተሰጠውን ተግባር መፈጸም ይኖርበታል፡፡

1.1.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>፤

- ከሰኔ 30 በፊት ባንኩ በሐረማያ ዩኒቨርሲቲ ስም የተከፈቱ የባንክ ሂሳቦቹን ብሎክ እንዲያደርግና ለማዕከላዊ ግምጃ ቤት ፈሰስ እንዲያደርግልን በደብዳቤ መጠየቃችን፤
- ከሰኔ 30 በኋላ በቀጣይ ፈሰስ የተደረገበትን አድቫይዝ ለገ/ኢ/ት/ሚኒስቴር ለማድረስ ባንኩን በአካል ብንጠይቅም ባንኩ በሰኔ 30 ቀን ከዩኒቨርሲቲው በደረሰው ትዕዛዝ መሰረት ብሎክ አድርጎ ፈሰስ ያላደረገ መሆኑን ባደረግነው ክትትል መረዳታችን፤
- ከገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር የተላከውን መመሪያ ኮፒ ለባንኩ ከደብዳቤው ጋር አያይዘን የላክን መሆኑ፤
- የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ይህንን ብሎክ አድርጎ ፈሰስ የማድረግ ጉዳይ በአድራሻ ለብሔራዊ ባንክ እና ለንግድ ባንክ ጽፎ የላከና በግልባጭ ለዩኒቨርሲቲው ያሳወቀና በዚሁ ግልባጭ መመሪያ ተከትለን በሰኔ 30 ቀን ብሎክ ተደርጎ ፈሰስ እንዲሆን የጠየቅን መሆኑና በአድራሻ የተፃፈለት የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በበኩሉ በአድራሻ ተጽፎ የተላከለት በዚህ መመሪያ የደረሰውን መፈፀም የመጀመሪያ ድርሻው ቢሆንም ነገር ግን ብሎክ አድርጎ ፈሰስ አለማድረጉን በመግለፅ ይህንኑ መረዳት ካስፈለገ ባንኩ ድረስ በአካል በመሄድ በመጠየቅ መረዳት የሚቻል በመሆኑ ግኝቱ በዚሁ መሰረት እንዲታይ እና ለባንኩ ከነማስጠንቀቂያ በመግለፅ የምንፈፅም መሆኑን በትህትና እናሳውቃለን በማለት በላኩት ምላሽ ላይ ገልፀዋል፡፡

1.1.5 <u>የኦዲተሩ አስተያየት</u>፤

ዩኒቨርስቲው የባንክ ሂሳብ ብሎክ እንዲደረግ ለባንክ ደብዳቤ መጻፍ ብቻ ሳይሆን ባንኩ ብሎክ መደረጉን፤ ወደ ማዕከላዊ ግምጃ ቤት ፈሰስ የሚደረገው ሂሳብ ፈሰስ መደረጉን እንዲሁም ብሎክ የተደረገው ወደ ማዕከላዊ ግምጃ ቤት የባንክ ሂሳብ ገቢ የተደረገበትን የባንክ አድቫይስ መቅረቡን በወቅቱ መከታተል እና ማረጋገጥ ነበረበት፡፡ በመሆኑም የተጠቀሰውን የገንዘብ መጠን ለሚመለከተው መ/ቤት ፈሰስ በማድረግ ሪፖርት ሊያቀርብ ይገባል፡፡

2. <u>የገቢ ሂሳብ፤</u>

2.2 ከተገኘው ጥቅም ላይ ያልተቀነስ ቅድመ -ታክስ፤

2.2.1 ግኝት

የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀፅ 91 የግብር ከፋይ መለያ ቁጥርን ባለመጠቀም የሚጣል መቀጮ በሚለው ርዕስ ስር ባሉት ንዑስ አንቀፅ 1 ላይ ግብር ከፋዩ ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ግብር ቀንሶ ለሚያስቀረው ሰው የግብር ከፋይ መለያ ቁጥሩን ያላቀረበ እንደሆነ ግብር ቀንሶ የሚያስቀረው ሰው ከተከፋይ ሂሳብ ላይ 30 ፐርሰንት ቀንሶ ገቢ ማድረግ እንዳለበት በሚያዘው መሰረት ስለመፈፀሙ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

- የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ፈቃድ ላላቀረቡ ለማስተርስ ዲግሪ እና ለፔኤች ድግሪ በሚዘጋጅ የጥናት ምርምር ጹሑፍ / Thesis Dissertation Research Examiner / እንግዳ ፈታኝ መምህራን ከሚከፈላቸው ክፍያ ላይ 30 ፐርሰንት ቅድመ ታክስ ቀንሶ ብር 79,440.00 ገቢ ማድረግ ሲገባ ከፈታኝ መምህራን ያልተቀነሰና በቀን 28/10/09 ዓ.ም በሂሳብ ማዘዣ ቁጥር 3260/09 ከቅደመ-ታክሱ ብር 32,031.04 አለአግባብ በዩኒቨርሲቲው የተሸፈነ መሆኑ፤

ዝርዝር ሁኔታ ከታች በአባሪ ቁጥር 1 ተመልክቷል፡፡

2.2.2 ስጋት፤

መንግስት ሊያገኘው የሚገባውን ገቢ ያሳጣዋል፡፡ በተጨማሪ መንግስት ለተጨማሪ ወጪ ሊዳረግ ይችላል፡፡

2.2.3 የማሻሻያ ሃሳብ ፤

ዩኒቨርሲቲው ማናቸውም የራሱ ተቀጣሪ ያልሆኑ መምህራን ከሚያገኙት ጥቅም ላይ ወይም ከሚከፈላቸው ክፍያ ላይ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ካላቸው 2 ፐርሰንት ከሌላቸው ደግሞ 30 ፐርሰንት ቆርጦ በማስቀረት ለሚመለከተው ግብር ሰብሳቢ መ/ቤት ገቢ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ በመሆኑም ለመንግስት መግባት ያለበት ቅደመ-ታክስ በኦዲት ናሙና ከታዩት በተጨማሪ ሌሎች እንዲዚሁ አይነት ተመሳሳይ ክፍያዎች ከሚመለከታቸው አካል በሙሉ ተሰብስቦ ዩኒቨርስቲው የከፈለውን ቀንሶ ተራፊውን ለሚመለከተው ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት ገቢ ሊደረግ ይገባል፡፡

2.2.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፤

ለመንግስት ገቢ የልተደረገ ቅደመ ታክስ በሚል አርዕስት ስር ኮሌጁ የግብር ክፍያ የመለያ ቁጥር ላላቀረቡ መምህራን ክፍያ ፈፅመዋል የተባለው በትክክል ያልታየ መሆኑን እየገልፅን፤ የተዘረዘሩትን መምህራኖች የግብር ክፍያ መለያ ቁጥር

/መታወቂያ/ ኮፒ አድርገን ከግኝቱ ጋር የላክን ስለሆነ ስለዚህ ኮሌጁ የግብር ከፍያ መለያ ቁጥር ሳይኖራቸው የከፈለው ክፍያም ሆነ ለሚመለከተው መስሪያ ቤት ገቢ ያላደረገ ክፍያ አለመኖሩን ተረድታችሁ ከግኝት እንዲነሳ በማክበር እንጠይቃለን ሲሉ ጠይቀዋል፡፡

2.2.5 <u>የኦዲተሩ አስተያየት</u>

የመምህራኖቹ የግብር ከፍያ መለያ ቁጥር ኮፒ ተደርጎ ተያይዟል የተባለው ከተሰጠው ምላሽ ጋር ያልተያያዘ ሲሆን በመውጫ ውይይቱ ወቅትም ያልቀረበ ስለመሆኑ የተማመንበት በመሆኑ ግኝቱ እንዳለ ይሆናል፡፡

2.3 <u>ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በመመሪያው በተቀመጠው የሪፖርት ይዘት መሰረት ሪፖርት ያልተደረገ የውስጥ ገቢ እና የፕሮጀክት ሂሳብ፤</u>

2.3.1 <u>ግኝት፤</u>

የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 10/1 የመንግስት የሂሳብ ሪፖርት ይዘት የገቢ፣ የወጪ፣ የገንዘብ ዝውውር፣ የተሰብሳቢ፣ የተከፋይ፣ የሂሳብ ማመዛዘኛ፣ የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ የሂሳብ ሪፖርት መቅረብ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጂ የሆስፒታሉ /ህይወት ፋና/ የውስጥ ገቢ ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ ፡

- በባንክ ሂሳብ ቁጥር 1000166210031 በባንክ መግለጫው መሰረት ሰኔ 30/2009 ዓ.ም ብር 6,545,352.58 የሆስፒታሉ የውስጥ የገቢ ሂሳብ ዘመናዊ በሆነና በቴክኖሎጂ የተደገፈ የሂሳብ አያያዝ ዘዴ (IBEX) ያልተመዘገበ ከመሆኑ በላይ በመንግስት የሂሳብ አያያዝና አወቃቀር /Charts of accounts/ ተመዝግቦ የሂሳብ ሪፖርቱ ይዘቱን ጠብቆ የማይዘጋጅና ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር የማይቀርብ መሆኑ፣

የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 9 ተራ ቁጥር 1 እና 2 መሰረት ማንኛውም የመንግስት መ/ቤት ከዓለም አቀፍ ድርጅቶችና ከውጭ አገር ለጋሽ መንግስታት የሚያገኘውን የብድርና የእርዳታ ገንዘብ፡ ከሚኒስትሩ በቻናል አንድ የገንዘብ ፍሰት የተላለፈውን፣ በመ/ቤቱ ባንክ ቀጥታ ከአበዳሪና እርዳታ ሰጪዎች የገባውን ሂሳብ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ መሰረት የተዘጋጁትን ቻርት ኦፍ አካውንትስ፣ ቫውቸር፣ መዝገቦችና የሪፖርት ማቅረቢያ ቅጾችን በመጠቀም ሂሳቡን መዝግቦ መያዝና ወርሃዊ፣ የሩብ አመትና አመታዊ ሪፖርት ከባንክ መግለጫው ጋር ማቅረብ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው ፡

- ከPCCSR & AJLA project በባንክ ሂሳብ ቁጥር 1000059217279 እስከ ሰኔ 30/2009 ድረስ ብር 5,199,433.26 ፣
- ከPRIME project በባንክ ሂሳብ ቁጥር 1000037197894 እስከ ሰኔ 30/2009 ድረስ ብር 480,128.25 ፣
- ከISSD Poject በባንክ ሂሳብ ቁጥር 1000037198726 እስከ ሰኔ 30/2009 ድረስ ብር 939,221.71 በድምሩ ብር 6,618,783.82 የእርዳታ የገቢ ሂሳብ ዘመናዊ በሆነና በቴክኖሎጂ የተደገፈ የሂሳብ አያያዝ ዘዴ (IBEX) ያልተመዘገበ እና የሂሳብ ሪፖርቱ ተዘጋጅቶ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር የማይቀርብ መሆኑ በኦዲት ወቅት ታውቋል፡፡

2.3.2 ስጋት፣

የውስጥ ገቢ እና የፕሮጀክት ሂሳብ ዘመናዊ በሆነ ቴክኖሎጂ ተደግፎ ካልተያዘ ከፍተኛ ጊዜና ጉልበት የሚፈጅ ከመሆኑ በተጨማሪ ለስህተት የሚዳርግና ስህተቱንም በአጭር ጊዜ ውስጥ ፈልጎ ለማግኘትም ሆነ ስህተትን ወዲያውኑ ለማስተካከል እንዲሁም የውስጥና የውጭ ኦዲተሮች የሂሳቡን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ከፍተኛ ጊዜና ገንዘብ ሊጠይቅ ይችላል፡፡ በተጨማሪም የሚቀርበው የውስጥ ገቢ ሪፖርት ታዓማኒነት የጎደለው እንዲሆን ያደርገዋል፡፡

2.3.3 የማሻሻያ ሃሳብ፣

የውስጥ ገቢ እና የፕሮጀክት ሂሳብ ልክ እንደ መደበኛ በጀት የሂሳብ ሪፖርት ይዘት መሰረት ለብቻው የሂሳብ እንቅስቃሴ ዘመናዊ በሆነ የሂሳብ አያያዝ ዘዴ በቴክኖሎጂ ተደግፎ መያዝ ስለሚኖርበት በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር የሂሳብ አያያዝ ዘዴ (IBEX) እንዲያዝ የስራ አመራሩ የእርምት እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም የውስጥ ገቢ ሂሳብ ሪፖርት ተዓማኒነት እንዲኖረው በመንግስት የሂሳብ አያያዝና አወቃቀር /Charts of accounts/ እየተመዘገበ በመመሪያው በተቀመጠው የሂሳብ ሪፖርት ይዘት መሰረት ተዘጋጅቶ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ሊቀርብ ይገባል፡፡

2.3.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

- የሆስፒታሉ የስራ አመራር ሆስፒታሉ በአሁኑ ጊዜ ወደ IBEX የተሸጋገረ ሲሆን በ2009 ዓ.ም የውስጥ ገቢ ሂሳብ እዛው በሐረር ካምፓስ ሂሳቡ እንዲያዝ በመደረጉና በስራው ማስጀመሪያ የIBEX ፕሮግራም ከገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ተጠይቆ እስኪመጣ ችግር የነበረ ቢሆንም በአሁኑ ጊዜ የተጀመረና እየተሰራ የሚገኝ መሆኑ፣

- የ2009 የሂሳብ ሪፖርቱም ዝርዝር በግኝቱ በተጠቀሰው መሰረት በIBEX ባይሆንም ሪፖርቱ በተሟላ መልኩ የተዘጋጀና በሐረር ካምፓስ የፋይናንስ አስተዳደር ተባባሪ ዳይሬክቶሬት ቢሮ እንደሚገኝ እየገለፅን፤ ባስፈለጋችሁ ጊዜ መጠየቅና ማየት የምትችሉ መሆኑን በትህትና እንጠይቃለን ለወደፊቱ ግን በኦዲቱ በተሰጠው አሰራር ብቻ ለመስራት ስራው መጀመሩን፤
  - የPRIME & PCCSR Project የአካውንቲንግ ሶፍትዌር Peachtree የተጠቀምንበት ዋና ምክንያት እርዳታ ሰጪ ድርጅቶቹ ሊሰራላቸው የፈለጉት በጀት አያያዝና አወቃቀር እንዲሰራ በማስገደዳቸው እና ፕሮጀክቶቹ የራሳቸውን Chart of Accounts በአማካሪ በማሰራት ማናቸውም ወጪዎች በበጀት እስትሪም አሰራር በአራት (4) በመከፋፈል IR1, IR2, IR3 & IR4 ከነዚህ ስር የተለያዩ ስራዎችን የተለያዩ የበጀት ወጪ አርዕስቶች የራሳቸው የተመደበ በጀት በመኖሩ እና በዚሁ ስር እንዲተዳደር በመፈለጋቸው የተነሳ እና በነዚሁ ፈንድ እስትሪም ስር በIBEX የቻርት ኦፍ አካውንቱን ማካተት ባለመቻሉ፤
  - የIBEX ሶፍትዌር ለዚህ ፕሮጀክት ደጋፊ ድርጅቶች ሪፖርት በሚፈልጉት መልኩ ዲዛይን ለማድረግ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ስለማይፈቅድና በተጨማሪ ሶፍትዌሩም በሽያጭ ከገበያ የማይገኝና በመንግስት መ/ቤቶች ለመንግስት ሂሳቦችና የመ/ት በጀት አስተዳደር ብቻ በሚያመች መልኩ ተብሎ የተሰራ በመሆኑ፤
  - ድጋፍ የሚያደርጉ የበነ አድራጊ ድርጅቶች /ሀገራት/ ሪፖርቱን በእነሱ ፍላጎት መልኩ ካልቀረበ የገንዘብ ድጋፍ የማያደርጉ በመሆኑ፤
  - የISSD Project በተመለከተ የIBEX አካውንቲንግ ሶፍትዌር መጠቀም ያልተቻለበት ምክንያት እርዳታ የሚሰጠው ድርጅት ሐረማያ ዩኒቨርሲቲን ጨምሮ ኢትዮጵያ ውስጥ ወደ አስር የሚሆኑ ፕሮጀክቶች ያሉት ሲሆን፤ ለሁሉም ፕሮጀክቶች ተመሳሳይና ወጥ የሆነ የፋይናንስ አሰራር ለመጠቀም ስለፈለገ ይህንን በማሰብ Peachtree Accounting ሙሉውን አሰራር እራሱ እርዳታውን የሰጠው ድርጅት በራሱ በሚያመቸው መልኩ በመቅረፅ በሁሉም ፕሮጀክቶች ኮምፒዩተር ላይ ጭነዋል፡፡ የሊጋሹ የድርጅቱ ዋና ዓላማ በየፕሮጀክቶቹ ላይ ያለውን የፋይናንስ Accounting System የተጫነበት ኮምፒዩተር ዋና መስሪያ ቤት ከሚገኘው ኮምፒዩተር (Server) ጋር በማገናኘት አሰራሩን በኔትዎርክ በማገናኘት ማናቸውንም የፋይናንስ ሪፖርቶች On line ማግኘትና ከሁሉም ፕሮጀክቶች የሚገኘውን ሪፖርት

በዚሁ ሶፍትዌር ኮንሰሊዴት በማድረግ ሪፖርቱን በቀላሉ ፕሮጀክቱ ለሚመለከታቸው አካላት በወቅቱ ለማቅረብ አስቦ ወደዚህ አሰራር መግባቱን፤

- IBEX ሶፍትዌር ፕሮግራም በየተፈለገው ፕሮጀክት በሁሉም መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ሊሰራበት ቢፈለግ ማግኘት ባለመቻሉ ምንያቱም የIBEX ሶፍትዌር በራሱ በገ/ኢ/ት/ሚ/ር የIBEX ባለሞያዎች በራሳቸው ለተፈቀደላቸው የመንግስት መስሪያ ቤቶች በአካል ቀርበው ሶፍትዌሩን የሚጭኑ እንጂ ሌሎች የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ከገበያው ገዝተው ለፈለጋቸው አገልግሎት ወደ ኮምፒዩተር ጭነው ሊጠቀሙበት የማይቻልና የማይሰጥ መሆኑ፤
- የIBEX ሶፍትዌር ተገኝቶ እንኳን ሶፍትዌሩ ቢጫን ለፌደራልና የክልል መንግስታት የሒሳብና የበጀት አሰራር ብቻ ተከትሎ የተዘጋጀ በመሆኑና ለሌሎች አገልግሎቶች በማያመች ማስተካከል የማይቻል በመሆኑ፡፡
- በተራ ቁጥር 1 ላይ በተጠቀሰው መሰረት ለጋሽ ድርጅቶች የISSD Project ሂሳብ በPeachtree የአካውንቲንግ ሶፍትዌር ብቻ እንዲሰራላቸው በመጠየቃቸው የተነሳ እና ለጋሾቹ በራሳቸው የአካውንቲንግ ሶፍትዌሩን ዲዛን አድርገው ለእያንዳንዱ ፕሮጀክት ጭነው ተግባራዊ በማድረጋቸው የተነሳ በመሆኑ እንጂ ሆነ ተብሎ ያልተፈፀመ መሆኑን ለስራ አመራሩ አስረድተው በቀጣይ ከገ/ኢ/ት/ር/ሚ/ር ደብዳቤ በመፃፍ መጠየቅ እንዳለብን ማስታወቃችንን፡
- ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች በነዚህ በግኝት በቀረቡት ፕሮጀክቶች ሂሳቦች በPeacthre Accounting System የተጠቀምን መሆኑን ተረድታችሁ ለወደፊቱ ግን የገ/ኢ/ት/ሚ/ር ለሁሉም ለጋሽ በጎ አድራጎት ድርጅቶች የሪፖርት ፍላጎት በሚያሟላ መልኩ በሚፈለግ ጊዜ ሁሉ ማቅረብ የሚችል ከሆነ ይህንኑ ተከትለን በሚቀርበው የIBEX ሶፍትዌር በመመዝገብ ለሚከተለው ሁሉ ሪፖርት የምናደርግ መሆኑን ተረድታችሁ ከሪፖርት እንዲነሳ እንጠይቃለን በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

2.3.5 የ<u>ኦዲተሩ አስተያየት</u>፣

የሆስፒታሉ የሂሳብ ሪፖርቱ ይዘት ከባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ በስተቀር የጥሬ ገንዘብ፣ የገቢ፣ የወጪ፣ የገንዘብ ዝውውር፣ የተሰብሳቢ፣ የተከፋይ፣ የሂሳብ ማመዛዘኛ ሪፖርት ተዘጋጅቶ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ያልቀረበ በመሆኑ በኦዲት ማሻሻያ ሃሳብ መሰረት እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

2.4 ከተለያዩ የእንስሳት እርባታዎች የተገኝ የውስጥ ገቢን በተመለከተ ፣

2.4.1 ግኝት ፣

የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ 650/2001 አንቀጽ 66 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 መሰረት ማንኛውም የመንግስት ተቋም በተቋሙ ፕሬዝዳንት ጥያቄና በቦርዱ ውሳኔ የገቢ ማስገኛ ድርጅት ሊያቋቁም እንደሚችል እና ድርጅቱ የራሱ ህጋዊ ሰውነት ያለው ሆኖ እንደማንኛውም የንግድ ድርጅት ህጉ የሚጠይቀውን ሁሉ በማሟላት መሥራት እንደሚገባቸው ይደነግጋል፡፡ ዩኒቨርሲቲው ምንም እንኳን በ2009 በጀት ዓመት ራሱን የቻለ የሰውነት መብት ያለው ኢንተርፕራይዝ ባያቋቁምም የራሳቸውን ገቢ በራሳቸው ወጪ መሸፈን የሚችሉ የተለያዩ ቢዝነስ ሴንተሮች ያሉት በመሆኑ የገቢ ማስገኛዎቹ ቅኝት በማድረግ እና ከኢንተርፕራይዝ ዳይሬክቶሬት በተሰጠን የ2008 እና 2009 በጀት ዓመት አራተኛ ሩብ ዓመት ሪፖርት መሰረት ኦዲት ሲደረግ፡

- በ2008 በጀት ዓመት ከዶሮ እርባታ በአጠቃላይ ከ12,560 ዶሮዎች ብር 1,336,187.50 ገቢ ሲገኝ በ2009 በጀት ዓመት ደግሞ በአጠቃላይ 19,510 ዶሮዎች ብር 870,962.50 ገቢ የተገኘ ሲሆን ከባለፈው በጀት ዓመት ጋር ሲነጻጸር በልዩነት ብር 465,225.00 ገቢው የቀነሰ ከመሆኑ በላይ ከዶሮ እርባታው ጋር በተያያዘ ተገቢውን የውስጥ ቁጥጥር ስርዓቱ ማለትም ቢን ካርዶች፣ የተለያዩ መዝገቦች በትክክል እየተመዘገቡ እና እየተረጋገጡ ከወጪ ቀሪው ምን ያህል እንደሆነ ወቅታዊ የሆነ ምዝገባ የሌለው መሆኑ ፣
- በ2008 በጀት ዓመት ከአሳማ እርባታ በአጠቃላይ ከ65 አሳማዎች ብር 158,350.00 ገቢ ሲገኝ በ2009 በጀት ዓመት ደግሞ በአጠቃላይ ከ108 አሳማዎች ብር 105,000.00 ገቢ የተገኘ ሲሆን ከባለፈው በጀት ዓመት ጋር ሲነጻጸር በልዩነት ብር 53,350.00 ገቢው የቀነሰ ከመሆኑ በላይ ከአሳማ እርባታው ጋር በተያያዘ 4 አሳማዎች የህይወት ታሪካቸው ማለትም ክብደታቸው፣ ከተወለዱ ምን ያህል ጊዜ እንደሆናቸው ሳይረጋገጥ የተገዙ መሆኑ፣ ክፍሉ የአሳማዎቹን የሽያጭ ዋጋ በመጨመር አሳማዎቹን የሚገዛቸው የጠፋ ከመሆኑ በላይ አሳማዎቹ ከመጠን በላይ ክብደት እየጨመሩ ለሽያጭ በማይቀርቡበት ሁኔታ ያሉ መሆናቸውና በክፍሉ ውስጣዊ አሰራር ተገቢውን የሆነ ውሳኔ ወይም እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፣
- በንብ እርባታ ላይ ምን ያህል የንብ መንጋ እና ቀፎ ያለ መሆኑን የሚገልጽ ምንም አይነት ምዝገባ የሌለ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ ለእርባታው ከሚወጣው የሰራተኛ፣ የመኖ እና የተለያዩ ወጪዎች አንጻር ሲታይ ለዚያውም በብዛታቸውም ቢሆን ብልጫ ያለው ሆኖ ሳለ በበጀት ዓመቱ

የተገኘው ገቢ ከባለፈው በጀት ዓመት ገቢ ጋር ሲነጻጸር ያነሰ እና ተገቢውን የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ያልተዘረጋለት መሆኑን በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችላል፡፡

2.4.2 <u>ስጋት፣</u>

ለቢዝነስ ሴንተሮቹ ከሚወጣው ወጪ አንጻር ተገበውን ገቢ የማይገኝ ከሆነና አስተማማኝ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ከሌለ ዩኒቨርሲተው ለተጨማሪ ወጪ ከመዳረጉ በላይ ለግለሰቦች መጠቀሚያ እንዲሆን መንገድ ይከፍታል፡፡

2.4.3 <u>የማሻሻያ ሃሳብ፣</u>

የስራ አመራሩ በቢዝነስ ሴንተሮቹ /በግብርና ልማት/ ያለውን የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት በመገምገም ከሚወጣው ወጪ አንጻር ተገቢውን ገቢ መገኘቱን እና አሰራሩ ለግለሰቦች መጠቀሚያ እንዳይሆን ጊዜ ሳይሰጠው አስፈላጊውን እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡ በተጨማሪም በቢዝነስ ሴንተሮች /በግብርና ልማት/ የሚከናወነውን አጠቃላይ ሂደት የሚገልጽ ወቅታዊ ምዘገባ እየተደረገ ከወጪ ቀሪ ባልተቆራረጠ እና ወጥነት ባለው ሁኔታ እየተረጋገጠ ሊመሳከር ይገባል፡፡

2.4.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

1. የዶሮ እርባታን በተመለከተ

- ❖ በ2008 በጀት ዓመት የቄብ ዶሮዎች ሽያጭ መንግስታዊ ያልሆነው ZOA ለሚባለው ድርጅት በልዩ ሁኔታ የተከናወነ ሲሆን በሚዳጋ ቶላ ወረዳ ለሚኖሩ አርብቶ አደሮች ገዝቶ ላከፋፈለው ቄብ ዶሮች ድርጅቱ ባስቀመጠልን መስፈርት መሰረት (በልዩ እንክበካቤ ማሳደግ፤ ለሶስት ወር መኖ አዘጋጅቶ በልዩ እንክብከካቤ ቦታው ድረስ ማጓጓዝና ሙያዊ ደጋፍ በመስጠቱ) ከአከባቢ ማህበራት ከምናቀርብላቸው የአንድ ቄብ ዶሮ ዋጋ 85 ብር በተለየ ዋጋ የአንድ ቄብ ዶሮ ዋጋ በብር 150.00 (መቶ ሐምሣ) 5000 ቄቦችን ለሽያጭ በማቅረብ ገቢው ሊያድግ መቻሉን፤
- ❖ በ2009 በጀት ዓመት መጨረሻ ላይ በእርባታ ክፍሉ የነበረው የዶሮ ቁጥር 19510 ሲሆን ይህንን የሚያሳየው ክፍሉ ከሽያጭ ይልቅ ተተኪ የእርባታ ዶሮዎች ማምረት ላይ ተኩረት ማድረጉንና በተጨማሪ ለ6 ወር ያህል የእንቁላላል ማስፈልፈያ ማሽን ተበላሽቶ በመቆየቱ (መለዋወጫ ሀገር ውስጥ ባለመገኘቱ ከውጭ ሀገር እስኪመጣልን ድረስ ጊዜ በመውሰዱ) እንደሁም ከተሰራ በኋላም ለእርባታው ተተኪ ዶሮዎች መያዝ ስለነበረበት ለ8 ወር ያህል ምንም አይነት የቄብ ዶሮች ሽያጭ ያልተካሄደ ሲሆን የተሸጡ ዶሮዎች በተለያየ እድሜ የተለያየ ዋጋ በመሆኑ በዚህ ምክንያት የ2009 ዓ.ም. ገቢ ሊቀንስ መቻሉን፤ ከእያንዳንዱ እንቁላል ጣይ ዶሮዎች የሚሰበሰበው እንቁላል ለእንቁላል ግምጃ ቤት ሰራተኛ መረካከቢያ ቅጽ

ያለ ሲሆን ይህ ግን በቂ አይደለም ለተባለው፡- በአሁኑ ጊዜ አዲስ የመረካከቢያ ቅጽ ተዘጋጅቶ እየተሰራበት የሚገኝ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

2. ከአሳማ እርባታ

❖ የእርባታ ክፍሉ ለሽያጭ ያደረሳቸው አሳማዎች የቅርብ አለቃ በፈጠረው የዋጋ ጭማሪ የአሰራር ክፍተት በተነሳ አሳማዎቹ ሳይሸጡ በመቅረታቸውና በአካባቢም የአሳማ ገበያ በመቀዛቀዙና ፍለጎትም በመቀነሱ ገቢው እንዲቀንስ ምክንያት መሆኑ፣

ከአሣማ እርባታ ጋር በተያያዘ አራት አሣማዎች የሕይወት ታሪካቸው ማለትም ክብደታቸው ከተወለዱ ምን ያህል ጊዜ እንደሆናቸው ሣይረጋገጥ የተገዙ ለሚለው ፡-

❖ በወቅቱ አሳማዎች የእርስበርስ መዋለድ ምክንያት ለሚመጣው ችግር /Inbreeding depression/ እንዳይፈጠር በዘር ግንዳቸው የማይቀራረቡ አሳማ ከሌላ ቦታ እዲገዙ የተደረገ ሲሆን ለግዥው የሄዱ ግለሰቦች በስህተት መረጃውን ይዘው ሳይመጡ በመቅረታቸው የተነሳ አሳማዎቹ መረጃው ቀርበው እስከሚረጋገጥ ለብቻ ተለይተው እንዲቆዩ ተደርገው ከሻጩ እርባታ መረጃው እንዲመጣ ሂደት ላይ ያለና ባለን በለሙያዎችም ከተለያዩ በሽታዎች ነፃ መሆናቸውን በማረጋገጥ ላይ የሚገኙ መሆኑ፣

ክፍሉ የአሣማዎቹን የሽያጭ ዋጋ በመጨመር አሣማዎቹን የሚገዛ የጠፉ ከመሆኑም በላይ አሣማዎቹ ከመጠን በላይ ክብደት እየጨመሩ ለሽያጭ በማይቀርቡበት ሁኔታ ላይ ያሉ በመሆናቸው እና በክፍሉ ውስጣዊ አሰራር ተገቢውን ውሳኔ ወይም እርምጃ አልተወሰደም ለሚለው፡-

❖ ቀደም ብሎ ከላይ እንደተገለፀው ይህንን የሆነበት ምክንያት በአከባቢም የአሳማ ገበያ በመቀዛቀዙና ገገርዎች ዋጋ ካልቀነሰ አንወሰድም በማለታችው ሲሆን፣ ለተፈጠረው ችግር መፍትሄ ለመስጠት ዩኒቨርሲቲው የገበያ ጥናት እያደረገ መሆኑንና ጎን ለጎን ገገር ድርጅቶች የመግዣ ዋጋቸው በማቅረብ በጨረታ እንዲሳተፉ ተጋብዘዋል፡፡ በማለት በላኩት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

3 **የወጪ ሂሳብ፣**

3.1. **ደመወዝና ተዛማጅ ወጪዎች፣**

3.1.1 **የክፍያ ተመን ሳይኖረው የተፈፀመ ክፍያ፣**

3.1.1.1 **ግኝት፣**

በዩኒቨርሲቲው ሴኔት ሌጂስሌሽን የአካዳሚክ ባለሙያዎች ግዴታዎች በሚለው ስር ተማሪዎችን ማማከር፣ ፈተና መፈተን፣ የማስተማሪያ መሳሪያ መከለስ እና የመሳሰሉትን ተግባራት ማከናወን እንዳለበት ተጠቅሷል። በተጨማሪም ጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ጥር

13/2003 በቁጥር ጠ80-አጠ52/02/13 በተጻፈ ደብዳቤ ከትምህርት ሚኒስቴር የቀረበለትን የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የመምህራን የተሻሻለ የትርፍ ሰዓት ክፍያ በተፈቀደው አግባብ በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል የወጣ የክፍያ ተመን ሳይኖር፡-

- በዋናው ግቢ ብር 1,995,903.72፣ በህክምና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ በቀን 28/07/09 ዓ.ም በሂሳብ ማዘዣ ቁጥር 741/09 ብር 102,000.00 እንዲሁም በቀን 25/02/09 ዓ.ም በሂሳብ ማዘዣ ቁጥር 176/09 ብር 286,000.00 በድምሩ ብር 388,000.00 በጠቅላላ ብር 2,383,903.72 የሆኖራሪየም ክፍያ የተከፈለ መሆኑ፣ ዝርዝር ሁኔታው ከታች በአባሪ ቁጥር 2 ተመልክቷል፡፡
- በዋናው ግቢ ብር 3,095,460.88 ከውስጥ ገቢ እንዲሁም ብር 346,664.59 ከመደበኛ በጀት እና በአካዳሚክ ምርምር ክላስተር ብር 51,786.56 በድምሩ ብር 3,493,912.03 ለማስተርነት ወይም ለዶክተርነት ዲግሪ በሚዘጋጅ የጥናት ምርምር ጹሑፍ / Thesis Dissertation Research Supervision / በተማሪዎች ልክ ለማስተርስ ተማሪዎች ብር 1,000.00 እና 2,000.00 ለረዳት እና ለዋና አማካሪዎች ፣ ለፒኤችዲ ተማሪዎች ብር 2,500.00 እና 5,000.00 ወ.ዘ.ተ ለረዳት እና ለዋና አማካሪዎች እንደቅድም ተከተላቸው የክፍያ ተመን ሳይኖር ክፍያው የተፈጸመ መሆኑ፣ ዝርዝር ሁኔታ ከታች በአባሪ ቁጥር 2.1 ተመልክቷል፡፡
- በዋናው ግቢ ብር 656,117.00 እንዲሁም በህክምና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ብር 604,983.41 በድምሩ ብር 1,261,100.41 ጥናታዊ ፅሁፍ ግምገማ ላይ ለተሳተፉት እና ላስተባበሩት ሰራተኞች፤ ተመራቂ ተማሪዎች ሥልጠና ለሰጡ እና የተማሪዎች የተግባር ፈተና ለፈተኑት እና ላስተበበሩት ሠራተኞች ሥራ ለሰሩበት በሚል ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፣ ዝርዝር ሁኔታ ከታች በአባሪ ቁጥር 2.2 ተመልክቷል፡፡

በአጠቃላይ በድምሩ ብር 7,138,516.16 ክፍያዎቹ በመንግስት ወይም በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል የወጣ የክፍያ ተመን ሳይኖር የተከፈሉ መሆኑን በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡

3.1.1.2 ስ<u>ጋት፣</u>

በመንግስት ወይም በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል የወጣ የክፍያ ተመን ሳይኖር ክፍያ መፈጸም ለገንዘብ ብክነት መከሰት ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡ በተጨማሪም ተጠያቂነት ያመጣል፡፡

3.1.1.3 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>፣

በመንግስት ወይም በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል የወጣ የክፍያ ተመን ሳይኖር ክፍያ መፈጸም አግባብ ባለመሆኑ ጉዳዩ ከሚመለከተው አካል ጋር በመነጋገር ስለሚከፈለው የክፍያ ተመን ጥናት ተደርጎ በሚገኘው ውጤት መሰረት መስፈርት ወይም መመዘኛ /Criteria/ ተዘጋጅቶ እንዲሁም የክፍያ ተመኑ ወይም መጠን በሚመለከተው መ/ቤት በማስፈቀድ ክፍያውን ሊፈፅም ይገባል፡፡

3.1.1.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

ለድርሳን ምርምር አማካሪዎች እና ለፈታኞች የሚከፈል ክፍያዎች አሰራር ዩኒቨርሲቲው የተከተለው ዝም ተብሎ ህግና ስርአት ና ገደብ የለሽ ተመን የለሽ በሆነ ሁኔታ ሳይሆን ከዚህ በታች በተዘረዘረ ሁኔታ ነው፡፡

1. የዳሰሳ ጥናት መባድረግ ስለ ክፍያ እና ስለ አሰራሩ በተመራማሪ መ/ራን የፅሁፍ ጥናት በማስደረግ የቀረበ መሆኑ፡፡
2. በሐገር ደረጃ ለዚህ ለድርሳን ምርምር አማካሪዎች እና ለፈታኞች የሚከፈል ክፍያዎች ዙሪያ የፀደቀ የመንግስት መመሪያ መኖሩን አጣርተን በየዩኒቨርሲቲው የተለያዩ የክፍያ ተመን እንጂ ወጥ የሆነ ተመን በሚመለከተው የመንግስት አካል የሌለ መሆኑ በማወቃችን፤
3. በሀገር ደረጃ መጥ የሆነ ተመን የሌለ መሆኑን ስንረዳ በዳሰሳ ጥናቱ በቀረበው ጥናታዊ ፅሁፍ መነሻ በማድረግ የሁሉንም ዩኒቨርሲቲዎች የክፍያ ተመን ተመልክተን አማራጭ የምንለውን መጠነኛ /ወጪ/ ለመንግስት ዝቅተኛ ወጪ የሚያስከትለውን መርጠን በዚሁ እንዲሰራ በስራ አመራር ቀርቦ ከፍተኛ ውይይት ተደርጎ በስራ አመራር ፀደቀ፡፡
4. በዚሁ በፀደቀ ውስጥ መመሪያ መሰረት እንዲሰራ አሰራር ዘርግተን አፈጻጸሙን በየሩብ አመቱ እየታየ ወደ ስራ የተገባ መሆኑ፤

የሐረማያ ዩኒቨርሲቲ ድህረ ምረቃ ፕሮግራም ዳይሬክቶሬት የሁለተኛ የሶስተኛ ድግሪ ተማሪዎችን በተለያዩ የሙያ መስኮች ሰልጣኞችን በመቀበል ለብዙ ዓመታት በማሰልጠን ላይ የሚገኝ አንጋፋ ተቋም ነው፡፡ እነዚህ ሠልጣኞች ብቁና ተወዳዳሪ ሆነው ለአገሪቱና ብሎም በዓለም ዙሪያ በሙያቸው እንዲያገለግሉ ለማስቻል የቲዎሪ ትምህርትና ድርሳን ምርምር ያካሂዳሉ፡፡ ይህ የድርሳን ምርመር

ጥናት ጥራቱን የጠበቀ እንዲሆን ለምርምር ትኩረት በመስጠትና በጀት በመመደብ በአማካሪዎቻቸው የቅርብ ክትትል እየተደረገ የምርምር ጥናት ያካሂዳሉ፡፡ በመጨረሻም ሰልጣኞች የምርምር ውጤታቸውን የውጭና በዩንቨርሲቲው የሚገኙ ፈታኞችና ማህበረሰብ በተገኙበት በይፋ የምርምር ሥራቸውን ያቀርባሉ፡፡

ለድርሳን መርምር የጽሁፍና የቃል ፈተና ግምገማ ለሚያካሂዱ ፈታኞች ወይም ባለሙያዎች በቂ ጊዜ ወስደው ከአንድ እስከ ሁለት ወር በማንበብና የማስተካከያ ሃሳብ በመስጠት፤-በዩንቨርሲቲው በመገኘት ተማሪዎችን የቃል ፈተና ይፈትናሉ፡፡ ውጤትም ይሰጣሉ፡

ዝርዝር አሰራሩን እንደሚከተለው በዝርዝር ቀርቧል፡-

ለፒኤች (PhD) ዲግሪ ተማሪዎች ሁለት አማካሪ ላላቸው ለዋናው አማካሪ ብር 6,000 ለተባባሪ አማካሪ ብር 4,000 ይከፈላል፡፡

ተማሪው ሶስት አማካሪዎች ቢኖሩት ለዋናው አማካሪ ብር 5,000 ለቀሪ ሁለት አማካሪዎች ለእንዳንዳቸው ብር 2,500 ይከፈላል፡፡

የአማካሪዎች ብዛት ከዚህ በላይ ሲጨመር ለእያንዳንዱ የሚደረግ ክፍያም በተመለከተው መሠረት እየቀነሰ ይሄዳል፡፡ በማንኛውም ሁኔታ ድምር ክፍያው ከ10,000 ብር በላይ አይሆንም፡፡

- ለሁለተኛ ድግሪ ተማሪዎች ለሁለት አማካሪዎች ብር 3,000 ይከፈላል፡፡ ይህም ክፍያ የአማካሪዎች ቁጥር ቢጨምርም እንኳ ጥቅል ክፍያው ከ3000 በላይ ሊሆን አይችልም፡፡
- ለፒኤች ዲግሪ ተማሪዎች ለሶስት ፈታኞች (ሊቀመንበር፤ ለውስጥና ለውጭ) ለእያንዳንዳቸው ብር 1,800 በድምሩ ብር 5,400 ሲከፈል ለሁለተኛ ድግሪ ተማሪዎች ሶስት ፈታኞች ለእንዳንዳቸው ብር 1,000 በድምር ብር 3,000 ይከፈላል፡፡ ይህ የአማካሪ ክፍያና የድርሳን ምርምር ፈተና የአገልግሎት ክፍያ ከሥራው አድካሚነትና ሥራው ከሚጠይቀው ሙያና ጊዜ አንጻር የሚደረግ መጠነኛ የማበረታቻ ክፍያ ነው፡፡ ይህ ክፍያ በተለያየ ጊዜያት በዩኒቨርሲቲው የተለያዩ አስተዳደር አካላት እየተገመገመ የድህረ ምረቃ ትምህርትን በጥራት ለማስኬድና አንጋፋ የዩንቨርሲቲ መምህራንን እንዲሁም በሌሎች መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ መሥሪያ ቤቶች ውስጥ የሚገኙ ምሁራንን ተሳትፎ ለመጨመር የተደረገ በጣም አነስተኛ የሆነ የማበረታቻ ክፍያ ነው፡፡ እንዲህም ሆኖ ክፍያው አገልግሎት የሚሰጡትን ምሁራንን እምብዛም የማያረካና የማያበረታታ በመሆኑ በየወቅቱ ቅሬታ እያስከተለ ይገኛል፡፡ በመሆኑም ይህን መሰል ሥራ ለማሰራት ችግር እያጋጠመን ይገኛል፡፡ ለወደፊቱ ችግሩን ለመቅረፍ ተጨማሪ የፈታኝ ክፍዎችን ማሻሻልና

የድርሳን ምርምር ጥራቱን ማስጠበቅ እንደሚያስፈልግ ይታመናል፡፡ ይህንንም ለማድረግ የመመመሪያ (guideline) ሥራ ዝግጅት ተጀምሯል፡፡ ስለዚህ ችግሩ ከትምህርት ጥራት አኳያ ሊታይና ማንኛውም ይህንን የተመለከተ ውሳኔ ሲሰጥ በጥንቃቄና ሃላፊነት በተሞላበት መልክ መሆን አለበት፡፡

- ለሶስተኛ እና ለሁለተኛ ደግሪ ለሚማሩ ተማሪዎች የድርሳን ምርምር በጀት በሚመለከት ለቀረበው አስተያየት የድርሳነ ምርምር በጀት መጠን ምርምሩ በሚፈለገው የጥናት ዓይነትና ጥልቀት የሚወሰን ሲሆን እንደስልጠናው ዓይነት ይለያያል፡፡ በዚሁም መሠረት በዩንቨርሲቲው የአስተዳደር ካውንስል መክሮ በተለየ ሙያ መስኩ የሚያስፈለገው በጀት ተወስኖ ወደ ሥራ የተገባበት አሠራር ነው፡፡ ለረጅም ዓመታትም ሲሰራበት ቆይቷል በ2009 ዓ/ም በዚሁ ላይ በመሞርከዝ በዩኒቨርሲቲው ደንብና መመሪያ በተዘጋጀው የLetter of Contract Agreement to Overload Assignments Related to Dissertation/Thesis Advising and Examining Activities በሚል ፎርማት ተሞልቶ ክፍያውም የተፈጸመ መሆኑን እየገለጽን የክፍውን ፎርማት 2 ገጽ አባሪ አያይዘን የላክን መሆናችንን እንገልጻለን፡፡

3.1.1.5 <u>የኦዲተሩ አስተያየት</u>፣

ዩኒቨርሲቲው ባወጣው ተመን መሰረት ለፒኤች (PhD) ዲግሪ ተማሪዎች ሁለት አማካሪ ላላቸው ለዋናው አማካሪ ብር 6,000.00 ለተባባሪ አማካሪ ብር 4,000 ይከፈላል፡፡ ተማሪው ሶስት አማካሪዎች ቢኖሩት ለዋናው አማካሪ ብር 5,000.00 ለቀሪ ሁለት አማካሪዎች ለእያንዳንዳቸው ብር 2,500 ይከፈላል፡፡ ይህን የክፍያ ተመን መንግስት ባጸደቀው የዋና እና ተባባሪ ፕሮፌሰር የመምህራን ትርፍ ሰዓት ክፍያ ተመን ብር 120 በማካፈል ክሬዲት ሃወር በማምጣት እንደገና ደግሞ በ120 ብር በማብዛት ዩኒቨርሲቲው ያወጣውን ተመን መልሶ የሚሰጥ ስለሆነ መመሪያን የተከተለ ነው ለማለት የማያስችል በመሆኑ በኦዲት ማሻሻያ ሃሳብ ላይ በተቀመጠው መሰረት እርምጃ ሊወደሰድ ይገባል፡፡ በተጨማሪም ተያይዟል የተባለው ፎርማት ተያይዞ አልቀረበም፡፡

3.1.2 <u>ዘላቂነት ባለው የስራ መደቦች ላይ በቀን ሰራተኝነት የተቀጠሩ ሰራተኞችን በተመለከተ</u>፣

3.1.2.1 <u>ግኝት</u> ፣

- የሲቪል ሰርቪስ ሚኒሰቴር በቁጥር ሲሰሚ30/ጠ18/22/459 በቀን 16/04/2005 ዓ.ም በኮንትራት /በጊዜያዊ ተቀጥረው የሚገኙ ሰራተኞችን ቋሚ ለማድረግ በወጣው አፈጻጸም መመሪያ መሰረት ዘላቂነት ባለውና በሲቪል ሰርቪስ ሚኒሰቴር በተመደበ የስራ መደብ ላይ በኮንትራት /በጊዜያዊነት ተቀጥረው የነበሩ ሠራተኞች ቅጥር እንዲቋረጥ ሆኖ በአስቸኳይ እንዲሰናበቱና ከየካቲት 30/2005

ዓ.ም በኋላ ቅጥር እንደማይፈፀም እንዲሁም ቅጥር ፈጽሞ የተገኘ የስራ ሃላፊ በህጉ መሰረት ተጠያቂ እንደሚደረግ ይገልጻል፡፡

- ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው በግብርና ልማት ማስተባበሪያ ክፍል የተለያዩ የእርባታ ክፍሎችን ደህንነት ለሚጠብቁ፣ የእንስሳት መኖ ለሚያዘጋጁ እና ለሚንከባከቡ ሰራተኞች በቀን ብር 20 እና 35 በማሰብ በድምሩ ብር 733,600.00 ፣
- በካምፓስ እና በስልጠና ማዕከል ስር ለሚገኙ ለአስተናጋጅ፣ ጽዳት፣ ስጋ ቤት አራጅ፣ ምግብ አብሳይ፣ እንጀራ ጋጋሪ፣ ስጋ ከታፊ፣ ቦንቦሊኖ ስራተኛ ወ.ዘ.ተ. ለመሳሰሉት ስራተኞች በቀን ብር 18፣ 21፣ 26፣ 40፣ 46 በማሰብ በድምሩ ብር 288,430.20፣

በጠቅላላ ድምሩ ብር 1,022,030.20 ቀጣይነት እና ዘላቂነት ባላቸው የስራ ዘርፎች ቋሚ የስራ መደብ እንዲሆኑ ጥናት በማድረግ መዋቅር ሚኒስቴር መ/ቤቱን በማስፈቀድ ክፍያውን መፈጸም ሲገባ በቀን ሰራተኝነት የተለያየ የክፍያ ተመን በማድረግ እንዲሁም ለቦታው የሚያስፈልገው የሰው ሃይል በጥናት ባልተደረሰበት ሁኔታ ከፍተኛ የሰው ሃይል በመጠቀም ክፍያው ወጪ ቆጣቢ አሰራርን እና መመሪያን ያልተከተለ መሆኑ በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡

ዝርዝር ሁኔታ ከታች በአባሪ ቁጥር 3 ተመልክቷል፡፡

3.1.2.2 <u>ስጋት</u> ፣

- መመሪያን መጣስ ተጠያቂነት ያመጣል፡፡
- ዘላቂነት ባላቸው የስራ መደቦች ሰራተኞችን በቀን ሰራተኝነት ቀጥሮ ማሰራት የሰው ሃይል በእቅድ እንዳይመራና በዜጎችና በመንግስት ላይ ከፍተኛ ኪሳራ ሊያስከትል ይችላል፡፡

3.1.2.3 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u> ፣

ማናቸውም በውስጥ ገቢ የሚከፈሉ ክፍያዎች የመንግስት ደንብና መመሪያ የተከተሉ መሆን አለባቸው። በመሆኑም ዘላቂነት ባለው የስራ ዘርፍ በቀን ሰራተኝነት ቀጥሮ ማሰራት አግባብነት የሌለው በመሆኑ ጊዜ ሳይሰጠው በስራ ዘርፎቹ ላይ ጥናት በማድረግ ቋሚ የስራ መደብ እንዲያገኙ የፐብሊክ ሰርቪስ የሰው ሃብት ልማት ሚኒስቴርን ጠይቆ በማሰፈቀድ ሲፈቀድ ክፍያው ሊፈጸም ይገባል። ለወደፊቱ እጅግ አስፈላጊ ለሆነና ለአጭር ጊዜ ብቻ የኮንተራት /ጊዜያዊ ቅጥር መፈጸም አስገዳጅ ሁኔታ ከተፈጠረ ጥያቄውን በቅድሚያ ሚኒስቴሩን በማሳወቅ ተቀባይነት ሲያገኝ ተፈጻሚ መደረግ ይኖርበታል፡፡

3.1.2.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

ከላይ በየሥራ ክፍሉ የተጠቀሱት የሥራ ዝርዝሮች ያልተጠኑና በሲቪል ሰርቪስ ያልተፈቀዱ ናቸው፡፡ ነገር ግን ለግቢው ማህበረሰብ አገልግሎት እጅግ አስፈላጊ በመሆናቸው እስኪጠኑና እስኪፈቀድ በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ግቢ አገልግሎት እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡ ለወደፊቱ መወሰድ ያለበት የማሻሻያ እርምጃ ላይ እንዳስቀመጣችሁት የስራ መዋቅሩ ተጠንቶ የሥራ መደቦች እንዲፈቀዱ ማድረግ ግዴታ በመሆኑ ባጭር ጊዜ ዘላቂነት ያላቸውን ሥራዎች ለይተን በማስፈቀድ ስራውን ለማስቀጠል ጥረት እንደሚደርጉ፣

እነዚህ ስራዎች ከተቋጡ የሚያስከትለው ችግር ማህረሰቡ አገልግሎት በማጣት ለእንግልት ከመዳረጉም በላይ የመማር ማስተማሩም ስራ ሊስተጓጎል ስለሚችል ጥናቱና ማስፈቀዱ እየተከናወነ አገልግሎቱን ማስቀጠል እንድንችል ዩኒቨርሲቲው ካለበት አካባቢና ካለው ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር እንዲታይ ቢደረግ፡

ለቀን ሰራተኞች እየተከፈለ ያለው የተለያየ መጠን ያለው ክፍያ በተመለከተ ታሳቢነቱ የአንድ ቋሚ የመንግስት ሠራተኛ ባለሙያ ያልሆነ ብር 961.00 እና ባለሙያ የሆነ ብር 1500.00 እና ከዚያ በላይ በመሆኑ ሥራው ሙያ የሚያስፈልገው እና ሙያ የማያስፈልገው መሆኑን በመለየት አሰሪውና ሠራተኛው በመስማማት የተፈጸመ ክፍያ መሆኑን እየገለፅን ለዚህ የተዘጋጀ ውልና ማስረጃ አለመኖሩም በቀን የሚሰራና ክፍያውም በቀን የሚታሰብ መሆኑን በላኩት ምላሽ ላይ ገልፀዋል፡፡

3.1.3 <u>የሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ እና አላግባብ ለጤና ሞያተኞች በተፈቀደው የተረኝነት አበል ስሌት መሰረት የተሰላ የትርፍ ሰዓት ክፍያ፣</u>

3.1.3.1 <u>ግኝት</u>

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ሰኔ 17 ቀን 2005 ዓ.ም. ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በፃፈው የደብዳቤ ቁጥር መ200-813/6 ለጤና ሞያተኞች በቀረበው ጥናት መሰረት በተራ ቁጥር ስድስት ላይ የፀደቀ ሲሆን የተረኝነት አበል ክፍያ የሚያገኙ የስራ ክፍሎች ዝርዝር የውስጥ ደዌ እስፔሻሊስት፣ የህፃናት ሃኪም፣ የማህፀን ስፔሻሊስት፣ የቀዶ ህክምና ስፔሻሊስት፣ የአጥንት ስፔሻሊስት፣ የአይን ስፔሻሊስት፣ የተቀናጀ ቀዶ ጥገና፣ አጠቃላይ ሃኪም፣ የሰመመን ባለሞያ፣ ነርስ ፕሮፌሽናል፣ አጠቃላይ ነርስ፣ ሚድዋይፈር፣ ፋርማሲስት፣ ድራጊስት፣ ላብራቶሬ ቴክኖሎጂስት፣ ላብራቶሪ ቴክኒሽያን እና ራዲዮግራፈር ሲሆኑ ከዚህ ሙያ ውጪ ያሉ ባለሙያዎች የተረኝነት አበል የማይገባቸው መሆኑን የተገለፀ ቢሆንም ዩኒቨርሲቲው በተለያዩ ቀናቶች የተረኝነት አበል ክፍያ ለማይገባቸው ክፍሎች በኦዲት ናሙና ከወደቁት ውስጥ በድምሩ ብር 248,497.22 በሆስፒታሉ ለሚሰሩ ለገ/ያዥ እና ለካርድ ክፍል ትርፍ ሰዓት ክፍያ ሲከፍል ከንጋቱ 12 ሰዓት እስከ ምሽቱ 4 ሰዓት

ለሚሰራ ትርፍ ሰዓት ለመደበኛው ስራው በሰዓት የሚከፈለው ደመወዝ በ1.25 ተባዝቶ፣ ከምሽቱ 4 ሰዓት እስከ ንጋቱ 12 ሰዓት ለሚሰራ ትርፍ ሰዓት ለመደበኛ ስራው በሰዓት የሚከፈለው ደመወዝ በ1.5 ተባዝቶ፣ በሳምንት የእረፍት ሰዓት ለሚሰራ ትርፍ ሰዓት ለመደበኛ ስራው በሰዓት የሚከፈለው ደመወዝ በ2 ተባዝቶ እንዲሁም በህዝብ በዓላት ቀን ለሚሰራ ትርፍ ሰዓት ለመደበኛ ስራው በሰዓት የሚከፈለው ደመወዝ በ2.5 ተባዝቶ ሂሳቡ ያልተሰላ እና በሰነዱ ላይ ሰራተኞቹ የሰሩበት ቀን ከላይ በቀረበው ዝርዝር መሰረት ሰዓቱ ተከፋፍሎ ሳይቀመጥ ለጤና ሞያተኞች በተፈቀደው የተረኝነት አበል ክፍያ ስሌት መሰረት በትርፍ ሰዓት የሰሩበት ቀን ብዛት ወደ ሰዓት ተቀይሮ በሰራተኞች የአንድ ሰዓት ደመወዝ በማብዛት ሂሳቡ የተሰላ በመሆኑ የየትርፍ ሰዓት የክፍያው ስሌቱን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ ዝርዝር ሁኔታው እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

.ቁ	ቀን	የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር	የደረሰኙ አይነት	የገንዘቡ መጠን	የተከፈለው ክፍል
1	30//09/16	288	PV	13,481.67	ገንዘብ ያዥና ካርድ ክፍል
2	24/04/17	1371	PV	25,898.21	››
3	24/11/16	582	PV	15,076.94	››
4	16/02/17	1069	PV	15,630.98	››
5	22/12/16	739	PV	16,572.28	››
6	24/10/16	408	PV	23,417.53	››
7	03/04/17	1271	PV	21,374.32	››
8	14/01/17	852	PV	16,208.85	››
9	30/06/17	7857	PV	24,104.45	››
10	05/07/17	1890	PV	24,746.13	››
11	06/06/17	1708	PV	24,707.62	››
12	22/05/17	1566	PV	27,278.24	››
ድምር				248,497.22	

3.1.3.2 <u>ስጋት፣</u>

ደንብና መመሪያን ያልተከተለ ክፍያ መፈጸም ለገንዘብ ብክነት ከመዳረጉም ባሻገር ተጠያቂነትን ያስከትላል፡፡

3.1.3.3 **የማሻሻያ ሃሳብ** ፣

ዩኒቨርሲቲው ማናቸውም የትርፍ ሰዓት ክፍያ ሲፈጽም በትርፍ ሰዓት ስሌት መሰረት መሆን ይኖርበታል፡፡ ለወድፊቱም የዚህ አይነት አሰራር እንዳይከሰት ጥብቅ ቁጥጥር እና ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡

3.1.3.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

የተረኝነት አባል ተብሎ የቀረበው ዝርዝር ለሆስፒታሉ የካርድ ክፍል ሠራተኞች ለሆስፒታሉ የዕለት ገንዘብ ሰብሳቢዎች እና በሆስፒታሉ ላይ ተመሳሳይ አገልግሎት ለሚሰጡ ሠራተኞ የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሚ/ርን አስፈቅደን የተከፈለ የትርፍ ሰዓት ክፍያ ነው፡፡ እንደሚታወቀው በሆስፒታሉ የካርድ ክፍል ሳይኖር የተወሰነም ቢሆን የአገልግሎት ክፍያ የሚቀበል ሠራተኞ ሳይኖር የህክምና አገልግሎት መሰጠት አይቻለንም፡፡ ሰለዚህ ከላይ በተጠቀሱት የሥራ መደቦች ላይ በነበረው የሠራተኛ እጥረት የትርፍ ሰዓት ተፍቅዶ እንድከፈል ተደርጓል፡፡ የተባለው ክፍያው ከDuty ጋር በአንድ ሰነድ የተሠራ ከመሆኑ ባላይ ክፍያው የተፈፀመው በሲቪል ሠርቪስ የትርፍ ሰዓት መመሪያ መሠረት መሆኑን በትህትና እንገልፃለን፡፡ በማለት በሰጡት ምላሽ ላይ ገልፀዋል፡፡

3.1.3.5 የኦዲተሩ አስተያየት

ትርፍ ሰዓት ክፍያ ሲከፍል ከንጋቱ 12 ሰዓት እስከ ምሽቱ 4 ሰዓት፣ ከምሽቱ 4 ሰዓት እስከ ንጋቱ 12፣ በሳምንት የዕረፍት ሰዓት እንዲሁም በህዝብ በዓላት ቀን ለሚሰራ ትርፍ ሰዓት ተከፋፍሎ ሰዓቱ ባልተቀመጠበት ሁኔታ በሲቪል ሠርቪስ የትርፍ ሰዓት መመሪያ መሠረት ተስርቷል ለማለት አያስችልም፡፡ በመሆኑም ስራ አመራሩ በኦዲት ማሻሻያ ሃሳብ ላይ በተቀመጠው መሰረት ለወደፊቱ የእርምት እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

3.1.4 የጥበቃ ሰራተኞች የትርፍ ሰዓት ክፍያ፣

3.1.4.1 ግኝት፣

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በቁጥር ገ/ኢ/ል/ሚ1/59/2/4 በቀን 17/09/02 ለፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ባስተላለፈው መመሪያ መሰረት ‹‹ስለ ትርፍ ሰዓት ክፍያ አፈጻጸም በማስመልከት ከኤጀንሲው ሰኔ 29 ቀን 2001 ዓ/ም በቁጥር መ30/ጠ13/36/8/3 የተላለፈው የአፈጻጸም መመሪያ ተግባራዊ ሳይደረግ እንደቆየ ይታወቃል፡፡ መመሪያው በተለይም በስራ ባህሪያቸው ምክንያት ከመደበኛ የስራ ሰዓት ውጪም ጭምር ለሚሰሩ የመንግስት መ/ቤቶች ጠቃሚ እንደሚሆን ስለታመነበት ያለአግባብ ብክነት እንዳይከሰት የተጠቃሚ መ/ቤቶችን የስራ ሁኔታዎች ግምት ውስጥ በማስገባት በኤጀንሲው በኩል በልዩ ሁኔታ እየተፈቀደ ስራ ላይ እንዲውል›› የተወሰነ መሆኑ መመሪያው ቢያመለክትም፤

- ዩኒቨርሲቲው በቁጥር ሐዩ/አስ/ተ/ጉ/ም/ና/11/880/09 በቀን 21/04/2009 የትርፍ ሰዓት ጠይቆ ከፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት ሚኒሰቴር በቁጥር ፐ/ስ/ሚ47/ጠ13/1/3 በቀን 07/05/2009 ከተፈቀደው በትርፍ ሰዓት ሊከፈላቸው

ከሚገባ የስራ መደብ ውጪ በዩኒቨርሲቲ ዋና ግቢ ውስጥ ለሚሰሩ ለጥበቃ ሰራተኞች በድምሩ ብር 3,839,682.93 አለአግባብ የትርፍ ሰዓት ክፍያ ተከፍሎ የተገኘ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል፡፡ ዝርዝር ሁኔታውም ቀጥሎ ተመልክቷል፡

ተ/ቁ	ቀን	ቫውቸር ቁጥር	የወጪው ምክንያት	የገንዘብ መጠን
1	25/3/17	3180	ትርፍ ሰዓት	485,668.50
2	24/11/16	3486	‹‹ ››	522,828.28
3	25/11/16	1951	‹‹ ››	284,951.67
4	21/12/16	2327	‹‹ ››	278,041.03
5	31/10/16	1260	‹‹ ››	321,919.15
6	24/11/16	404	‹‹ ››	266,908.06
7	19/8/16	2494	‹‹ ››	264875.13
8	3/7/17	1926	‹‹ ››	463,883.50
9	18/5/17	3881	‹‹ ››	477,007.64
10	19/06/17	4482	‹‹ ››	473,599.97
				3,839,682.93

3.1.4.2 ስጋት፣

በመንግስት ወይም በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል የወጣ የክፍያ መመሪያ ፍቃድ ሳይኖር ክፍያ መፈጸም ለገንዘብ ብክነት መከሰት ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡

3.1.4.3 የማሻሻያ ሃሳብ፣

ከፌዴራል ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት ሚኒስቴር ፍቃድ ውጪ ለአስተዳደር ሰራተኞች እየተከፈለ ያለው የትርፍ ሰዓት አበል በአስቸኳይ እንዲቆም እና አላግባብ የተከፈለውም ከሰራተኞቹ ተመላሽ እንዲደረግ፡፡ ለወደፊቱም ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት ዩኒቨርሲተው በመንግስት ደንብና መመሪያ መሰረት በሚመለከተው መ/ቤት በማስፈቀድ ክፍያውን ሊፈፅም ይገባል፡፡ በተጨማሪም የትርፍ ሰዓት ክፍያ መንግስት ላይ ከሚያስከትለው ከፍተኛ ወጪ አንጻር ክፍት የስራ መደቦችን በሰው ሃይል በማሟላት ስራዎች በፈረቃ ማሰራት ይገባል፡፡

3.1.4.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

በበጀት አመቱ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በሁሉም አካባቢ ያለመረጋጋትና የፀጥታ ችግር ተከስቶ የነበረ በመሆኑና ሰላማዊ የመማር ማስተማር ለማስቀጠል ሲባል በርብርብና የተለያዩ መንገዶችን በመጠቀም የታቀደውን የአመቱን የትምህርት ፕሮግራም በተቻለ

መጠን ለማስቀጠልና ለማጠናቀቅ በተቀመጠው እስኬጁል መሰረት ሰላማዊ የመማር ማስተማር ሂደትን ለማስቀጠል ሲባል በርካታ ርብርብ በማድረግ ማሰራትና የመንግስትን ውስን ሀብት በቅድሚያ ተሰጥቶት ካልተጠበቀ በጊዜው በነበረው ያለመረጋጋት ሙሉ ንብረቱን ሊያጣና ዳግም መልሶ ወደነበረበት መመለሱ ለሀገራችን ከፍተኛ ችግር ውስጥ የሚጥል በመሆኑ ዩኒቨርሲቲው የሀገር ሀብትን ከአደጋ ለመከላከል ሲባል ይሁንና በዚያን ወቅት በሚከሰቱ ችግሮች ውስጥ እራሳቸውን ለአደጋ አጋልጠው የመማር ማስተማር ሂደቱን ለማስቀጠል ሲሉ ከፍተኛ የሚባል መስዋዕትነት ከፍለው የተያዘውን ዕቅድ አስቀጥለው እንዲጠናቀቅ ላስቻሉ የጥበቃ አባላት ቢያንስ ሌላ ማድረግ ባይቻል በብርድና በጭለማ ለለፉበት በዝቅተኛ ደመወዛቸው መሰረት በትርፍ ለሰሩበት የትርፍ ሰአት ሊከፈል ተችሎአል፡፡ የሐገርን ውስን ሀብት ከጥፋት ለመከላከል የተሰራ ስራ መሆኑ በሌላ በኩል በሚመለከተው ሚ/ር መስሪያ ቤት ትርፍ ሰአቱ ተጠይቆ ያልተፈቀደ መሆኑ በዚህ የተነሳ የተከፈለ ክፍያ መሆኑን በመረዳት ከግኝት ይወጣ ዘንድ በትህትና እንጠይቃለን፡፡

3.2 <u>ለእቃና አገልግሎት ግዥ፣</u>

3.2.1 <u>አቅራቢዎች ሳይወዳደሩ በቀጥታ የተፈጸመ ግዥ</u>

3.2.1.1 <u>ግኝት፣</u>

ሰኔ/2002 በወጣው የፌዴራል መንግስት የግዥአፈጻጸም መመሪያ ክፍል 4 አንቀጽ 15.2-15.4 መሠረት በአዋጁና በመመሪያው በተፈቀደው ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር የመንግስት መ/ቤቶች ማናቸውንም ግዥ በግልፅ የጨረታ ዘዴ መፈጸም እንዳለባቸው፣ የመንግስት መ/ቤቶች ከግልፅ ጨረታ ውጭ በሌሎች የግዥ ዘዴዎች ግዥ መፈጸም የሚችሉት በአዋጁና በዚህ መመሪያ የተገለጹት ሁኔታዎች ሲሟሉ ብቻ እንደሆነ እንዲሁም ከግልጽ ጨረታ ውጭ በሌሎች የግዥ ዘዴዎች የሚጠቀም ማናቸውም የመንግሥት መ/ቤት በእነዚህ ዘዴዎች ለመጠቀም የመረጠበትን ምክንያትና ሁኔታዎች የሚገልጽ ሠነድ መያዝ እንዳለበት በሚያዘው መሰረት መፈጸማቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በዋናው ግቢ በድምሩ ብር 1,663,844.17 ዕቃ ከመመሪያው ውጪ ግዥው ያለውድድር የተፈጸመ መሆኑ በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

የሂሳቡ ዝርዝር ሁኔታ ከታች ከአባሪ 4 ይመልከቱ፡፡

3.2.1.2 <u>ስጋት፣</u>

ግዥ በመመሪውያ መሠረት ካልተፈፀመ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም፣ ይህም ቁጠባን፣ የአፈፃፀም ብቃትንና ውጤታማነትን ማስገኘቱን ማረጋገጥ አይቻልም፣ የመንግሥት ገንዘብም ለምዝበራ ሊጋለጥ ይችላል፡፡

3.2.1.3 **የማሻሻያ ሃሳብ፣**

ዩኒቨርሲቲው ማናቸውንም የእቃና አገልግሎት ግዥ ሲፈጽም በመንግስት የግዥ አዋጅ፣ ደንብ እና መመሪያ መሰረት ሊፈጽም ይገባል፡፡ በመሆኑም የዚህ አይነት አሰራር የመንግስት ጥቅም የሚያሳጣ አሰራር ስለሆነ ዩኒቨርሲቲው በቀጥታ ግዥ ሲፈጽም በልዩ ሁኔታ የሚመለከተውን አካል በመጠየቅ ሲፈቀድለት ግዥውን ሊፈጽም ይገባል፡፡

1.2.1.4 **የሥራ አመራሩ ምላሽ፣**

- ሐረማያ ዩኒቨርሲቲ የሞተር ሳይክል ግዥ ለመፈፀም ከመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ፍቃድ መገኘቱ ይታወሳል፡፡ በዚሁ መሰረት ግዥው በውስን ጨረታ የግዥ ዘዴ ለመፈፀም ሐረርና ድሬደዋ የሚገኙ ተወዳዳሪዎችን የጋበዝን ቢሆንም የቀረበው ዋጋ የገበያ ዋጋ ባለመሆኑ እና የተጋነነ በመሆኑ ምክንያት ጨረታው ተሰርዟል፡፡ የኦዲት ግኝት ላይ እንደተገለፀው በቀጥታ የግዥ ዘዴ ግዥውን ፈጽመን ሳይሆን ፕሬዝዳንት በማስፈቀድ በለቀማ የግዥ ዘዴ የተፈፀመ መሆኑ፤
- የተሽከርካሪ ጥገናን በተመለከተ ባለፉት ዓመታት ሐረማያ ዩኒቨርሲቲ ተሽከርካሪዎች በተለያዩ የግል ጋራዦች ቢጠገኑ፤
  - ሀ). ያሉት የግል ጋራዦች አቅማቸው ውስን መሆኑ
  - ለ). በቂ የተሽከርካሪ ማቆያ ቦታ የሌላቸው በመሆኑ
  - ሐ).ጥገና በሚያካሄዱበት ወቅት ለተሽከርካሪዎች የሚገጠሙባቸው መለዋወጫዎች ትክክለኛ ኦርጂናል ዕቃዎች ስለመሆናቸው ምንም ዓይነት ማረጋገጫ መንገድ የሌለን በመሆኑ፡

ከላይ የተጠቀሱትን ችግሮች ከግምት ውስጥ በማስገባት እጅግ ቢያንስ የተሽከርካሪዎቹ አስመጪ ጋራዦች ምንም እንኳን ለጥገና የሚጠይቁት ክፍያ በጣም ከፍተኛ ቢሆንም ቢያንስ የሚጠቀሙአቸውን የመለዋወጫ ዕቃዎች ኦርጂናሎች የሆኑ እና ከላይ የግል ጋራዥች እሏቸው ብለን ያልናቸው ችግሮች ስሌሉባቸው ሌሎች የግል ጋራዥን ላይ በተደጋጋሚ ጊዜ ያደረግናቸው ሙከራዎች ጋራዦቹ

- ሁሉን አቀፍ በቂ ባለሙያ የሌላቸው በመሆኑ፤
- በቂ የመኪና ማቆሚያ ቦታ የሌላቸው በመሆኑ፤
- የኢንሹራንስ ሽፋን የሌላቸው በመሆኑ እና

የግዥ አፋፃፀም መመሪያ በአንቀፅ 25 ንዑስ አንቀፅ 4 እና 5 እንደተደነገገው ማለት የመንግስት መ/ቤቱ ለሚጠቀምበት ዕቃ የሚያስፈልገው መለዋወጫ የሚገኘው ቀደም ሲል ዕቃውን ከሸጠው አቅራቢ ብቻ ሲሆንና ግዥው ከሌላ አቅራቢ እንዲፈፀም ቢደረግ የሚገዛው ዕቃ ወይም አገልግሎት መ/ቤቱ ከሚጠቀምበት መሣሪያ ወይም አገልግሎት ጋር ተጣጥሞ የማይሄድ መሆኑ በባለሙያ ሲረጋገጥ ከአስመጪው መፈፃም እንደሚችል በሚፈቀድው መመሪያ መሠረት እና ከአስመጪ ኩባንያዎች ውጪ የሚፈጸሙ የተሸከርካሪ ጥገናዎች ላይ እምነት መጠል (ኃላፊነት መውሰድ) ስለከበደን ሁሉንም ተሽከርካራዎችን በአስመጪ ድርጅቶች ስናስጠግን ቆይተናል፡፡ ነገር ግን በቅርቡ ከኢትዮጰያ ፌድራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፓብሊክ የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በደረሰን መመሪያ መሠረት ከ2010 በጀት ዓመት ጀምረን የተሽከርካሪዎችን ጥገና የመንግስት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ በሚፈቅደው መሠረት የመወዳደሪያ መስፈርት እና የጋረዥዎች ደረጃ ከመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በመጠየቅ እና ብሄራዊ ግልፅ ጨረታ በማውጣት እና ተወዳዳሪዎችን በተፈላጊ መስፈርቶች መሠረት በመገምገም አሸናፊ ሆኖ በሚመረጠው ድርጅት (ጋራዥ) ተሽከርካሪዎቻችን ለማስጠገን ከጨረታ ሰነድ ዝግጅት ጀምሮ በሂደት ላይ የምንገኝ በመሆኑ ሁኔታው በቅርቡ ይስተካከላል ብለን የምናምን መሆናችንን እንገልፃለን በማለት በላኩት ምላሽ ላይ ገልፀዋል፡፡

3.2.1.5 <u>የኦዲተሩ አስተያየት</u> ፣

የሞተር ሳይክል ግዥው በለቀማ የተገዛ ነው ቢባልም ግዥው በራሱ የተፈጸመው ግዥ መፈጸም በማይቻልበት ጊዜ ሰኔ ላይ ከመሆኑ በላይ ከአንድ አቅራቢ (ማንአለብሽ አስመጪ ድርጅት) የተፈጸመ እና በገበያ ላይ ሊገኝ የሚችልና በቂ አቅራቢዎች ሊገኙበት የሚችል አቅርቦት በመሆኑ ግዥው በውድድር ሊፈጸም ይገባ ነበር፡፡እንዲሁም የተሽከርካሪ ጥገናን በተመለከተ በትላልቅ የተሽከርካሪ አስመጪ ኩባንያዎች በቀጥታ ስምምነት ጥገና በማድረግ የሚወጣውን ወጪ ለመቀነስ እንደማንኛውም የግዥ አገልግሎት በጨረታ ሊፈጸም ይገባል፡፡

3.2.2. <u>በጀት ዓመቱን ያልጠበቀ ሂሳብ</u>፣

3.2.2.1 <u>ግኝት</u>፣

የፌደራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የመደበኛና ካፒታል የስራ ማስከጃ ወጪዎች ሲፈጸም ወጪው ለሚደረግበት ተግባር በበጀት ዓመቱ የተያዘ ወይም ወጪውን ለመሸፈን ቀሪ በጀት መኖሩንና ወጪው በመስሪያ ቤቱ ዕቅድ ወስጥ የተያዘና በጥሬ ገንዘብ ፍላጎት ላይ የተካተተ መሆኑ ሳይረጋገጥ ወጪ መፈፀም እንደማይገባ መመሪያው ይገልፃል፡፡ በዚህም መሠረት

በዩኒቨርሲቲው የሚፈፀሙ ክፍያዎች መመሪያውን የተከተሉ ለመሆኑ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በዩኒቨርሲቲው ለተፈፀሙ የዕቃ እና የአገልግሎት ግዥዎች፣

በዋናው ግቢ ለ2008 በጀት ዓመት ለተፈጸመ ግዥ የሰራተኞች ደንብ ልብስ እና የመጸሃፍት ግዥ በበጀት እጥረት ምክንያት ሳይከፈል የቀረ በማለት በ2009 በጀት ዓመት በድምር ብር 1,052,112.89 ተከፍሎና ተመዝግቦ ተገኝቷል።

የሂሳቡ ዝርዝር ሁኔታ እንደሚከተለው ቀርቧል።

ተ.ቁ	ቀን	የተከፈለው ምክንያት	ቫውቸር ቁጥር	የተከፈለው ድርጅት	የእቃው ገቢ ደረሰኝ ሞዴል 19	እቃው ገቢ የሆነበት ቀን	የገንዘብ መጠን
1	15/7/16	የሰራተኞች ደንብ ልብስ	43	ቶውፊቅ አብዱሳ	757002	23/10/08	260,419.64
2	31/10/16	የመጽሃፍት ግዥ	1192	ሪሊያብል ድርጅት	757021	30/10/08	53,035.50
					757022	30/10/08	110,136
					757023	30/10/08	134,987.25
					757024	30/10/08	54,597.50
					757026	30/10/08	35,458.75
					757027	30/10/08	45,816.25
					757028	30/10/08	34,856.25
					757051	30/10/08	54,059.75
					757052	30/10/08	59,569.50
					757053	30/10/08	81,196.50
						ጠቅላላ ድምር	1,052,112.89

3.2.2.2 **ስጋት፣**

ዩኒቨርሲቲው የዕቃ ወይም የአገልግሎት ግዥ በፈፀመበት እና አቅርቦቱን ባገኘበት በጀት ዓመት ሂሳቡ በወጪ ባለመመዝገቡ የበጀት አጠቃቀሙን የተዛባ ያደርገዋል፡፡

3.2.2.3 **የማሻሻያ ሃሳብ ፣**

በ2009 በጀት ዓመት በዕቅድ ለተያዙ ስራዎች ማከናወኛ ከተፈቀደለት በጀት የቀድሞውን በጀት ዓመት ክፍያ መፈጸሙ ተቋሙ የበጀት ህጉን ተከትሎ

አለማከናወኑን ያመለክታል፡፡ በመሆኑም ክፍያዎች በወቅቱ እንዲከፈሉ እና ተገቢው የበጀት አጠቃቀም ሥርዓት ተግባራዊ እንዲደረግ ጥብቅ ቁጥጥርና ክትትል ሊደረግ ይገባል ፡፡

3.2.2.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>፤

በዚሁ መመሪያ አንቀጽ 14 ተራ ቁጥር 1 (አንድ) እና 2 (ሁለት) በበጀት አመቱ የተያዘ በጀት ወይንም ወጪውን ለመሸፈን ቀሪ በጀት መኖሩ ከተረጋገጠ በሚለው ስር ባለው ሀረግ መሰረት በ2009 የበጀት አመት ለሰራተኞች የደንብ ልብስ የበጀት ዝውውር የገ/ኢ/ል/ሚር ጠይቀን ተፈቅዶልን በዚሁ ግዜውን ለመፈፀም በመመሪያው የተቀመጠውን ቅድመ ሁኔታ ቀሪ በጀት መኖሩን የበጀት ሽግሽግ (ዝውውር) በማድረግ በማረጋገጥና በጥሬ ገንዘብ ውስጥ አካተን ጠይቀን በማስመጣት የተፈãመ መሆኑ የመéሀፍት ግዜን በተመለከተ በ 2009 የበጀት ዝግጅት ወቅት ባለፈው አመት ታቅዶ ያልተገዛውን በታሳቢነት በመያዝ በቂ በጀት የተፈቀደለትና የጥገንዘብ እቅድ ውስጥ አካተን ጠይቀን በማምጣት የተከፈለ መሆኑን ተረድታችሁ ከግኝቱ እንዲነሳ እየጠየቅን የበጀት ዝውውርና ሽግሽግ የተደረገበትን መረጃ ኮፒ አያይዘን አቅርበናል፡፡

3.2.2.5 <u>የኦዲተሩ አስተያየት</u> ፤

በበጀት ዓመቱ ውስጥ ለተገዙ እና ለገቡ እቃዎቸ ክፍያው በበጀት ዓመቱ ካልተከናወነ በቀጣይ በጀት ዓመት በበጀት አጠቃቀም ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያመጣል፡፡ በመሆኑም ስራ አመራሩ በኦዲት ማሻሻያ ሃሳብ ላይ በተቀመጠው መሰረት ለወደፊቱ የእርምት እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡ እንዲሁም የበጀት ዝውውር የተጠየቀበትና የተፈቀደበት ማስረጃ ኮፒ ተደርጎ ተያይዟል የተባለው ያልተያያዘ መሆኑ ታውቋል፡፡

3.3 <u>ውሎ አበል</u> ፤

3.3.1 <u>አለአግባብ የተከፈለ ውሎ አበል ክፍያ</u>፤

3.3.1.1 <u>ግኝት</u> ፤

የውሎ አበል በኢ.ፌ.ድ.ሪ ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር በ29/10/2004 በቁጥር ሲ.ሰ.ሚ.30/ጠ13/40/883 ስለመንግስት ሰራተኞች የአገር ውስጥ የቀን የውሎ አበል አከፋፈል በወጣ መመሪያ መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- በዋናው ግቢ ብር 408,718.00፣ በአካዳሚክ ምርምር ክላስተር ብር 225,170.52 እና በእንስሳት ህክምና ኮሌጅ ብር 40,850.00 ብር በድምሩ ብር 674,738.52 የተማሪዎች ምርቃ በዓል የጥበቃ ሠራተኞች ከመደበኛ ስራቸው ውጪ የጸጥታ ችግር የአስተዳደር ስራን በማስተባበር ለሰሩበት፣ ለማስተርስ ድርሳን አስፈፃሚዎች

ለአስተባበሩት፣ በተለያዩ የስብሰባ ጊዜ ለአስተባበሩበት፣ በትርፍ ሰዓት ለሰሩ በሚል ሰራተኞቹ ለስራ ጉዳይ ከሚሰሩበት ቦታ ወደ ሌላ ባልሄዱበት ሁኔታ አለአግባብ በውሎ አበል ተመን መሰረት ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል።

ዝርዝር ሁኔታ ከታች በአባሪ ቁጥር 5 ቀርቧል፡፡

3.3.1.2 **ስጋት፣**

ደንብና መመሪያን ያልተከተለ ክፍያ መፈጸም ለገንዘብ ብክነት ከመዳረጉም ባሻገር ተጠያቂነትን ያስከትላል፡፡

3.3.1.3 **የማሻሻያ ሃሳብ ፣**

የቀን የውሎ አበል ክፍያ ሊፈጸም የሚችለው ሰራተኛው ከሚሰራበት መ/ቤት ወደ ሌላ ቦታ በሚሄድበት ወቅት ለቁርስ፣ ለምሳ፣ ለእራት እና ለአልጋ መንግስት ባወጣው ተመን መሰረት በመሆኑ አለአግባብ የተከፈለው ክፍያ መመሪያን የጣሰ ከመሆኑ ባሻገር መንግስትን ለተጨማሪ ወጪ የሚዳርግ በመሆኑ ማናቸውም ክፍያ በሚፈጸምበት ወቅት መመሪያን የተከተለ እንዲሆን ጥብቅ ቁጥጥርና ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡ በተጨማሪም ሰራተኞቹ በትርፍ ሰዓት የሰሩት ስራ ከሆነ መንግስት በፈቀደው የትርፍ ሰዓት ተመን መሰረት ክፍያው ሊፈጸም ይገባል፡፡

3.3.1.4 **የሥራ አመራሩ ምላሽ**

- ከሥራው ባህሪና ብዛት አኳያ ሥራዎቹ ከመደበኛ ሰዓት ውጪ እና ምሽት ጊዜ፣ እሁድና ቅዳሜን ጨምሮ ለረጅም ጊዜያት በእረፍት ጊዜ ይከናወናሉ፡፡ በሥራውም ፀሐፊዎች፣ የቴክኒክ ረዳቶች፣ ረዳት ምሩቃን፣ የትምህርት ክፍል ኃላፊዎች፣ የድህረ-ምረቃ ክፍል ሠራተኞች፣ የሬጅስትራር ሠራተኞች፣ የጥበቃ አባላት፣ የትራንስፖርት ክፍልሠራተኞች፣ የፋይናንስና ግዥ ሠራተኞች፣ የስልጠናማዕከል ሠራተኞችና ሌሎች እንደየሁኔታው ይሳተፋሉ፡፡ በእነዚህ ሠራተኞች በጎ ፈቃድና ከፍተኛየሥራ ሞራል የተነሣ በየወቅቱ የምናካሂደው የድርሳነ-ምርምር ፈተና በተሳካና ከስህተት በፀዳ መልኩ ሲካሄድ ቆይቷል፡፡እንግዲህ ይህ ሥራ የሚከናወነው በአብዛኛው በትርፍ ሰዓት በመሆኑ በሥራው የተሳተፉትን የዩኒቨርስቲውን ሠራተኞች እንደሚሳተፉበት የሥራ ብዛትና ክብደት የማበረታቻ ክፍያ ስንከፍል ቆይተናል፡፡ የድህረ-ምረቃ ፕሮግራም ክፍያው ሠራተኞች ላባከኑት የትርፍ ሰዓት ማካካሻ እንደሆነ ያምናል፡፡ ክፍያውን የሚያገኙ ሠራተኞች ቁጥርየሚፈተኑ ተማሪዎች ቁጥርና ተማሪዎችን ለፈተና ባቀረቡ ፕሮግራሞች ቁጥር የሚወሰን ነው፡፡ በመሆኑም የተማሪ ቁጥርና የትምህርት ፕሮግራሞች በመጨመራቸው የተከፋይ ቁጥርም ጨምሯል፡፡ የድህረ-ምረቃ ድርሳናት ፈተና ዝግጅት እጅግ ጊዜ የሚፈልግና የተማሪዎችን የአካዳሚክ መረጃ በጥንቃቄና በተለያዩ ደረጃዎች በጥራት ማዘጋጀትን ይጠይቃል፡፡ ከዚህም ባሻገር በርካታ እንግዶች

ከተለያዩ የሀገሪቷ ክፍሎች እና ውጪ ሃገር ስለሚመጡ የምርምር ድርሳናትን የማዘጋጀት፣ የመበተን፣ ለእንግዶች የትራንስፖርት ዝግጅትና የመስተንግዶ ማከናወን እጅግ አድካሚና ከሥራ ሰዓታትና ቀናት ውጪ ጭምር የሚሰሩ ሥራዎች ናቸው፡፡ በዚህ ሥራ የሚሳተፉ የዩኒቨርስቲው ሠራተኞችም ያለመሰልቸት ሥራውን በብቃት ያከናውናሉ፡፡ በዚህም ምክንያት ሥራው ያለምንም እንከን እና መፋለስ በጥሩ ሁኔታ ይካሄዳሉ፡፡የተማሪዎችም የትምህርት ማስረጃዎች (በፈተና ወቅቱ የሚዘጋጁ) ያለመዝረክረክ እና የጎላ ስህተት ሳይኖር በጥራት ይዘጋጃሉ፡፡ በመሆኑም ከላይ በተገለፁት ሁኔታዎች የሚፈፀሙ ስለሆነ ክፍያዎች ይከፈላሉ በማለት ገልፀዋል፡፡

3.3.1.5 <u>የኦዲተሩ አስተያየት</u> ፣

ሰራተኞቹ ከመደበኛ የስራ ሰዓት ውጪ ለሰሩበት በሚል በውሎ አበል ተመን መሰረት ክፍያ መፈጸም አግባብነት የለውም፡፡ በመሆኑም ስራ አመራሩ በኦዲት ማሻሻያ ሃሳብ በተቀመጠው መሰረት እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

3.4 <u>የግንባታ ሂሳብ</u> ፣

3.4.2 <u>በወቅቱ ተመላሽ ያልተደረገ የግንባታ የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ፣</u>

3.4.2.1 <u>ግኝት፣</u>

የህንጻ ተቋራጮች እና ዩኒቨርሲቲው በገቡት የውል ስምምነት መሰረት ግንባታው 80% ሲሆነው ህንጻ ተቋራጮቹ የወሰዱትን ቅድሚያ ክፍያ ሙሉ ለሙሉ ተመላሽ ማድረግ እንዳለባቸው ይገልጻል፡፡ በዚሁ መሰረት በግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት በተሰጠን የግንባታዎች ያሉበት ደረጃ መረጃ መሰረት ኦዲት ሲደረግ፡ ደመራ ኢንጅነሪንግ ኮንስትራክሽን የተማሪዎች ማደሪያ ህንጻዎች ግንባታ ተራቋጩ ስራውን 100% አጠናቆ ርክክብ ተፈጽሞ ተማሪዎች እየኖሩበት ሳለ በተቀጽላ ሌጀር ኮድ 0011 ብር 1,293,000.75 የግንባታ ቅድመ ክፍያ በውሉ መሰረት ተመላሽ ያልተደረገ እና በተሰብሳቢ ሂሳብ ወይም በ4251/ በግንባታ ቅደመያ ክፍያ/ ሂሳብ መደብ የሚታይ መሆኑን በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡

3.4.2.2 <u>ስጋት፣</u>

በግንባታዎቹ ሥራ መጓተት ለሌላ የልማት ሥራ ሊውል የሚችለውን ከፍተኛ መጠን ያለው የቅድሚያ ክፍያ በተቋራጮቹ እጅ እንዲቆዩ እና ለሌላ ግንባታ እንዲያውሉት ዕድል ይሰጣል፡፡

3.4.2.3 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u> ፣

በውሉ በተቀመጠው መሰረት የግንባታው ደረጃ 80% ሲሆን ተቋራጩ የወሰደውን ቅድሚያ ክፍያ ሙሉ ለሙሉ መመለስ አለበት ፡፡ በመሆኑም አለአግባብ በህንጻ

ተቋራጩ፣ ስም በተከፈተው ተቀጽላ ሌጀር ላይ የሚታየው ቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ ተጣርቶ ከድርጅቱ የሚፈለገው ገንዘብ ጊዜ ሳይሰጠው ተመላሽ ሊደረግ ይገባል፡፡

3.4.2.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

ዩኒቨርሲቲው በአብዛኛው ውል የተቋረጠባቸው ፕሮጀክቶች ላይ በመንግስት ግዢ እና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ሪፖርት ተደርጎ አብዛኛው ውሳኔ አግኝቶ የተቀሩት ውሳኔ በመጠባበቅ ላይ ይገኛል፡፡ ህጋዊ እርምጃ ለመሄድ የህግ ክፍሉ የውል ማስቶርጎም እና የክስ ጭብጥ በማዘጋጀት ሂደት ላይ ይገኛል፡፡ ሥራቸውን 100 % አጠናቀው የቅድመ ክፍያ ያለባቸው በሌላ በኩል በተከፋይ የተያዘ ሂሳብ ያላቸው ስለሆኑ ሌሎቹንም በማካተት በ 2010 ማጣራት በማድረግ በአፋጣኝ ቀጣይ እርምጃ የሚወሰድ መሆኑን እያሳወቅን ለማጠቃለል ዩኒቨርሲቲው በአብዛኛው ውል የተቋረጠባቸው ፕሮጀክቶች ላይ በመንግስት ግዢ እና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ሪፖርት ተደርጎ አብዛኛው ውሳኔ አግኝቶ የተቀሩት ውሳኔ በመጠባበቅ ላይ ይገኛል፡፡ በማለት በላኩት ምላሽ ላይ ገልፀዋል፡፡

3.4.3 በንብረት ገቢ ማድረጊያ ደረሰኝ /ሞ-19/ ያልተመዘገቡ የተጠናቀቁ ጊዜያዊ እና የመጨረሻ ርክክብ የተደረገባቸው ግንባታዎችን በተመለከተ፣

3.4.3.1 ግኝት ፣

የፌዴራል መንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003ዓ.ም አንቀጽ 7/2 ፊደል ሀ የመንግስት መስሪያ ቤቶች ያከናወኑዋቸውን የግንባታ ስራዎች እንደ ቋሚ ንብረቶች በተለየ መዝገብ መመዝገብ እንዳለባቸው ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው በድምሩ ብር 906,037,824.63 የሚያወጡ የተለያዩ የተጠናቀቁ ጊዜያዊ እና የመጨረሻ ርክክብ የተደረገባቸው ግንባታዎች ዩኒቨርሲቲው ንብረትነት ለመሆናቸው በሚረጋገጥበት ሁኔታ በንብረት ገቢ ማድረጊያ ደረሰኝ /ሞ-19/ በተጨማሪም በቋሚ ንብረት መመዝገቢያ ካርድ / Fixed Asset Registration Card-FAR/ እና የተጠቃሚዎች እጅ ላይ የሚገኙ ቋሚ ንብረቶች መቆጣጠሪያ ካርድ/Fixed Asset with user Control Card -UC/ ያልተመዘገቡና በተጠናቀቁ ግንባታዎች ላይ የዚህ አይነት አሰራር በዩኒቨርሲቲው ውስጥ እየተከናወነ አለመሆኑን በኦዲት ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ የሂሳቡ ዝርዝር ሁኔታ እንደሚከተለው ቀርቧል፡

ተ.ቁ	የሚከናወነው የግንባታ	ግንባታው የተከናወነበት	ፕሮጀክቱን የሚያከናውነው ድርጅት	የግንባታው ጠቅላላ ዋጋ
1	የማስፋፊያ ስራ ዲ እና ኢ	ዋናው ግቢ	ኤ ደብሊው ሃኪም ኮንስትራክሽን	22,228,132.82
2	የኮምፕሌክስ ህንጻ ፊኒሽንግ ስራ	‹‹ ››	ሪዝ እንጂነሪንግና ኮንስትራክሽን	4,943,624.87
3	የተማሪዎች መኖሪያ ህንጻ	ጭሮ ካማፓስ	በረካ ኮንስትራክሽን	12,637,631.24
4	የተማሪዎች መኖሪያና ካፍቴሪያ ህንጻ	ዋና ግቢ	አፍሮ ጽዮን ኮንስትራክሽን	267,932,349.21
5	የወርክ ሾፕ ግንባታ	‹‹ ››.	ዛምራ ኮንስትራክሽን	65,535,462.33
6	የስፖርት አካዳሚ ግንባታ	‹‹ ››	አፍሮ ጽዮን ኮንስትራክሽን	532,760,624.16
			ድምር	906,037,824.63

3.4.3.2 ስጋት፣

ግንባታ ክፍሉ የግንባታ ስራዎችን አጠናቆ ካስረከበ በኃላ ግንባታዎቹ የዩኒቨርሲቲው ንብረት ለመሆናቸው በቋሚ ንብረት መመዝገቢያ መዝገብ ካልተመዘገቡ ግንባታዎቹን በቀላሉ ለመቆጣጠር ያሉበትን ደረጃ ለማወቅ ለማደስ ለማስጠገን አዳጋች ሊሆን ይችላል፡፡በተጨማሪም ለግንባታው አጠቃላይ የወጣውን ወጪ ለማወቅ እንዲሁም የእርጅና ቅናሽ ሂሳብ በቀላሉ ለማስላት አያስችልም፡፡

3.4.3.3 የማሻሻያ ሃሳብ ፤

ከግዥ ውጪ የቋሚ ንብረቶች አንዱ ምንጭ ንብረቶችን ማስገንባት ወይም በራስ መገንባት መሆኑ ይታወቃል፡፡በመሆኑም ማንኛውም ግንባታ ተጠናቆ ጊዜያዊ ወይም የመጨረሻ ርክክብ ሲደረግ ግንባታው የዩኒቨርሲቲው ቋሚ ንብረት በመሆኑ ይህንን ሃላፊነት በተሰጠው አካል ወይም በህንጻዎቹ ስም በንብረት ገቢ ማድረጊያ ደረሰኝ /ሞ-19/ ገቢ ተደርጎ በቋሚ ንብረት መመዝገቢያ ካርድ / Fixed Asset Registration Card-FAR/ እና የተጠቃሚዎች እጅ ላይ የሚገኙ ቋሚ ንብረቶች መቆጣጠሪያ ካርድ/Fixed Asset with user Control Card -UC/ ሊመዘገብ ይገባል፡፡

3.4.3.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

የፌደራል መንግስት የንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 14/2003 አንቀጽ 7/2 የመንግስት መ/ቤቶች ያከናወኑአቸውን የግንባታ ስራዎች እንደ ቋሚ ንብረት በተለየ መዝገብ መመዝገብ እንዳለባቸው ቢገለጽም በበጀት አመቱ ርክክብ የተደረገባቸውን ግንባታዎች ለመመዝገብ ብዙም ከባድ ባይሆንም

ህንጻዎች እንደ ቋሚ ንብረቶች ስቶር ውስጥ ማስገባት የማይቻሉ ከመሆናቸውም በላይ የስቶር ሠራተኞች ግንባታዎችን በሞዴል 19 ገቢ አድርገው ሲፈርሙ በአንጻሩ ህንጻዎቹን በቋሚ ንብረት ወጪ ደረሰኝ ላይ በመፈረም የሚከባቸው ሰው የሌለ (ሠራተኞች የተለያዩ ክፍሎች የሚጠቀሙባቸውን ህንጻዎች በኃላፊነት ፈርመው ለመረከብ ፍቃደኞች ስለማይሆኑ የስቶር ሠራተኞችም በንብረት ወጪ ደረሰኝ ፈርሞ የሚረከባቸው ሰው በሌለበት ሁኔታ ህንጻዎችን በሞዴል 19 ፈርመው ገቢ ለማድረግ ፍቃደኛ ስለማይሆኑ መሆኑን እየገለጽን ወደፊት እላይ የተጠቀሱት ችግሮች ሲፈቱ በመንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ መሠረት ገቢና ወጪውን የምንሰራ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡ በማለት በላኩት ምላሽ ላይ ገልፀዋል፡፡

3.5 መንግስታዊ ለሆኑ ድርጅቶች የተሠጠ የድጋፍ ሂሳብን በተመለከተ፣

3.5.1 ግኝት፣

የፌደራል መንግስት የሂሳብ አያያዝና አወቃቀር ስርዓት መመሪያ በግልፅ እንደተቀመጠው በ6412 የሂሳብ መደብ ተመዝግቦ ወጪ ማድረግ የሚቻለው ነፃ የአስተዳደር እና መንግስታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች የሚሰጥ ድጋፍ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ይሁን እንጂ በዋናው ግቢ ከመደበኛ በጀት ብር 499,999.99 እንዲሁም ከውስጥ ገቢ ብር 500,000.00 በድምሩ ብር 949,999.99 ነፃ ላልሆኑ የአስተዳደር እና መንግስታዊ ለሆኑ ድርጅቶች ከውስጥ ገቢና ከመደበኛ በጀት ክፍያ ተፈፅሞ ተገኝቷል፡፡ ዝርዝር ሁኔታው እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

ተ.ቁ	ቀን	የደረሰኝ አይነት	የደረሰኝ ቁጥር	የሂሳብ መደብ	የተከፍለበት ምክኒያት	የገንዘብ መጠን
1	16/0609	PV	2881	6417	የአዳማ ከተማ 100ኛ አመት የምስረታ በአል የተደረገ ድጋፍ	100,000.00
2	17/06/09	PV	2890	6417	11ኛው ብሄር ብሄረሰቦች ከብረ በአል ለሀረሪ ክልላዊ መንግስት የተሰጠ ድጋፍ	149,999.99
3	12/07/09	PV	3091	6412	ለኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት የባህልና ቱሪዝም ቢሮ የተሰጠ ድጋፍ	200,000.00
4	24/6/09	JV	S-591	6214	ለጋራ ሙለታ ሆስፒታል የተሰጠ ድጋፍ	500,000.00
					ጠቅላላ ድምር	949,999.99

3.5.2 **ስጋት፣**

ዩኒቨርሲቲው ደንብና መመሪያን መሰረት ያላደረገ ክፍያ የመንግስትን ሀብት ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል ፡፡

3.5.3 **የማሻሻያ ሃሳብ፣**

ዩኒቨርሲቲው ማናቸውም ክፍያ ሲከናውን ደንብና መመሪያን መሰረት ያደረገ ሊሆን ይገባል፡፡ ስለዚህ ከደንብና መመሪያ ወጪ የሚከፈል ክፍያ አግባብነት እንደለለው ተወቆ ለወደፊት የማስተካከያ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

3.5.4 **የስራ አመራሩ ምላሽ** ፣

ሐረማያ ዩኒቨርሲቲ በ2009 የበጀት አመት በእቅዱ አካቶ በማቀድ በበጀት አስደግፎ ያስፈቀደና በዚሁ መሰረት ከቀረቡት በርካታ የድጋፍ ጥያቄዎች በበላይ አመራሩ በጥልቀት በመመርመር ከ95 በመቶ ጥያቄዎቹን ሳይቀበልና ክፍያ ሳይፈፅም የመለሰ ሲሆን፤ በዚሁ በግኝት የቀረቡት ግን በሐረሪ ክልላዊ መንግስት የጤናና ህክምና ሳይንስ ኮሌጅ እና የህይወት ፋና ሪፈራል ቲቺንግ ሆስፒታል ያለውና በዚህ የሐረሪ ክልል የብሔር ብሔረሰቦች ዝግጅት ወቅት አንዱና ዋነኛው በክልሉ ውስጥ ከተሰሩ የመሰረተ ልማት አውታሮች ውስጥ ሆስፒታሉ አንዱና ዋነኛው በመሆኑ በዛ ወቅት

1ኛ. ሆስፒታሉ በሀገራችን የመንግስት ተወካዮች ማለት በጠቅላይ ሚኒስቴሩና ሌሎች ሚኒስቴሮች ጭምር ህንፃ ግንባታው የታየና የተጎበኘ በመሆኑ፤

2ኛ. የሐረማያ ዩኒቨርሲቲ የጤና እና ህክምና ሳይንስ ኮሌጅ በዚሁ በሐረሪ ክልላዊ መንግስት ውስጥ የሚገኝ በመሆኑና አንዱና በክልሉ ውስጥ ብቸኛው አንጋፋው የመንግስት ዩኒቨርሲቲ በመሆኑ፤

የሐረማያ ዩኒቨርሲቲ በዚህ የሐረሪ ክልላዊ መንግስት ውስጥ ያለውን የጤናና ህክምና ሳይንስ ኮሌጅ ተማሪዎች፣ መምህራን እና የመንግስት ሀብትን በአግባቡ ከአደጋ ይዞ ለማቆት የክልሉ ድጋፍና ቀና ሀሳብ የግድ ይላል፡፡

ስለዚህ በዚህ የተነሳ ከክልሉ የቀረበው ድጋፍ ለሐረማያ ዩኒቨርሲቲ ቅድሚያ ተሰጥቶት መደገፍ የኛም ድርሻ መሆኑን በመረዳትና ነገውን የተሳካ አብሮ መስራት ከማሰብ የተደረገ መጠነኛ ድጋፍ ነው፡፡

የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት የባህልና ቱሪዝም የተደረገው ድጋፍ በተመለከተ የሐረማያ ዩኒቨርሲቲ በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ክልል ውስጥ ያለ የመንግስት ዩኒቨርሲቲ ሲሆን፤በተለይ በምስራቅ የሀገሪቱ ክፍል የሚገኝ አንጋፋ ዩኒቨርሲቲ ነው፡፡ በተለያዩ ግዜያት የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ዩኒቨርሲቲውን ተማሪዎች፣ የመንግስት ውስን ሀብት እና ሰራተኞቹንና መምህራኑን ጭምር በተለያዩ ጉዳች ሲያግዙና ሲደግፉ ቆይተዋል፡፡ ይህ ድጋፋቸው በአሁኑ ግዜም ቀጥሎ ይገኛል፡፡ በተጨማሪ የሐረማያ

ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በክልሉ ባሉ በርካታ ቢሮዎች እንዱስትሪዎች በሚደረጉ የመስክ ስልጠና ተሰማርተው የትምህርት ጥራቱን ለማስጠበቅ በሚደረጉ የተማሪ የመስክ ላይ ስልጠናዎችን እንዲሰለጥኑ በመፍቀድና በራሳቸው ባለሙያተኞች ያለምንም ተጨማሪ ክፍያ በበጎ ፈቃድ እያገዙ ቆይተዋል፡፡ ከላይ በተጠቀሱት ዝርዝር ሁኔታዎችን የዩኒቨርሲቲው አመራር በጥልቀት በመረዳትና ለወደፊትም ተማሪዎቹ በዚህ የክልሉ ባህልና ቱሪዝም በርካታ ጥናቶችን በውስጡ ለማከናወንም የሚያግዝ መሆኑን በመረዳት በጣም አነስተኛ የገንዘብ ድጋፍ ሊያደርግ ችሏል፡፡ ለጋራ ውለታ ሆስፒታል የተሰጠ የገንዘብ ድጋፍ በተመለከተ ሐረማያ ዩኒቨርሲቲ ከተቋቋመበት አንዱ ተልዕኮ አንፃር በአካባቢው ማህበረሰብ አገልግሎት መስጠት በመሆኑ ይህ ሆስፒታል ደግሞ ለአካባቢው ማህበረሰብ የተሟላ አገልግሎት ለመስጠት ከፍተኛ የገንዘብ ችግር እንደገጠመውና ችግር ላይ በመሆኑ ለአካባቢው ማህበረሰብ አገልግሎት በበቂ ሁኔታ መስጠት እንዳልቻለ በጽሁፍ ገልፆ ድጋፍ በመጠየቅና እንዲሁም የዚህ ሆስፒታል ችግሮቹ በተወሰነ ደረጃ ተቃለው አገልግሎት መስጠት መቻሉ የሀረማያ ዩኒቨርሲቲ የጤና ተማሪዎች ለተግባር ትምህርት በሆስፒታሉ ሲሰማሩ በተሻለ ሁኔታ ሰልጥነው የአካባቢውን ማህበረሰብ ችግር ሊቀርፍ የሚችል የህክምና አገልግሎት መስጠት የሚያስችላቸውን እውቀትና ክህሎት ያስገኛል ብሎ በማሰብ እና የትምህርት ጥራትንም ከማስጠበቅ አንፃር በማሰብ የተደረገ መጠነኛ ድጋፍ መሆኑን ትረዱ ዘንድ እየጠየቅን፤ በቀጣይ ድጋፍና ስፖንሰር በመንግስት ትዕዛዝ በደረሰን ደብዳቤ መሰረት ተግባራዊ እያደረግን መሆኑእና የማሻሻያ ሐሳብን የተቀበልን መሆንን እያሳወቅን ከዚህ በፊት የተደረገው ግን በዩኒቨርሲቲው የአስተዳደር ካውንስል ወሳኔ መሰረት የተደረገ መጠነኛ ድጋፍ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡ በማለት ገልፀዋል፡፡

3.6.1 <u>ከክፍያው ላይ ያልተቀነሰ እና ለመንግስት ገቢ ያልሆነ ተጨማሪ እሴት ታክስ፣</u>

5.6.2 <u>ግኝት፣</u>

በተሻሻለው በገ፣ው ተይዞ ስለሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 27/2004 ዓ.ም አንቀጽ 5/1 ታክሱ ተቀናሽ የሚደረግበት የግብይት ዋጋ ወኪሉ ከብር 50,000.00 በላይ ዋጋ ያለው የእቃ ወይም የአገልግሎት ግዥ ሲፈጽም ለተጨማሪ እሴት ታክስ ከተመዘገቡት ታክስ ከፋዩች ብቻ መሆኑን ይገልጻል፡፡ በዚሁ መሰረት በኦዲት ናሙና ከታዩት የውስጥ ገቢ ሂሳብ ውስጥ ከተፈጸመው የስጋ ከብቶች ግዥ ዩኒቨርሲቲው ታክስ መቀነሱን ኦዲት ሲደረግ ፡

- በድምሩ ብር 1,106,428.89 ከሀረማያ አካባቢ ገበሬ ህብረት ስራ ዩኒየን የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ ሆኖ ሳለ መቀነስ ያለበት ታክስ ያልተቀነሰ እና

ለሚመለከተው ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት ገቢ ያልሆነ መሆኑን በኦዲት ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ዝርዝር ሁኔታ ከታች በአባሪ 6 ቀርቧል፡፡

5.6.3 **ስጋት፣**

ለመንግስት መግባት ያለበት የተጨማሪ እሴት ታክስ በወቅቱ እንዳይገባ ያደርገዋል፡፡በተጨማሪም መመሪያን መጣስ ተጠያቂነት ያመጣል፡፡

5.6.4 **የማሻሻያ ሃሳብ፣**

ከስጋ ከብት ግዥው ላይ ያልተቀነሰው የተጨማሪ እሴት ታክስ ተሰብስቦ ለሚመለከተው ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት ገቢ ሊደረግ ይገባል፡፡ ለወደፊቱ ታክሱ ተቀናሽ የሚደረግበት የግብይት ዋጋ ዩኒቨርሲቲው ከብር 50,000.00 በላይ ዋጋ ያለው የእቃ ወይም የአገልግሎት ግዥ ሲፈጽም ለተጨማሪ እሴት ታክስ ከተመዘገቡት ታክስ ከፋዮች ብቻ መሆኑ አለባቸው፡፡ በተጨማሪም ከአቅራቢዎች ጋር ውል ሲገባ የአንዱ ዋጋ የተጨማሪ እሴት ታክስ ታክሎበት ወይም ሳይታከልበት መሆኑን በግልጽ በውሉ ላይ ሊቀመጥ ይገባል፡፡

5.6.5 **የሥራ አመራሩ ምላሽ፣**

ከሀረማያ አካባቢ ገበሬ ህብረት ስራ ዩኒየን የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ ሆኖ ሳለ መቀነስ ያለበት ታክስ ያልተቀነሰ ለተባለው በወቅቱ የተማሪ የስጋ ቀለብ ከገበሬ ላይ ገዝቶ ለማቅረብ የተደረገ ግዢ በመሆኑ ጨረታው ሲሰጥ የተጨማሪ እሴት ታክስ ታሳቢ ሳይደረግ ከከብት አቅራቢዎች ጋር ውል ባለመዋዋላችን የተነሳ ብሎም የተማሪ ቀለብ በተማሪ 15 ብር ሂሳብ በድጋሚ 15 በመቶ ሲጨመር የበጀት እጥረት ስለሚያመጣ እና ብሎም የስጋ ከብቶችን ከገበሬ ሲገዛ value added ሳይደረግ ቀጥታ ስለሚገዛ በሚል ግልፅ ባለመሆኑ የተፈጠረ ስለሆነ ለወደፊቱ በኦዲቱ በተሰጠው መሰረት ለመስራት የተስማማን መሆኑን እየጠቀስን በግንዛቤ ችግር የተፈጠረ ስለሆነ በቀጣይ ማስተካከያ ወስደን የምናሳውቅ ይሆናል፡፡ በማለት ገልፀዋል፡፡

4. **የተሰብሳቢ ሂሳብ፣**

4.1 **በደንቡ መሠረት በወቅቱ ያልተወራረደ የተሰብሳቢ ሂሳብ፣**

4.1.1 **ግኝት፣**

የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 8 /4 ፊደል መ የተሰብሳቢ ሂሳብ በቂ ማስረጃ ሲቀርብበት ብቻ በተሰብሳቢ ሂሳብነት መያዝ ያለበት ሆኖ የተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችት እንዳይፈጠር ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ በዚህ መሰረት ኦዲት ሲደረግ ፡

- በ4203 የሂሳብ መደብ የሚታይና ለደመወዝ ቅድመ ክፍያና ለውሎ አበል ለተለያዩ ግለሰቦች ተሰጥቶ ሳይሰበሰብ ከአንድ ዓመት እስከ አምስት አመት የቆየ ብር 1,476,464.66 ተሰብሳቢ ሂሳብ መኖሩ፣
- በ4211 የሂሳብ መደብ ለተለያዩ እቃዎች መግዣ በቅድሚያ ክፍያ ወጪ ሆኖ በጊዜ ገደቡ ሳይወራረድ ከአንድ ዓመት በላይ የቆየ ብር 3,883,712.79 መኖሩ፣
- በ4253 የሂሳብ መደብ ላይ የሚታይና ለተለያዩ ድርጅቶችና እቃ አቅራቢዎች ተሰጥቶ ከአራት አመት እስከ አስር ዓመት የቆየ ብር 4,832,924.09 መኖሩ፣
- በ4274 የሂሳብ መደብ ላይ የሚታይ እና ሌሎች በሚለው በቅድሚያ ክፍያ ወጪ ሆኖ በጊዜ ገደቡ ሳይወራረድ ከሁለት አመት እስከ አስር ዓመት የቆየ ብር 34,996,962.20 መኖሩ፣

በጠቅላላ በድምሩ ብር 45,190,063.74 በወቅቱ ሳይወራረድ የቆየ ሂሳብ መገኘቱ በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

4.1.2 ስጋት፣

ተሰብሳቢ ሂሳቦች በወቅቱ ካልተወራረዱ ከቆይታ ብዛት ወደ ማይሰበሰቡበት ደረጃ ሊደርሱ ይችላሉ፡፡

4.1.3 የማሻሻያ ሃሳብ ፣

በውዝፍ የሚታየው ተሰብሳቢ በወቅቱ እንዲወራረድ እና የተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችት እንዳይፈጠር የዩኒቨርሲቲው የበላይ አመራር ተገቢውን ቁጥጥርና ክትትል ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

4.1.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

የሐረማያ ዩኒቨርሲቲ የፋይናንስ የስራ ሂደት በተለያዩ ምክንያቶች የሰራተኞች ስራ መልቀቅና የስራ ጫና በሚፈጥረው ውጥረት ውስጥ እየሰራ ያለ ቢሆንም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ያሉት ተሰብሳቢዎች ሙሉ በሙሉ በ2009 ዓ.ም እየተወራረዱ ያሉ ሲሆን በቀጣይ በወጥነት የተለየ ቲም አዘጋጅተን በትኩረት ተከታትለን በህጉ መሰረት የምናወራርድ ይሆናል፡፡ የቆዩ ተሰብሳቢዎችን በተመለከተ በጊዜው ተሰብሳቢ ሂሳቡን ታሪክ በሚያውቁና በጡረታ በተገለሉ ባለሙያዎች ሰነዶችን በማሰባሰብ ዝርዝር ጥራዝ አዘጋጅተን ለገ/ኢ/ት/ሚኒስቴር ያቀረብንና በአፈፃፀም ረገድ የተሰብሳቢ ሂሳቦች Write off ለማድረግ በጣም አስቸጋሪ የሆኑ አካሄዶችን የያዘ በመሆኑ በተፈለገው ፍጥነት ውሳኔ ተሰጥቶት ሊጠፋ አልቻለም፡፡ ይሁን እንጂ ለተደረገው ጥረት ማሳያ ይሆን ዘንድ የጥራዙን ኮፒ ለኦዲተሮቹ በኦዲት ወቅት አሳይተናል፡፡ ይህንኑ

ጥረት እነርሱም የተገነዘቡ ሲሆን በተሰብሳቢ ሂሳቦች ዙሪያ በኦዲት በቀረበው ግኝት ዩኒቨርሲቲው በቀጣይ በርካታ ስራዎችን ለመስራት የታቀደና ወደ ስራ የተገባ እና የተሰብሳቢ ሂሳብ የእርጅና ግዜ ትንተና የተሰራና ዝግጁ የሆነ ስለሆነ በቀጣይ የማወራረድ ስራው ይሰራል በቀጣይም በከፍተኛ ሁኔታ የተሰብሳቢ ሂሳብ ይቀንሳል የሚል እምነት አለን፡፡ ስለዚህ በ2010 የበጀት አመት ትኩረት ተሰጥቶት በተሰራው የተሰብሳቢ የእርጅና ግዜ ትንተና መሰረት አስፈላጊውን ሁሉ የምንሰራ መሆኑ እናሳውቃለን፡፡ በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

4.1.5 <u>የኦዲተሩ አስተያየት</u> ፣

ተሰብሳቢ ሂሳብን በተመለከተ ለተደረገው ጥረት ማሳያ ይሆን ዘንድ የጥራዙን ኮፒ ለኦዲተሮቹ በኦዲት ወቅት አሳይተናል ቢባልም በወቅቱ ያልተወራረዱ ሂሳቦች በኦዲት ወቅት ተረጋግጠው ለዩኒቨርሲቲው በመግለጫ ተጠይቆ የመጨረሻ የተደረሰበትን በወቅቱ ያልተወራረደ ሂሳብ መተማመኛ ዩኒቨርሲቲው ከሰጠ በኃላ ተስተካክሎ የቀረበ ግኝት በመሆኑ ስራ አመራሩ በኦዲት ማሻሻያ ሃሳብ ላይ በተቀመጠው መሰረት ለወደፊቱ የእርምት እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

5 <u>ተከፋይ ሂሳብ</u> ፣

5.1 <u>በወቅቱ ለባለመብቱ ያልተከፈለ ሂሳብን በተመለከተ፣</u>

5.1.1 <u>ግኝት</u> ፣

የፌደራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 8/5 ፊደል ሀ መሠረት ማናቸውም ወደፊት ክፍያ የሚፈጸምባቸው ሂሳቦች ተከፋይ ሂሳብነታቸው የሚያረጋግጥ በቂ መረጃ ሲቀርብና ስልጣን ባለው አካል ሲፈቀድ በተከፋይ ሂሳብነት መያዝ እንደሚገባ ይገልጻል፡፡ በዚሁ መሰረት ኦዲት ሲደረግ

- በ5002 የሂሳብ መደብ የሚታይ ልዩ ልዩ ተከፋይ ሂሳብ ለሚመለከተው አካል ሳይከፈል ከአምስት አመት በላይ የቆየ ብር 2,191,655.67 መኖሩ፤
- በ5004 የሂሳብ መደብ የሚታይና የደመወዝ ተከፋይ ሂሳብ ለሚመለከተው አካል ሳይከፈል ከአንድ አመት በላይ የቆየ ብር 137,883.60 ሂሳብ መኖሩ፤
- በ5054 የሂሳብ መደብ የሚታይና ሌሎች ተከፋይ ሂሳቦች ለሚመለከተው አካል ሳይከፈል ከአምስት አመት በላይ የቆየ ብር 538,457.62 ሂሳብ መኖሩ፤

በጠቅላላ በድምሩ ብር 2,867,996.89 በወቅቱ ሳይከፈል የቆየ ሂሳብ መገኘቱ በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

5.1.2 ስጋት፣

ተከፋይ ዕዳዎች በወቅቱ ካልተከፈሉ በቆይታ ብዛት ከፍተኛ የዕዳ ክምችት ሊኖር ስለሚችል ተቋሙን ለጉዳት ሊዳርግ ይችላል፡፡

5.1.3 የማሻሻያ ሃሳብ ፣

የዕዳ ክምችት እንዳይኖር ተከፋይ ሂሳቦች በወቅቱ እንዲከፈሉ የእርምት እርምጃ መወሰድ አለበት፡፡

5.1.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

በተከፋይ የተያዙ ሂሳቦች በሀምሌ ወር የሚከፈሉ የመንግስ ተከፋዮች በሰኔ 29 ና 30 መጨረሻ ከተከፋይ የተያዙና በመመሪያው ወሩ ባለቀ እስከ ቀጣይ ወር 15 ቀን ድረስ መክፈል የሚቻልና የተከፈለ መሆኑን አስረድተው የተቀረው የ ግንባታ ፕሮጀክት ማስያዛ ስራው ሲጠናቀቅ የሚጠናቀቁ መሆኑን እያሳወቅን በቀጣይ በይበልጥ ለመስራት እየሰራን መሆኑን እናሳውቃለን፡፡ በማለት ገልፀዋል፡፡

5.1.5 የኦዲተሩ አስተያየት

የኦዲት ግኝቱ በተከፋይ ሂሳብ መደብ በ5002 ፣5004 እና 5054 ከአንድ አመት እስከ አምስት አመት ለቀዩ በወቅቱ ለባለመብቱ ላልተከፈሉ ተከፋይ ሂሳቦች ሲሆን ስራ አመራሩ የሰጠው ምላሽ ከኦዲት ግኝቱ ጋር የማይገናኝ በመሆኑ ስራ አመራሩ በኦዲት ማሻሻያ ሃሳብ ላይ በተቀመጠው መሰረት ለወደፊቱ የእርምት እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

6. በጀት

6.1.1 ግኝት፣

በፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 6/2 መሠረት የበጀት ዝውውር ወይም ተጨማሪ በጀት ካልተፈቀደ በስተቀር ለአንድ የመንግስት መ/ቤት በሂሳብ መደብ ተለይቶ ከተፈቀደው በጀት በላይ ወጪ መፈፀም እንደማይቻል ይገልጻል፡፡ እንዲሁም የዩኒቨርሲቲው የበጀት አስተዳደር፣ አጠባበቅ እና አጠቃቀም በፌዴራል መንግሥት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 እና በፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 12 መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- ለካፒታል በጀት ከተደለደለው ብር 108,058,251.10 ውስጥ ብር 99,795,628.90 በ2008 በጀት ዓመት የዞረ በ2009 በጀት ዓመት በመክፈቻ ሂሳብ የተመዘገበ እና

የተወራረደ በመሆኑ ልዩነቱ ብር 8,262,622.20 ከበጀት በላይ ስራ ላይ የዋለ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡ የሂሳቡ ዝርዝር ሁኔታ ከታች በአባሪ ቁጥር 7 ተመልክቷል ፡፡

6.2 <u>ስጋት</u> ፣

በህግ ከተፈቀደው በላይ በጀት መጠቀም ተጠያቂነት ሊያመጣ ይችላል፡፡

6.3 <u>**የማሻሻያ ሃሳብ**</u> ፣

የዩኒቨርሲቲው ዕቅድና ክንውን የተጣጣመ እንዲሆን መደረግ ይገባዋል፡፡ በተጨማሪም በበጀት ዕቅድ ዝግጅትና አጠቃቀም ላይ ተገቢው ጥንቃቄ እንዲሁም ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

6.4 <u>*የሥራ አመራሩ ምላሽ፣*</u>

- ለካፒታል በጀት በ2009 የበጀት አመት ከተደለደለው አመታዊ በጀት በላይ ብር 8,262,622.20 ጥቅም ላይ ውሎ ተገኝቷል ተብሎ ለቀረበው የኦዲት ግኝት የሐረማያ ዩኒቨርሲቲ የበጀት አጠቃቀሙን በሶፍትዌር በመታገዝ የሚያከናውን እና ለዚህም ስራ በየሩብ አመቱ የበጀት አጠቃቀሙን እየገመገመ ማስተካከያ የሚያደርግና ከበጀት በታችም ይሁን ከበጀት በላይ አፈፃፀሙን በጥብቅ የሚከታተል እና ቁጥጥር የሚያደርግ መሆኑን እየገለፅን፣ በቀረበው ግኝት በ6233 የወጪ ሂሳብ ብር 8,262,622.20 በከጀት በላይ የሚታየው ከዚህ በታች በሰንጠረዥ በግልጽ ለተቀመጡት ድርጅቶች በክፍያ ሰነዶች ተለይተው ከ2009 የበጀት ዓመት በፊት በተሰብሳቢ ሂሳብ 4251 የግንባታ ቅድሚያ ክፍያዎች ተይዘው የቆዩና በ2009 የበጀት አመት በተደረገው የከፍተኛ አመራሩ ባደረገው የግንባታ ፕሮጀክት ተቋራጮችን በውለታቸው መሰረት እንዲያጠናቅቁ በርካታ አስተዳደራዊ እርምጃ በማድረጋቸው እና ብሎም የግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤትም ባደረገው ከፍተኛ ቁጥጥርና ርብርብ በሰንጠረዡ የተጠቀሰው ከ2009 በጀት አመት በፊት የተሰጡ የግንባታ ቅድመ ክፍያዎች ከሚቀርበው የክፍያ ሰርተፊኬት እየተቀነሰ ሲከፈል የተሰብሳቢ ሂሳቡ ሲቀንስ በበኩሉ በጀቱ በብልጫ ሊያሳይና ሊመዘገብ መቻሉን እየገለፅን በተጨማሪ ከግኝቱ ጋር አባሪ 3 ገጽ ማያያዛችንን እያሳወቅን በዚሁ መሰረት ግኝቱ እንዲስተካከል በትህትና እንጠይቃለን፡፡ በማለት ገልፀዋል፡፡

6.5 <u>**የኦዲተሩ አስተያየት**</u>፣

ተያይዟል የተባለው መረጃ አልተያያዘም፡፡ ብር 99,795,628.90 በ2008 በጀት ዓመት የዞረው በ2009 በጀት ዓመት በመክፈቻ ሂሳብ የተመዘገበ እና የተወራረደ ተብሎ ከግኝቱ እንዲወጣ የተደረገው በሂሳብ መደብ 4251 የግንባታ ቅድሚያ ክፍያዎች የሚለውን የያዘ

በመሆኑ የተሰጠው ምላሽ ተቀባይነት የሌለውና አሳማኝ ባለመሆኑ ለወደፊቱ በተሰጠው አስተያየት መሰረት እዲፈፀም እናሳስባለን፡፡

7 **ንብረት ፣**

7.1. **የንብረት አመዘጋገብ፣ አያያዝ እና አጠባበቅ በተመለከተ፣**

7.1.1 **ግኝት፣**

የፌዴራል መንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 ንዑስ 5 የመንግሥት መስሪያ ቤቶች በእጃቸው ያለውን የመንግሥት ንብረት በጥንቃቄ የመያዝ፣ የመጠቀም፣ የመቆጣጠር እና አገልግሎቱ ሲያበቃ ወይም አገልግሎት ላይ በማይውሉበት ጊዜ በወቅቱ በተገቢው መንገድ እንዲወገዱ የሚል ሲሆን በዚሁ መሰረት ኦዲት ሲደረግ፣

የአላቂ እና የቋሚ እቃዎች የንብረት አያያዝን በተመለከተ፣

በዋናው ግቢ፣

- ❖ በቋሚ በስቶር ክፍል ተመድበው የሚሰሩ ሰራተኞች ንብረት የመያዝ በሞደል 19 ገቢ የማደረግና በሞደል 22 ንብረት ወጪ የማድረግ ሃላፊነቶችን በአንድ ሠራተኛ የሚሠራ መሆኑ፣
- ❖ ለቋሚ እቃ የገቢና ወጪ መከታታያ (ስቶክ ካርድ) የማይዘጋጅ መሆኑ፣
- ❖ የአላቂ የገቢና ወጪ መከታታያ (ስቶክ ካርድ) ምዝገባ እየተከናወነ ቢሆንም የንብረቱ መነሻ ምዝገባ መሠረቱ የማይታወቅ እና እየተመዘገበ ያለውም ምዝገባው ወጥነት የሌለው መሆኑ፣
- ❖ የተለያዩ ለቧንቧ ዝርጋታ የሚያገለግሉ በርከት ያሉ የእቃ መሳሪያዎች እና እንዲሁም ቋሚ እና አላቂ እቃዎች ንብረቱን በማን ወጪ እንደተደረገና ባለቤታቸው የማይታወቅ በተለያየ ቦታ በግቢ ውስጥ ለሚገኝ ኮንቴይነሮች ውስጥ ተከማችቶ የሚገኙ መሆኑ፣
- ❖ የተለያዩ የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች በረጅም ጊዜ ግልጋሎት እና በብልሽት ምክንያት ወደ ንብረት ክፍል ተመላሽ በሚሆንበት ጊዜ እና ከጥገና ክፍል አዲስ ዕቃ ወጪ ተደርጎ ለጥገና በሚውልበት ጊዜ ተጠግኖ የተቀየረው ዕቃ አሮጌው ወደ ንብረት ክፍል ተመላሽ በሚደረግበት ጊዜ፣ ቀድሞ የወጣ ዕቃ መሆኑ መለያው ቁጥር ተረጋግጦ ገቢ የማይደረግ መሆኑ፣
- ❖ ንብረት (የቋሚና አላቂ) የሚያንቀሳቅሱ (የሚይዙ) ሠራተኞች በተለያየ ምክንያት የሥራ ክፍል ሲቀይሩ ወይም ተቋሙን ሲለቁ ማስረከብ በሚገባቸው ልክ ለማስረከባቸው ያስረከቡት ከወጪ ቀሪ ትክክለኛነት በውስጥ ኦዲት የማይረጋገጥ መሆኑ፣

❖ የመኪና መለዋወጫ፣ የኤሌክትሪክ እና የቧንቧ ዕቃዎች በዋናው ግምጃ ቤት ንብረቶቹ ገቢ ተደርገው፣ ለሚፈለገው አገልግሎት በሚዘጋጅበት ወቅት በዋናው ግምጃ ቤት ወጪ ተደርጎ በቀጥታ ለሚፈለገው አገልግሎት ማዋል ሲገባ፣ ከዋናው ስቶር ወደ ጊዜያዊ (ሚኒ) ስቶር ገቢ የተደረጉት ንብረቶች ተገቢው ከወጪ ቀሪ ምዝገባ የሚያሳይ ስነ-ስርዓት (Stock card) በሌለበት፣ ንብረቶቹ በየቀኑ ከሚኒ ስቶር ወደ ሚመለከተው የስራ ክፍል ወጪ የሚደረጉ (የሚሰራጩ) በመሆኑም ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች የንብረቶቹ ወጪ ተቋሙ ለተጠቀመበት አገልግሎት የዋለ መሆኑን ለማረጋገጥ አዳጋች ሆኖ ተገኝቷል፡፡

<u>የተማሪዎች ምግብ ግምጃ ቤት፣ የመምህራን መዝናኛ ክበብ ግምጃ ቤት እና ሪሶርስ ግምጃ ቤት ፣</u>

❖ የተማሪዎች የምግብ ግምጃ ቤት ጤፍ ለማስፈጨት የወጣው እና ተፈጭቶ የመጣው የጤፍ ዱቄት ተገቢው መረካከቢያ ጤፉን ለማስፈጨት ከወሰደው አካል ጋር ባለመኖሩ፣ የወሰዱትን ጤፍ እና ፈጭተው የመለሱትን የጤፍ ዱቄት ተመዝኖ ርክክብ የማይደረግ መሆኑ እንዲሁም ዛላ በርበሬ ፣ምስር ክክ ለአበጣሪ ሰራተኞቹ በየጊዜ የሚሰጥ ሲሆን ተበጥሮ ካበቃ በኋላ የተሰጣቸው መጠን መልሶ ሲያስረክቡ ተመዝኖ ርክክብ የማይፈፀም መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል፡፡

<u>በዋናው ግቢ የተበላሹ ንብረቶችን በተመለከተ</u>

- በወድ ዋጋ የተገዙ አዳዲስ 6 የምርጥ ዘር የማጣሪያ ማሽን ከ12 ዓመት በላይ ያለምንም አግልጋሎት የተቀመጠና የተቀመጠበትም ሁኔታ ጥንቃቄ በጎደለው ሁኔታ መሆኑ፣ ስዕላዊ መግለጫ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

- በውድ ዋጋ የተገዛ አዲስ የኑግ ዘር መዝርያ ማሽን ያለ አገልግሎት ለብዙ አመታት የቆየና የተቀመጠበትም ሁኔታ ጥንቃቄ በጎደለው ሁኔታ መሆኑ፣ ስዕላዊ መግለጫ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

- ከአስተዳደር ህንፃ ጀርባ የሚገኝ ትልቅ ጄኔሬተር በብልሽት ምክንያት በሚል ያለምንም አገልግሎት የተቀመጠ፣
- በቤተ መፅሐፍት/ዋናው / ውስጥ የሚገኙ 5 ፕሪንተርና የኮፒ ማሽኖች በብልሽት ምክንያት ግልጋሎት የማይሰጡ መሆኑ፣
- አዲስ 3 ግዙፍ የዳቦ መጋገርያ ማሽኖች ያለአገልግሎት የቆሙ፤ስዕላዊ መግለጫ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

- አንድ የልብስ ማጠብያ ማሽን በብልሽት ምክንያት ያለአገልግሎት የቆመ፣
- አንድ የዳቦ መቁረጫ ማሽን በብልሽት ምክንያት ያለአገልግሎት የቆመ፣
- የውሃ ማሞቂያ ማሽን በብልሽት ምክንያት ያለአገልግሎት የቆመ ፣
- አግሪካልቸር ላበራቶሪ ወስጥ ፡
    - በወድ ዋጋ የተገዛ Autoclave /የባክቴሪያ መሳሪያ / ያለአገልግሎት በብልሽት ብዙ አመት የቆመ ማሽን፣ ስዕላዊ መግለጫ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

- በብልሽት ምክንያት ያለአገልገሎት የተቀመጡ 2 ፍሪጅ ፣
- Plan science/agronomy laboratory ውስጥ2 Gross champers የማይሰሩ፣

- ማዕከላዊ ላብራቶሪ
    - በወድ ዋጋ የተገዛ Termowagee የተባለ ማሽን ያለምንም ብልሽት የተቀመጠ ቢሆንም ነገር ግን ለዚህ ክፍል የማይሆንና ለምህንድስና ክፍል የሚሆን ቢሆንም ያለአግባብ በዚህ ክፍል ውስጥ የተቀመጠ፣
    ስዕላዊ መግለጫ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

- ሶይል ኬሚስተሪ ላብራቶሪ
    - ሁለት Hud የተባለ የኬሚካል ጭሶችን ወደ ውጪ የሚያስወግድ መሳሪያ ሲሆን በብልሽት ምክንያት የቆመ ፣ስዕላዊ መግለጫ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

-
- Distiller የተባለ የተጣራ ውሃ ማውጫ ሲሆን 600W የሚጠቀም ቢሆንም ነገር ግን የሀይል አቅም አነስተኛ መሆኑ ያለምንም ብልሽት የተቀመጠ፤
- Distiller የአፈር ማጣርያ ማሽን /የናይትሮጂን መስርያ ማሽን ሲሆን በብልሽት ምክንያት አገልግሎት የማይሰጥ፣
- ሁለት ፍሪጅ በብልሽት ምክንት በሚል አገልግሎት የማየሰጥ

❖በመሆኑም ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች የተለያዩ ማሽኖች በተለያዩ ምክንያት ግል,ጋሎት ላይ እየዋሉ ባለመሆናቸው ዩኒቨርሲቲውን እንዲሁም መንግስትን ላላስፈላጊ ወጪ እየተዳረገው መሆኑ በኦዲት ወቅት ለማየት ተችሏል፡፡

7.1.2 ስጋት፣

- በመንግሥት ውስን ሀብት የተገዙት ንብረቶች ለብክነትና ለምዝበራ ሊጋለጡ ይችላሉ፡፡
- በአሮጌ ዕቃዎች ላይ ወቅታዊ እርምጃ አለመውሰድ ከፍተኛ መጠን ያለው የተለያዩ ንብረቶች ለበለጠ ብልሽት እንዲዳረጉ የሚያደርግ አሰራር ነው፡፡
- አመታዊ የቋሚ እቃ ቆጠራ በንብረት ክፍል ውስጥ ብቻ የሚከናወን ከሆነ በሰራተኞች እጅ ያለውን ቋሚ እቃ ደህንነት/ያለበት ሁኔታ/ ለማወቅ እና ተገቢውን እርምጃ ለመውሰድ አያስችልም፡፡
- በህክምና መድኃኒቶች ላይ አስተማማኝ የቁጥጥር ስርዓት ካልተዘረጋ መድሃኒቶች ለታቀደው ዓላማ ላይውሉ ይችላሉ፡፡

7.1.3 የማሻሻያ ሃሳብ፣

- ማናቸውም ተመላሽ መለዋወጫ እቃዎች የተመላሽ እቃዎች ንብረት ክፍል ለብቻ ተዘጋጅቶላቸው ተመላሽ የተደረጉት ንብረቶች በእቃ ገቢ ማድረጊያ ደረሰኝ /ሞ-19/ ተመዘግበው ለጥበቃ አመቺ በሆነ ቦታ ሊቀመጡ ይገባል፡፡
- ያለጥቅም የተቀመጡ እቃዎች የሚሰሩትና የማይሰሩት ተለይተው ተገቢውን እርምጃ ሊወሰድባቸው ይገባል፡፡

- ሰራተኞች በሚቀያየሩበት ወቅት ማስረከብ በሚገባቸው ልክ ለማስረከባቸውን ያስረከቡት ከወጪ ቀሪ ትክክለኛነት እንዲረጋገጥ፣ የተማሪዎችና የሀሙማን የምግብ ዕቃዎች ከብክነትና ከጉድለት እንዲሁም በመንግሥት ላይ ተጨማሪ ወጪ እንዳያስከትል በታዩት ግድፈቶች ላይ የእርምት እርምጃ ጊዜ ሳይሰጠው ተገቢውን እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

7.1.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

1. መመሪያው በሚያዘው መሰረት ዩኒቨርሲቲውም ለቋሚ እቃዎች ማርከርን ይጠቀማል፡፡ ሆኖም ግን በማርከር ተጽፌው የሚወጡ ዕቃዎች በቀላሉ የመጥፋት ባህርይ ያላቸው በመሆኑ አንዳንድ የቋሚ ንብረቶች ላይ ቁጥሮቹ እንደጠፉ ለመረዳት ችለናል፡፡ በመሆኑም በአሁኑ ሰዓት የፕላስቲክ ስቲከሮችን መጠቀም ጀምረናል፣ ይህም ቢሆን አመርቂ ባለመሆኑ በቀጣይ ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት በባርኮዲንግ ለመጠቀም እንቅስቃሴ መጀመሩን፣
2. ከዚህ ቀደም የቋሚ ንብረት መቆጣጠሪያ ካርድ ባለመኖሩ የተነሳ የተፈጠረ ችግር ሲሆን በአሁኑ ሰዓት ለእያንዳንዱ ሠራተኛ የተጠቃሚዎች ካርድ (UC) User Card የተዘጋጀ በመሆኑ በቀጣይ እንደሚቀረፍ፣
3. ቀደም ሲል የተመላሽ ዕቃዎች ግምጃ ቤት እጥረት በመኖሩ የተነሳ አንዳንድ ዕቃዎችን በጊዜው ተመላሽ ማድረግ አልተቻለም፡፡ በአሁኑ ሰዓት ትልቅ የተመላሽ ዕቃዎች ግምጃ ቤት በመገኘቱ የታዩ ችግሮች በመቀረፍ ላይ መሆናቸው፣
4. አገልግሎታቸውን የጨረሱ የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎችና ብረታ ብረት ነክ ንብረቶችን የማስወገድ ሃላፊነት የመንግስት ግዢና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት መሆኑ ይታወቃል፡፡ በዚሁ መሰረት የብረታ ብረትና አልሙኒየም ዕቃዎች በተጠናከረ መልኩ በመወገድ ላይ ሲሆኑ የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎችን በተመለከተ በተለያዩ ጊዜያት በደብዳቤም በአካልም በመሄድ ብናመለክትም እስካሁን መልስ ሊያገኙ አለመቻላቸውን፣
5. የአላቂ ግምጃ ቤት በአዲስ መልኩ እየተደራጀ በመሆኑ አስፈላጊው ግዢው የተፈፀመ ስለሆነ መደርደሪያዎቹ በመገጠም ላይ መሆናቸውን፣
6. ቀደም ሲል ዩኒቨርሲቲው በአንድ ጠቅላላ ግምጃ ቤት የሚተዳደር በመሆኑ የተነሳ የተፈጠረ ችግር ሲሆን በአሁኑ ሰዓት የተማሪዎች መመረቂያ ገዋንን በተመለከተ በተፃፈ ደብዳቤ ለሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች ሁሉ ጉዳዩን ያሳወቅን ሲሆን የተስተዋሉትን ክፍተቶች አግባብነት ባለው መልኩ ለማስተካከል እየሰራን እንገኛለን፡፡
7. በመለዋወጫ ዕቃ ግምጃ ቤት ሠራተኛው ያልተረከባቸው የተባሉት ንብረቶች ከ15-20 ዓመታት በፊት የተቀመጡ የመምህራን የግል ንብረቶች ሲሆኑ እነዚህም ጥቃቅን

ንብረቶች በተለያ ጊዜ ወደ ውጭ ሀገር ሄደው በዛው የቀሩ ሠራተኞች ንብረት መሆኑን ያረጋገጥን ሲሆን ግምጃ ቤት ውስጥ መቀመጣቸው አግባብነት የሌለው መሆኑ የታመነበት ስለሆነ ወደ ሌላ ቦታ የማለዋወጥ ስራ እየተሰራ ነው፡፡

8. የአላቂ ዕቃዎች ገቢና ወጪ መቆጣጠሪያ ካርድ (Stock Card) ሠራተኛዋ በወሊድ ምክንያት ስራ ላይ ባለመኖራቸው የተፈጠረ ክፍተት ሲሆን የአመዘጋገብ ክፍተት የታየባቸውን ሠነዶች በመለየት የትርፍ ጊዜያቸውን ጨምረው እንዲሰሩ በማድረግ የማስተካከያ እርምጃ በመሠራት ላይ ይገኛል፡፡

7.2 ተሽከርካሪዎች እና የነዳጅ አጠቃቀምን በተመለከተ፣

7.2.1 ግኝት፣

የፌዴራል መንግሥት የተሽከርካሪዎች ስምሪት እና አጠቃቀም መመሪያ 32/2004ዓ.ም ክፍል 3 አንቀጽ 9/1 እና 2 መ/ቤቶች የተሽከርካሪዎችን የነዳጅ ፍጆታ ለመከታተል እና መዝግቦ ለመያዝ እንዲረዳቸው የተሽከርካሪዎች የኪ/ሜ ቆጣሪ ጌጅ የተሟላና በትክክል የሚሰራ መሆኑን በየጊዜው በመከታተል ማረጋገጥ እንዳለባቸውና እያንዳንዱ ተሽከርካሪ የፈጀውን የነዳጅ መጠን ከሸፈነው የኪ/ሜ መጠን ጋር እየተገናዘበ ተገቢው ሪፖርት በየወሩ መቅረብ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ በዚህ መመሪያ መሰረት የዩኒቨርሲቲው ተሽከርካሪ መኪናዎችና ነዳጅ አጠቃቀም ኦዲት ሲከናወን፣

- ቁጥራቸው 20 የሚሆኑ ተሽከርካሪዎች የሚወገዱ በሚል የቆሙ፣
- 17 ተሽከርካሪዎች እያንዳንዳቸው ተጠግነው አገልግሎት ላይ የሚውሉ እና አገልግሎት ላይ የማይውሉ ለመሆናቸው ምንም አይነት ውሳኔ ሳያገኙ የቆሙ ፣
- የሰሌዳ ቁጥር ኢ.ቲ ኮድ 4-01398 መለዋወጫ አልተገኘለትም ያለምንም አገልግሎት የቆመ፤
- በተለያዩ ምክንያቶች የቆሙ በርከት ያሉ ተሽከርካሪዎች ካለመጠለያ የቆሙ መሆኑ፣
- 8 ትራክተሮች በብልሽት ምክንያት የማይሰሩ እና ከነዚህ ውስጥ ሦስቱ ሞተር የሌላቸው መሆኑ፣
- 11 ትራክተሮች የህይወት ታሪካቸውን የሚገልጽ ማህደር የሌላቸው መሆኑና የትራክተሮቹ ብዛት በውል የማይታወቅ መሆኑ፣
- የተለያዩ የትራክተር መለዋወጫ ዕቃዎች እና ጎማ ጥንቃቄ በጎደለው መልኩ የተቀመጡና አብዛኞቹም በአቀማመጥ ምክንያት ሙሉ ለሙሉ የተባላሹ መሆናቸው፣

- 14 ሞተር ሳይክሎች ተበላሽተዋል በሚል የቆሙ እንዲሁም አቀማመጣቸው ጥንቃቄ የጎደለው መሆኑ፣
- ዩኒቨርሲቲው የመኪና ነዳጅ ግዥ ፈጽሞ የተገዛው ነዳጅ ወደ ነዳጅ ማጠራቀሚያው ጉድጓድ ገቢ በሚደረግበት ጊዜ የነዳጅ ማደያ ንብረት ሠራተኛ ነዳጁን በመጠን ምን ያህል እንደተረከበ በፊርማ የሚያረጋግጥበት መሰረታዊ የስቶክ መዛግብቶችን በሞዴል 19 እና ስቶክ ካርድ በመጠቀም አስፈላጊውን ምዝገባ ሙሉ በሙሉ የማይመዘገብ መሆኑ፤
- የነዳጅ ማደያ ሠራተኛ በሞደል 20 በታዘዘበት መሠረት ለተሽካርካሪዎች እና ለተለያየ አገልግሎት ናፍጣና ነዳጅ እየተቀዳ የሚሞላው ህጋዊነት በሚያረጋግጥበት መሰረታዊ የስቶክ መዛግብቶችን ሞዴል 22 እና እስቶክ ካርድ በመጠቀም አስፈላጊውን ምዝገባ ሙሉ በሙሉ የተቀዳ ናፍጣና ነዳጅ የማይመዘገብ በመሆኑ በነዳጅ ማጠራቀሚያው ጉድጓድ እንዲሁም በርሜል ውስጥ ያለው ከወጪ ቀሪ ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፤
- ሠራተኛው በአግባቡ ለሥራ የሚያስፈልጉ ሠነዶች ማለትም የነዳጅ ማዘዣው ሞ/20 በአግባቡ ተይዘው የተቀመጡ ባለመሆኑ በዓመቱ ወጪ የሆነውን ናፍጣ እና ነዳጅ ትክክል ለመሆኑ ማነጻጸር ያልተቻለና ቢሮ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች ያልተሟሉለት በመሆኑ ከናፍታና ከነዳጁ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሰነዶች በአግባብነት ያልተያዙ መሆኑን ለማየት ተችሏል፡
- ጀኔሬተሮቹን ለማንቀሳቀስ በሰዓት ወይም በቀን የሚያስፈልገው የነዳጅ መጠን ጥናት ተደርጎ መጠኑ ባለመወሰኑ የመቆጣጠሪያ ስልት የሌለ መሆኑ፤
- የጀኔሬተር ኦፕሬተር የሥራ ክፍል ሠራተኞች /ኦፕሬተሮች/ ለማሽኖቹ የሚያስፈልገውን ነዳጅ በነዳጅ መጠየቂያ ቅጽ ላይ በመሙላት በሚመለከተው የሥራ ክፍል ኃላፊ የሚረጋገጥበት ሥርዓት የሌለ መሆኑ፤
- ለጀኔሬተሮች የዋለው የነዳጅ ፍጆታ ብዛትና የገንዘብ መጠን የሚገልጽ በማስረጃ የተደገፈ ሪፖርት ለማኔጅመንቱ ወይም ለሚመለከተው የስራ ሂደት የማይቀርብ በመሆኑም ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች ለነዳጅ የወጣው ወጪ ተቋሙ ለተጠቀመበት አገልግሎት የዋለ መሆኑን ለማረጋገጥ አዳጋች ሆኖ ተገኝቷል፡፡

7.2.2 ስጋት ፣

- ጌጃቸውና ኪ/ሜ መቁጠሪያቸው የማይሰሩ መኪኖች መጠቀም የነዳጅ አጠቃቀም ብክነት ሊያስከትል ይችላል፡፡
- ተጠግነው አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ ንብረቶች ለበለጠ ብልሽት ሊዳረጉ ይችላሉ፡፡
- ለጀኔሬተር አገልግሎት በሚውለው ነዳጅ ላይ አስተማማኝ የውስጥ ቁጥር ሥርዓት ካልተዘረጋ በከፍተኛ ገንዘብ ብክነት ያጋልጣል፣ የተገዛውም ነዳጅ ለሚፈለገው ዐላማ መዋሉን ለማረጋገጥ አዳጋች ከመሆኑም በተጨማሪ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር አለማድረግ ለብልሹ አሰራር መከሰት ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡
- በመንግስት ውስን ሃብት የተገዛው ነዳጅ ለብክነት ሊጋለጡ ይችላሉ ፡፡ በተጨማሪም ለብልሽ አሰራር በር ሊከፍት ይችላል፡፡

7.2.3 የማሻሻያ ሃሳብ ፣

- የዩኒቨርሲቲው አመራር በመንግሥት ውስን ሀብት የተገዙት ተሽከርካሪዎች አገልግሎት ላይ የሚውሉበትን ተገቢውን የሆነ እርምጃ ጊዜ ሳይሰጠው ሊወስድ ይገባል፡፡ለወደፊቱ በተሽከርካራች ዙሪያ አመራሩ ጥብቅ ቁጥጥር እና ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡
- የነዳጅ አጠቃቀም ሥርዓት ጠንካራ እንዲሆን የዩኒቨርሲትው የበላይ አመራራ ጊዜ ሳይወስድ ተገቢውን እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡
- የነዳጅ ወጪውን ትክክለኛነት ለማወቅ አስፈላጊውን ምዝገባ በማከናወን ሰነዶቹን በአግባቡ እንዲጠበቁ በማድረግ ለኦዲት በሚጠየቁበት ጊዜ ሰነዶቹ በተሟላ መልክ እንዲቀርቡ ዩኒቨርሲቲው ተገቢውን እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል፡፡
- ለጀኔሬተር በሚውለው የነዳጅ ፍጆታ ላይ አስተማማኝ የውስጥ ቁጥር ሥርዓት እንዲዘረጋ እንዲሁም የተዘረጋው የቁጥጥር ሥራት የሚጠበቀውን ውጤት ለማስገኘቱ ክትትል እንዲደረግ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

7.2.4 የሚመለከተው ኃላፊ ምላሽ፣

የማሻሻያ ሃሳቡን ተቀብለውታል፡፡

7.3 መድሃኒትና ለመድሃኒት አገልግሎት የሚውሉ መሳሪያዎች አያያዝ እና አጠባበቅ ፣

7.3.1 ግኝት፣

የፌዴራል ሆስፒታሎች የመድሀኒት አገልግሎት አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 001/2006 አንቀጽ 7.4 ማንኛውም ሆስፒታል ተቀጣጣይነት ያላቸውን ወይም መድሃኒቶችን

ሊበክሉ የሚችሉ ኬሚካሎችን እንዲሁም የህክምና መሳሪያዎችን እና መገልገያዎችን ከሌሎች መድኃኒቶች ለይቶ ማስቀመጥ አለበት፡፡እንዲሁም በዚሁ መመሪያ አንቀጽ 8.1 ከሆስፒታሉ የመድሃኒት መጋዘን ወደ ተለያዩ አገልግሎት መስጫ እና ማደያ ክፍሎች አገልግሎት ወጪ የሚደረጉ መድሃኒቶች ክፍሎቹ ከሚሰጡት አገልግሎት አኳያ የመድሃኒትና ህክምና ኮሚቴ ለየክፍሎቹ በሚዘጋጀው መዘርዝር መሰረት መሆን እንዳለበት ይገልጻል ፡፡ በዚሁ መሰረት የመድሃኒት አገልግሎት አሰጣጥ ኦዲት ሲደረግ ፡

<u>በህክምና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ</u>

- ከሆስፒታሉ የመድሃኒት መጋዘን ወደ ተለያዩ አገልግሎት መስጫ እና ማደያ ክፍሎች ከመሰራጨቱ በፊት ከሚሰጡት አገልግሎት አኳያ የመድሃኒትና ህክምና ኮሚቴ ለየከፍሎቹ በሚያዘጋጀው መዘርዝር መሰረት አለመሆኑ እና ይህ አሰራር በሆስፒታሉ ተገባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፣
- ሆስፒታሉ የመድሃኒት ቆጠራ በሚያደርግበት ወቅት የቆጠራው ውጤት ከመድሃኒት መቆጣጠሪያ መዝገቦች እና ከሂሳብ ሪፖርት ጋር ያልተገናዘበ መሆኑ፣
- በመድሃኒት ማደያ ክፍሎች የመድሃኒት ክምችት እና እንቅስቃሴን ለመከታተልና ለመቆጣጠር የሚያስችል ቢን ካርድ፣ስቶክ ካርድ ወይም ዘመናዊ ሶፍትዌር በመጠቀም ያልተቆራረጠ ወቅታዊ ምዘገባ የማይደረግ መሆኑ፣
- የአገልግሎት ጊዜያቸው ያለፈባቸው መድኃኒቶች እንዲሁም ተብላሽተው የተቀመጡ የህክምና መገልገያ መሳሪያዎች በአንድ የንብረት ክፍል ውስጥ ከመቀመጣቸው በተጨማሪ መሳሪያዎቹ ተጠግነው አገልግሎት ሊሰጡ እንደሚችሉና እንደማይችሉ በባለሙያ ሳይለይና ሳይረጋገጥ ለረዥም ጊዜ የተቀመጡ መሆኑ፣
- የሆስፒታሉ ፋርማሲ ክፍል በቁጥር 2/2071/51/2 በቀን 19/10/2009 ለኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድሃኒትና የጤና እንክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን ድሬዳዋ ቅርንጫፍ ብዛት ያላቸው የአገልግሎት ጊዜያቸው ያለፈባቸው መድኃኒቶች እንዲወገዱ ቢጠይቅም ሳይወገዱ ከሶስት ዓመት በላይ የቆዩ መሆኑ፣
- በላብራቶሪ ክፍል ውስጥ አዲስ ራዲዮ ሜትር በሪኤጀንት ግዥ ምክንያት ከሁለት ወር በላይ ፣ ማይንድ ድራይ ለኬሚስትሪ ስራ የሚያገለግል አንድ ዓመት፣ ሁማልላይት ፕላስ ስምንት ወር ፣ ጂን ኤክስፐርት ሁለት ወር ፣ ሁለት ፍሪጆች ከአንድ ዓመት በላይ አገልግሎት ሳይሰጡ የቆዩ መሆኑ

በዋናው ግቢ ፣

- በዋና ስቶር `መድሃኒት ስቶር ክፍል ተመድቦ የሚሰራ ሰራተኛ ንብረት የመያዝ፣ ገቢና ወጪ በሞዴል 19 እና 22 የማድረግ ሃላፊነቶችን በተደራቢነት የሚሰራ መሆኑ፤
- ከዋናው የመድኃኒት ስቶር መድኃኒት ወጪ ሆኖ ወደ መድኃኒት ማደያው (Dispensary room) የገባው መድሃኒት፤ ለመውጣቱ /ለመሰራጨቱ/ ማረጋገጫ የፕሪስክሪፕሽን ወረቀት ቢኖርም ከዋናው የመድኃኒት ስቶር የወጣው መድኃኒት እና በፕሪስክሪፕሽን ወረቀት ላይ የተመዘገበው መድኃኒት ተገናዝቦ ከወጪ ቀሪ መከታታያ (ስቶክ ካርድ) እና ቢን ካርድ ምዝገባ የማይከናወን ከመሆኑም በተጨማሪ መድኃኒቱ ተሰራጭቶ ሥራ ላይ የዋለው መድኃኒት ምን ያህል እንደ ተሰራጨ በአይነት እና በገንዘብ መጠን ተዘጋጅቶ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት የማይደረግ መሆኑ በኦዲት ወቅት ለማየት ተችሏል፡፡

7.3.2 **ስጋት** ፣

- የመድሃኒትና የመድሃኒት እቃዎች ብክነት ከማምጣቱ በላይ ለብልሹ አሰራር በር ይከፍታል፡፡
- የመድሃኒት ቁጠራው ትክክለኛ የመደሃኒት አያያዝና አጠቃቀምን ላያሳይ ይችላል፡፡
- የአገልግሎት ጊዜያቸው ያለፈባቸው መድኃኒቶች ጊዜ ሳይሰጠው ካልተወገዱ ለጤና ጠንቅ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡
- ወቅታዊ ምዘገባ የማይደረግ ከሆነ የመድሃኒት ክምችት እንዲኖር ከማድረጉ በላይ እንቅስቃሴውን በቀላሉ ለመከታተልና ለመቆጣጠር አያስችልም፡፡
- የአገልግሎት ጊዜያቸው ያለፈባቸው መድኃኒቶች ጊዜ ሳይሰጠው ካልተወገዱ ለጤና ጠንቅ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

7.3.4 **የማሻሻያ ሃሳብ**

- ከመድሃኒት መጋዘን ወደ ተለያዩ አገልግሎት መስጫ እና ማደያ ክፍሎች ከመሰራጨቱ በፊት ከሚሰጡት አገልግሎት አኳያ የመድሃኒትና ህክምና ኮሚቴ ለየክፍሎቹ በሚዘጋጀው መዘርዝር መሰረት መሆን አለበት ይህ አሰራርም ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- የአገልግሎት ጊዜያቸው ያለፈባቸው መድኃኒቶች እንዲሁም ተብላሽተው የተቀመጡ የህክምና መገልገያ መሳሪያዎች በተለያየ ንብረት ክፍል ውስጥ ለቁጥጥር አመቺ በሆነ መልኩ ሊቀመጡ ይገባል፡፡ የህክምና መገልገያ

መሳሪያዎች ተጠግነው አገልግሎት ሊሰጡ እንደሚችሉና እንደማይችሉ በባለሙያ ተለይተው ተገቢውን እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡ የአገልግሎት ጊዜያቸው ያለፈባቸው መድኃኒቶች ለጤና ጠንቅ እንዳይሆኑ የስራ አመራሩ ጊዜ ሳይሰጠው የሚወገዱበትን መንገድ ከሚመለከተው አካል ጋር በመነጋገር የሚቻለውን ሁሉ ሊያደርግ ይገባል፡፡

7.3.4 **የሚመለከተው ኃላፊ ምላሽ፣**

የተሰጠውን የማሻሻያ ሃሳብ ተቀብለውታል፡፡

8 ልዩ ልዩ ፣

8.1 ጥሬ ገንዘብን በተመለከተ ፣

8.1.1 **ግኝት፣**

የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የገንዘብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 7 የሂሳብ ሰነዶችና መዛግብት አያያዝና አጠቃቀም በሚለው ስር ‹‹የመንግስት መስሪያ ቤቶች ማናቸውንም የሂሳብ እንቅስቃሴ ሚኒስቴሩ ባወጣቸው ወይም ዕውቅና በሰጣቸው ቀጥለው በተመለከቱት የሂሳብ ሰነዶችና መዛግብቶች መያዝ አለባቸው፡፡ በአገር ውስጥ ገንዘብ ለሚፈፀሙ ክፍያዎች የወጪ ማስመስከሪያ መሂ/7/ በሣጥን የሚከናወን ክፍያ መሂ7/1 በባንክ በኩል የሚከናወን ክፍያ መሂ/7/2 ስራ ላይ ማዋል እንዳለባቸውና እና ጥሬ ገንዘብ የማይንቀሳቀስባቸው ወይም ጥሬ ገንዘብ ነክ ያልሆኑ ማናቸውም የሂሳብ ክንውኖች በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ መሂ/9 መፈጸም እንዳለባቸው መመሪያው ቢገልጽም በዋናው ግቢ እንዲሁም በሁሉም ክላስተሮች በሳጥን ለሚከናወን ክፍያ መሂ7/1/ (የሳጥን የወጪ ማስመስከሪያ) ወጪው መመዝገብ ሲገባው ጥሬ ገንዘብ ነክ ያልሆኑ ሂሳቦች በሚመዘገብበት በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ መሂ/9 ምዝገባው የሚከናወን መሆኑ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

8.1.2 **ስጋት** ፣

በሳጥን ለሚከፈሉ ማናቸውም ክፍያ በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ መሂ/9 መመዝገብ በገንዘብ ያዡ በኩል ጥሬ ገንዘቡን ለመከፈሉ ማረጋገጥ አያስችልም፡፡ በተጨማሪም ለብልሹ አሰራር መንገድ ይከፍታል፡፡

8.1.3 **የማሻሻያ ሃሳብ፣**

በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ መሂ/9 መመዝገብ ያለባቸው የሂሳብ እንቅስቃሴዎች ጥሬ ገንዘብ ነክ ያልሆኑ ለምሳሌ የደመወዝ ወጪ፣ የአይነት እርዳታ፣ አንዳንድ የተሰብሳቢ ሂሳብ እና የተከፋይ የሂሳብ እንቅስቃሴዎች፣ በስህተት የተመዘገቡትን ለማረም እና የመዝጊያ ሂሳቦች ምዝገባ የሚከናወንበት በመሆኑ የጥሬ ገንዘብ ነክ የሆኑ ሂሳቦች በሣጥን የሚከናወን ክፍያ መሂ7/1 (የሳጥን የወጪ ማስመስከሪያ ደረሰኝ) መመዝገብ ይኖርበታል፡፡

8.1.4 <u>የሚመለከተው ኃላፊ ምላሽ፣</u>

የተሰጠውን የማሻሻያ ሃሳብ ተቀብሎታል፡፡

8.2 <u>የደመወዝ የሂሳብ ምዝገባን በተመለከተ፣</u>

8.2.1 <u>ግኝት፣</u>

የፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ዓ.ም አንቀጽ 12/3 መሰረት ለሰራተኞች በባንክ በኩል ደመወዝ ሲከፈል አስፈላጊው የሂሳብ ምዝገባ መከናወን እንዳለበት ይገልጻል፡ ይሁን እንጂ ዩኒቨርሰቲው የደመወዝ ጥያቄ ክፍያ ሲቀርብ በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ /JV/ የሂሳብ ምዝገባው የማይከናወን እና ባንኩ በእያንዳዱ ሰራተኛ የቁጠባ ሂሳብ የተጣራ ደመወዝ ገቢ ማደረጉን የባንክ አድቫይስ ሲደርስ ብቻ የሂሳብ ምዝገባ የሚያከናወን መሆኑን በኦዲት ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

8.2.2 <u>ስጋት፣</u>

የደመወዝ ክፍያ ጥያቄ ሲቀርብ እና ደመወዝ ሲጠናቀቅ ተገቢውን ምዝገባ የማይከናወን ከሆነ ለሰራተኞች የተከፈለውን ትክክለኛ ውጪ ለማረጋገጥ አያስችልም፡፡ በተጨማሪም ለብልሹ አሰራር መንገድ ይከፍታል፡፡

8.2.3 <u>የማሻሻያ ሃሳብ፣</u>

ዩኒቨርሰቲው የደመወዝ ጥያቄ ክፍያ ሲቀርብ በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ /JV/ የሂሳብ ምዝገባው

6111----------------XXX

6131-----------------XXX

1101-------------------------xxx

5003-------------------------xxx

5004-------------------------xxx እንዲሁም ባንኩ በእያንዳንዱ ሰራተኛ የቁጠባ ሂሳብ የተጣራ ደመወዝ ገቢ ማደረጉን የባንክ አድቫይስ ሲደርስ በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ደረሰኝ/BPV/

5004--------------XXX

4103-------------------------XXX በማድረግ የሂሳብ ምዝገባው መከናወን አለበት፡፡

8.2.4 <u>የሚመለከተው ኃላፊ ምላሽ፣</u>

የተሰጠውን የማሻሻያ ሃሳብ ተቀብሎታል፡፡

8.4 በ2008 በጀት ዓመት በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት እርምጃ ያልተወሰደባቸውን ግኝቶች በተመለከተ፤

8.4.1 ግኝት፣

በ2008 በጀት ዓመት ኦዲት ሪፖርት በተሰጠው አስተያየት መሠረት እርምጃ ስለመወሰዱ ለማጣራት ኦዲት ሲከናወን፡- ዩኒቨርሲቲ በተወሰኑት የኦዲት ግኝቶች ላይ ሙሉ በሙሉ እንዲሁም በተወሰኑት ላይ በከፊል የእርምት እርምጃ የወሰደ ቢሆንም ከዚህ በታች በዝርዝር የተቀመጡት የኦዲት ግኝቶች እርምጃ ያልተወሰደባቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

- የውል ግዴታውን ካልፈጸመ አንድ መምህር ብር 111,168.00 ግንቦት 9/2006 ለተቋሙ እንዲከፍል የተወሰነ ሲሆን ገንዘቡ ከባለጉዳዩ ተመላሽ ተደርጎ ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፤
- የመኖሪያ ቤት ለተሰጣቸው መምህራን በበጀት ዓመቱ (2008ዓ.ም) አላግባብ ብር 158,200.00 የቤት አበል የተከፈለና ገንዘቡ ተመላሽ ያልሆነ መሆኑ፤
- ውጭ አገር ትምህርታቸውን ለሚከታተሉ አካዳሚክ ባለሙያዎች ግማሽ ደመወዝ መከፈል ሲገባው በበጀት ዓመቱ ሙሉ ደመወዝ በመከፈሉ በድምሩ ብር 246,996.00 አላግባብ በብልጫ የተከፈለ የደመወዝ ተመላሽ ያልሆነ መሆኑ፣
- ለተለያዩ ኮሚቴዎች ላስተባበሩበት፣ ለተሳተፉ ሰራተኞች ማትጊያ በሚል በድምሩ ብር 589,908.61 አለአግባብ ተከፍሎ ተመላሽ ያልሆነ መሆኑ፣
- በተከታታይ ትምህርት መርሃ-ግብር ላስተማሩ መምህራን በአስተዳደር ካውንስል በተወሰነው ተመን መሰረት በበጀት ዓመቱ ብር 1,822,579.00 በመመሪያው ከተፈቀደው ተመን በላይ ለአካዳሚክ ባለሙያዎቹ ከውስጥ ገቢ ክፍያ የተፈፀመ መሆኑ፤
- ለድህረ ምረቃ (Msc and Phd) ተማሪዎች ፈተና ለፈተኑበት/ለገመገሙበት (Internal and External Examiner/Session) እና የማማከር አገልግሎት ለሰጡበት (Supervision) በጥቅሉ የHonorarium ክፍያ በሚል እንደ ትምህርት ደረጃው ከሚመለከተው አካል የጸደቀ የክፍያ ተመን ሬት ሳይኖረው በአስተዳደር ካውንስል በተወሰነው ተመን መሰረት በድምሩ ብር 1,418,020.00 ክፍያ የተፈፀመ መሆኑ፤
- በዩኒቨርሲቲው ህንፃ ግንባታ ሥራ ላይ ከተሰማሩት የስራ ተቋራጮች መካከል፤ ባቢሌ የምርምር ማዕከል ግንባታ ላይ የተሰማራው የሥራ ተቋራጭ (ተስፋዬ

አስፈሪ) ብር 304,051.45፣ ጉርሱም የምርምር ማዕከል ግንባታ ላይ የተሰማራው የሥራ ተቋራጭ (ዳዊት ግርማይ) ብር 1,838,862.40፣ የማባዣ ክፍል ግንባታ ላይ የተሰማራው የሥራ ተቋራጭ (ተክለሐይማኖት አስገዶም) ብር 668,635.00 እና የእንስሳት ህክምናና ቄራ ግንባታ ላይ የተሰማራው የስራ ተቋራጭ (ኮባልት) ብር 450,590.60፣ በድምሩ ብር 3,262,139.45 የወሰዱት የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ እያለባቸው ውለታቸው የተቋረጠ መሆኑ፤

- በጤና ሳይንስ ኮሌጅ በአገራዊ ስልጠና ላይ ለተሳተፉ 624 ሠራተኞች ለተከፈለው የምሣ አበል ብር 154,853.25 እና የማህበረሰብ አቀፍ ትምህርት ክፍል የተግባር ልምምድ ከሚያደርጉ ከየጤና ተቋማት የተወጣጡ የምርምር ዘዴ ሥልጠና ለወሰዱ አሰልጣኞችና ለ44 ተሳታፊዎች ለተከፈለው ብር 76,437.00፣ በድምሩ ለብር 231,290.25 ተሳታፊዎቹ በትክክል ስልጠና ላይ መሳተፋቸውን የሚያመለክት የሥራ መከታተያ (Attendance Sheet) ያልቀረበ መሆኑ፤
- በዩኒቨርሲቲው በህንፃ ግንባታ ሥራ ላይ የተሰማሩ 4 የስራ ተቋራጮች (መላ ኢንጂነሪንግ፣ ደመራ ኢንጂነሪንግ፣ ጉሌድ ኮንስትራክሽንና እምነቴ እንዳሻው ኮንስትራክሽን) ለብር 17,672,437.04 የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና ያላቀረቡ እና ብር 14,964,325.86 የቅድሚያ ክፍያ የሚፈለግባቸው 3 የስራ ተቋራጮች (ጫላ ኮንስትራክሽን፣ ኤም ኮንስትራክሽንና ሳፍኮን ኮንስትራክሽን) ደግሞ ያቀረቡት ዋስትና ያልታደሰ /ጊዜው ያለፈበት/ መሆኑ፤
- ወደተለያዩ ተቋማት ለትምህርት ተልከው በገቡት ውለታ መሰረት ባለመፈፀማቸው የሚፈለግባቸው የገንዘብ መጠን ገና ያልታወቀና ክስ ያልተመሰረተባቸው በበጀት ዓመቱ (2008) ብዛት 46፣ ከ1992 እስከ 2007 ብዛት 92 በድምሩ 128 የፍትሐ ብሄር ጉዳዮች ለህግ አገልግሎት የተመሩ ቢሆንም ያለምንም እርምጃ የሚገኙ መሆኑ፤
- የዩኒቨርሲቲው የስራ ክፍሎች ስራቸውን ለማከናወንና ተፈላጊውን ውጤት ለማስገኘት ለተሰጣቸው መደበኛ የስልክ መስመሮች ወርሃዊ ተመን ያልወጣላቸው (የአጠቃቀም ቁጥጥር የማይደረግ) መሆኑ፤
- 4 ተሽከርካሪዎች የሠሌዳ ቁጥር የሌላቸው መሆኑ፤የተቋሙ ተሽከርካሪዎች የተሟላ የህይወት ታሪክ ማህደር የሌላቸው መሆኑ፤
- አሮጌ ተመላሽ የመለዋወጫ ዕቃዎች መረካከቢያ የሌለ መሆኑ፤የመለዋወጫ ዕቃ ግምጃ ቤት ሠራተኛ ከግንቦት 1/2005 ጀምሮ ወደ ሌላ ሥራ ሲመደቡ በእጃቸው ያለው ንብረት እስካሁን ርክክብ ያልተፈፀመ መሆኑ፤

- የምግብ ዕቃዎች የንብረት ገቢና ወጪ ደረሰኞች (ሞ/19) እና ሞ/22) የመያዝ፣ የማዘጋጀት፣ ስቶር ሳይኖራቸው ንብረቶቹን የመረከብና በሞዴል 22 ለምግብ ዕቃ የክምችት ግምጃ ቤት ሠራተኛ የማስተላለፍ ሥራ በአንድ ሠራተኛ የሚከናወን መሆኑ፤
- በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የምግብ ጥሬ ዕቃዎች ቆጠራ እየተደረገ ከወጪ ቀሪ ትክክለኝነት እንዲረጋገጥ ያልተደረገ መሆኑ፤
- የአተር ክክ፣ ድፍንና የተከካ ምስር ከምግብ ክምችት ግምጃ ቤት ለዝግጅት (ለማበጠር ሲተላለፍ) ርክክብ በጽሁፍ ወጪ የሚደረግበት አሠራር ካለመኖሩም በተጨማሪ ከተዘጋጀም (ከተበጠረ) በኋላ ተመልሶ ወደ ክምችት ግምጃ ቤት ሠራተኛዋ ሲተላለፍ እየተመዘነ ርክክብ ሳይፈጸም በቀጥታ ለአገልግሎት (ለወጥ ቤት) እየተጠየቀ ወጪ የሚደረግ መሆኑ፤
- 5 ትልልቅ ዳቦ መጋገሪያ ማሽኖች አገልግሎት መስጠት የሚችሉ መሆን አለመሆናቸው በትክክል የማይታወቅ በተለያዩ ክፍሎች የሚገኙ መሆኑ፤
- የበሰሉም ሆነ ያልበሰሉ የምግብ ዕቃዎች ርክክብ ወቅት የተማሪዎች ተወካይ የሚገኙ ለመሆኑ ማረጋገጫ ያልቀረበ መሆኑ፤
- በግዢና በዕርዳታ የሚመጡ መድሃኒቶችና የህክምና ዕቃዎች በማዕከላዊ ግምጃ ቤት ከሙያው ጋር አግባብ በሌላቸው ሠራተኛ የንብረት ገቢና ወጪ (ሞ/19 እና ሞ/22) የሚዘጋጅላቸው መሆኑ፤
- ለመድሃኒቶችና ሌሎች አላቂ የህክምና ዕቃዎች በግምጃ ቤቱ ባለሙያ ከሚጠበቅ ቢን ካርድ በስተቀር የገቢና ወጪ መከታተያ የሌለ መሆኑ፤
- በዋናው ግቢ የመድሃኒት ማደያ (Dispencery room) የተረከቡትና ያደሉትን የሚያመለክት ምዝገባ ካለመኖሩም በተጨማሪ የሥራ ክፍሉ 4ቱም ባለሙያዎች (ድረጊስት) በፈረቃ ሲቀያየሩ የመድሃኒት መጥፋት ወይም መጉደል ቢከሰት በጋራ (በተናጠል) ሊጠየቁበት የሚያስችል አሠራር የሌለ ከመሆኑም በላይ ባለሙያዎቹ በተለያየ ምክንያት ሲለቁ ከወጪ ቀሪ የማይረጋገጥ መሆኑ፤
- የዩኒቨርስቲው የዋናው የመድሃኒት ግምጃ ቤት ሠራተኛ (ባለሙያ) ከታህሳስ 1/2008 ጀምሮ ለውጥ ሲደረግ በወቅቱ በግምጃ ቤት የነበረውን ርክክብ የተፈጸመ ቢሆንም አስረካቢዋ ያስረከቡት ከወጪ ቀሪ ማስረከብ በሚገባቸው ልክ ለማስረከባቸው ትክክለኛነቱ ያልተረጋገጠ ከመሆኑም በተጨማሪ የቴክኖሎጂ ካምፓስ ድረጊስቶች (ባለሙያዎች) በተለያየ ምክንያት ሲቀያየሩ ርክክብ የማይፈጸም መሆኑ፤ (ለምሳሌ፡- አሁን ወደ ዋናው መድሃኒት ስቶር የተዛወሩና ተረካቢዋ (ድረጊስት ዝናሽ በቀለ ሳያስረክቡ የለቀቁ መሆኑ)፤

- የተቋሙ ሠራተኞችና ቤተሰቦቻቸው በተማሪዎች ክሊኒክ የዱቤ አገልግሎት እንዲያገኙ የተወሰነበት የጽሁፍ ማስረጃ ካለመቅረቡም በተጨማሪ የተለያየ የሥራ ክፍል ሠራተኞች የህክምና አገልግሎት ያገኙበት ብር 4,801.00 ያልተሰበሰበ መሆኑ፤
- የቴክኖሎጂና የቨተርነሪ ካምፓሶች የተማሪዎች ክሊኒክ ከዋናው ካምፓስ መድሃኒት ስቶር ድረጊስቶቹ (ባለሙያዎቹ) ጠይቀው ሲወስዱ አስቀድሞ ከወሰዱት መድኃኒት የቀረ መኖር አለመኖሩን ወይም ሙሉ በሙሉ በሥራ ላይ መዋሉ ሣይረጋገጥ እየተፈቀደ የሚሰጥ መሆኑ፤
- በቴክኖሎጂና ቨተርነሪ ካምፓሶች ድራጊስት ባለመኖሩ ባለሙያዎቹ የሚያስፈልጋቸው መድሃኒት ከዋናው መድሃኒት ግምጃ ቤት እየጠየቁ በመውሰድ መድሃኒቱን የመያዝ፤ ህክምናውን የማከናወን፤ መድህኒት የማዘዝና የማደሉ ሥራዎች በባለሙያዎቹ የሚከናወን መሆኑ፤
- መድሃኒቶች በአንድ ወጥ የሚጠበቁበት በቂ ስቶርና መደርደሪያ (ሼልፍ) ባለመኖሩ ለመድሃኒት መጠበቂያነት ባልተሰሩ በተለያዩ ቦታዎች ለብልሽት በሚዳርግ መልኩ በወለል ላይ ተደራርበው የተቀመጡ ከመሆኑም በተጨማሪ በንግድ ማዕከል የሚገኘው የመድሃኒት ስቶር በሮቹ (ግሪል ያልተደረጉ) መስታወት በመሆናቸው ለንብረት መጠበቂያነት ሊውል የማይችል መሆኑ፤
- በግዢና በዕርዳታ የሚመጡ መድሃኒቶችና የህክምና ዕቃዎች በማዕከላዊ ግምጃ ቤት ከሙያው ጋር አግባብ በሌላቸው ሠራተኛ የንብረት ገቢና ወጪ (ሞ/19 እና ሞ/22) የሚዘጋጅላቸው መሆኑ፤
- ከቀድሞ የመጽሃፍት ግምጃ ቤት ሠራተኛ ርክክብ የተፈፀመ ቢሆንም ማስረከብ በሚገባቸው ልክ ለማስረከባቸው ትክክለኛነቱ ያልተረጋገጠ ከመሆኑም በተጨማሪ መጽሃፍት የሚፈለግባቸው መምህራን የትውስት ካርድ (ሰነድ) በኃላፊነት የተረከባቸው ሳይኖር በመጽሃፍት ግምጃ ቤት የተቀመጡ መሆኑ፤
- በኮሌጁ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ መጽሃፍቱ የሚገኙበት ሁኔታ ለማረጋገጥ ቆጠራ ያልተደረገ መሆኑ፤(በመጽሃፍት ግምጃ ቤት፤ በሰርኩሌሽንና በስታክ የሚገኙ)፤ ዋና ግቢ
- በተለያዩ የሥራ ክፍሎች ለቢሮዎች፤ ለተማሪዎች ዶርምና ለመማሪያ ክፍሎች፤ ለመምህራን መኖሪያና ለእንግዳ ማረፊያ ቤቶች፤ ለምግብ ቤቶች፤ ለላይብራሪ አገልግሎት መስጫ ወጪ ለተደረጉ ቋሚ ንብረቶች የተሟላ መለያ ቁጥር ያልተሰጠ መሆኑ፤

- በ2005 በአቅራቢዎች ለናሙና የቀረቡ ብዛታቸው በትክክል ያልታወቀ ባለመደገፊያ ወንበሮች፣ በመመሪያው መሰረት ከ6 ወራት በላይ ያስቆጠሩ ቢሆንም ወደ ተቋሙ ገቢ ያልተደረጉ መሆኑ፣
- የተለያዩ አሮጌ የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች በአንድ ትልቅ ግምጃ ቤት ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፣
- ለአላቂ ዕቃ ገቢና ወጪ መከታተያ ስቶክ ካርድ ቢኖርም ምዝገባው ከወጪ ቀሪ መነሻ ያላደረገ ከመሆኑም በተጨማሪ የአንዱ በጀት ዓመት ከሌላው በጀት ዓመት በአግባቡ ተለይቶ የማይመዘገብ መሆኑ፣
- በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የገቢና የወጪ መከታተያ ስቶክ ካርዶች በቆጠራ ኮሚቴም ሆነ በውስጥ ኦዲት የማይዘጉ መሆኑ፣
- የመለዋወጫ ዕቃ ገቢና ወጪ መከታተያ ስቶክ ካርድ ቢኖርም ምዝገባው ከወጪ ቀሪ መነሻ ያላደረገ ከመሆኑም በተጨማሪ የተሟላ ምዝገባ የሌለ መሆኑ፣
- ከተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ መ/ቤቶችና ድርጅቶች በዕርዳታ የተገኙ መድኃኒቶችና ህክምና የህክምና መገልገያዎች ዋጋቸው ሣይታወቅ ገቢ የሚደረጉ መሆኑ፣
- ድራጊስት በፈረቃ ሲቀያየሩ በተናጠል ወይም በጋራ ሊጠየቁበት የሚያስችል አሠራር የሌለ መሆኑ፣

8.4.2 <u>ስጋት</u> ፣

በኦዲት ሪፖርቱ በተሰጡ የማሻሻያ ሃሳቦች መሠረት የእርምት እርምጃ አለመወሰዱ ለመንግሥት ሀብት ብክነት መንገድ የሚከፍት ከመሆኑም በተጨማሪ ተጠያቂነትንም ሊያስከትል ይችላል፡፡

8.4.3 **<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>** ፣

የዩኒቨርሲቲው የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እንዲቀረፉና ግልፅነትና ተጠያቂነት እንዲሰፍን የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር በኦዲት በሚሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሠረት የእርምት እርምጃ በመውሰድ የበኩሉን አስተዋፅኦ መወጣት እንደሚገባው በድጋሚ እናሳስባለን፡፡

8.4.4 **<u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>**

ስራ አመራሩ ምላሽ አልሰጠም፡፡

በመጨረሻም በኦዲቱ ወቅት ለተደረገልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፣

አባሪ 1 ከተገኘው ጥቅም ላይ ያልተቀነሰ ቅደመ-ታክስ

ተ.ቁ	ስም	በውሉ መሰረት የተከፈለ	30% የቅድሚያ ክፍያ ግብር መቀነስ	በልዩነት መከፈል የነበረበት	ለአገባብ ተከፈለ የቀን ውሎ አበል
1	ፐ/ር ፍቃዱ በየነ	2,800.00	840.00	1,960.00	1,498.00
2	ዶ/ር ዜላለም ተስፋዬ	2,800.00	840.00	1,960.00	1,926.00
3	ዶ/ር ዘላለም ይልማ	2,800.00	840.00	1,960.00	1,498.00
4	ዶ/ር ተስፋዬ አለሙ	2,000.00	600.00	1,400.00	1,926.00
5	ዶ/ር አይናለም ሀይሌ	2,000.00	600.00	1,400.00	1,498.00
6	ዶ/ር ስንታዩ ይርጋ	2,000.00	600.00	1,400.00	1,926.00
7	ዶ/ር ደቀባ እሸቴ	2,000.00	600.00	1,400.00	1,712.00
8	ዶ/ር አዱኛ ቶለራ	2,800.00	840.00	1,960.00	1,926.00
9	ዶ/ር ፍሬው ካሳ	2,000.00	600.00	1,400.00	1,712.00
10	ፐ/ር ተገኔ ነገሴ	3,000.00	900.00	2,100.00	1,926.00
11	ዶ/ር ጌታቸው አንሙት	2,800.00	840.00	1,960.00	1,498.00
12	ዶ/ር ጌትነት አሰፋ	2,000.00	600.00	1,400.00	1,498.00
13	ዶ/ር ለማ ፊጣ	2,000.00	600.00	1,400.00	1,926.00
14	ፐ/ር አጀቡ ኑርፈታ	2,800.00	840.00	1,960.00	1,926.00
15	ዶ/ር አዛኝ ተገኝ	2,000.00	600.00	1,400.00	1,498.00
16	ዶ/ር ኪዳኔ ገ/መስቀል	2,000.00	600.00	1,400.00	1,498.00
17	ዶ/ር ለገሰ ዱዲ	3,600.00	1,080.00	2,520.00	1,498.00
18	ዶ/ር ግርማ ተስፋሁን	3,600.00	1,080.00	2,520.00	1,498.00
19	ዶ/ር አደም በቀለ	3,000.00	900.00	2,100.00	1,926.00
20	ዶ/ር ስሜነህ ባዜ	3,000.00	900.00	2,100.00	1,926.00
21	ዶ/ር ዮሰፍ መርጋ	3,000.00	900.00	2,100.00	1,926.00
22	ዶ/ር ደረጀ በሪሁን	3,000.00	900.00	2,100.00	1,926.00
23	ዶ/ር እንድርያስ ጌታ	3,000.00	900.00	2,100.00	1,926.00
24	ዶ/ር አበባው ሽመልስ	4,000.00	1,200.00	2,800.00	1,284.00
25	ዶ/ር የአለምዘውደ ሞላ	3,000.00	900.00	2,100.00	1,498.00
26	ዶ/ር ስሳይ ደበበ	3,000.00	900.00	2,100.00	1,926.00
27	ዶ/ር ኑጉሴ ስሜ	3,000.00	900.00	2,100.00	1,498.00
28	ዶ/ር ሀ/ማርያም ተወልደ	3,000.00	900.00	2,100.00	1,498.00
29	ዶ/ር ጌታው ታደሰ	3,000.00	900.00	2,100.00	1,498.00
30	ዶ/ር ታዬ ተሰማ	2,800.00	840.00	1,960.00	1,498.00
31	ዶ/ር ኪዳኔ ተስፋዬ	2,800.00	840.00	1,960.00	1,498.00
32	ዶ/ርታስፋዬ ሽብሩ	2,800.00	840.00	1,960.00	1,498.00
33	ፐ/ር ፍቅሬ ለሜሳ	3,600.00	1,080.00	2,520.00	1,926.00

34	ዶ/ር ደረጀ አሰፋ	4,600.00	1,380.00	3,220.00	1,926.00
35	ዶ/ር አምሳሉ አያና	1,800.00	540.00	1,260.00	1,498.00
36	ዶ/ር ፍርዱ አዘረፈኝ	2,000.00	600.00	1,400.00	1,926.00
37	ዶ/ር ክበበው አሰፋ	3,000.00	900.00	2,100.00	1,712.00
38	ዶ/ር ብርሃኑ አሰማሉ	3,000.00	900.00	2,100.00	1,926.00
39	ዶ/ር ደቻሳ ሂርጳ	4,000.00	1,200.00	2,800.00	1,926.00
40	ዶ/ር ኤልያስ ሁርጌ	4,000.00	1,200.00	2,800.00	1,926.00
41	ዶ/ር አል መሀመድ	3,000.00	900.00	2,100.00	1,926.00
42	ዶ/ር ግርማ ሀ/ሚካኤል	2,000.00	600.00	1,400.00	1,926.00
43	ዶ/ር አበቡሽ ተስፋዬ	2,000.00	600.00	1,400.00	1,926.00
44	ዶ/ር ብርሃኑ ላቀው	2,000.00	600.00	1,400.00	1,712.00
45	ዶ/ር ተደሴ ደሳለኝ	2,000.00	600.00	1,400.00	1,498.00
46	ዶ/ር ለገሰ ወልዴ	2,000.00	600.00	1,400.00	1,498.00
47	ዶ/ር ነጋሽ ገለታ	2,000.00	600.00	1,400.00	1,926.00
48	ዶ/ር ነጋሽ ሀይሉ	2,000.00	600.00	1,400.00	1,712.00
49	ዶ/ር ጌታቸው አያና	2,000.00	600.00	1,400.00	1,926.00
50	ዶ/ር በቀለ ካሳ	2,000.00	600.00	1,400.00	1,712.00
51	ዶ/ር የኔነው ገ/ስላሴ	2,800.00	840.00	1,960.00	1,926.00
52	ዶ/ር ገብሬ ሀድጉ	2,000.00	600.00	1,400.00	1,926.00
53	ዶ/ር አክሊሉ መካሻ	2,000.00	600.00	1,400.00	1,926.00
54	ዶ/ር አባይነህ ደራሮ	2,000.00	600.00	1,400.00	1,498.00
55	ዶ/ር ሙክታር መሀመድ	2,000.00	600.00	1,400.00	1,284.00
56	ዶ/ር ተስፋዬ በቀለ	2,000.00	600.00	1,400.00	1,498.00
57	ዶ/ር ታምራት በቀለ	2,000.00	600.00	1,400.00	1,498.00
58	ዶ/ር ፋንታው አበጋዝ	2,000.00	600.00	1,400.00	1,498.00
59	ዶ/ር ዳንኤል ተሰማ	3,000.00	900.00	2,100.00	1,498.00
60	ዶ/ር ዘመን አያሌው	3,000.00	900.00	2,100.00	1,926.00
61	ዶ/ር ደሳለኝ ሞላ	3,000.00	900.00	2,100.00	1,926.00
62	ዶ/ር ጌታሁን ፋንታ	3,000.00	900.00	2,100.00	1,498.00
63	ዶ/ር ዘርሁን በርሄ	3,000.00	900.00	2,100.00	1,498.00
64	ዶ/ር አየለ ተሰማ	3,000.00	900.00	2,100.00	1,926.00
65	ዶ/ር መሃዲ እጌ	4,000.00	1,200.00	2,800.00	1,284.00
66	ዶ/ር ቱሉ ደገፉ	3,000.00	900.00	2,100.00	1,498.00
67	ዶ/ር መስፍን ታደሰ	3,000.00	900.00	2,100.00	1,498.00
68	ዶ/ር ሙሉጌታ ክብረት	3,000.00	900.00	2,100.00	1,926.00
69	ዶ/ር ፋሪሲ ሀይሉ	2,000.00	600.00	1,400.00	1,926.00
70	ዶ/ር ሙሉጌታ ከበደ	3,000.00	900.00	2,100.00	1,498.00

71	ዶ/ር ክፍሌ ዳኜ	3,000.00	900.00	2,100.00	1,498.00
72	ዶ/ር ድርባ ሙሉጌታ	3,000.00	900.00	2,100.00	1,498.00
73	ዶ/ር ሀባቴ ተክሌ	4,000.00	1,200.00	2,800.00	1,498.00
74	ዶ/ር አሀመድ ሀሴን	3,000.00	900.00	2,100.00	1,498.00
75	ዶ/ር ዳንኤል ብስራት	3,000.00	900.00	2,100.00	1,498.00
76	ዶ/ር ናሰ ገበየው	3,000.00	900.00	2,100.00	1,498.00
77	ዶ/ር ሲሳይ ታደሰ	3,000.00	900.00	2,100.00	1,926.00
78	ዶ/ር ሙሉጌታ ወ/ሚካኤል	3,000.00	900.00	2,100.00	1,284.00
79	ዶ/ር ሀጎስ ወ/ጊዮርግስ	3,000.00	900.00	2,100.00	1,926.00
80	ዶ/ር ካሳሁን ቱሬ	3,000.00	900.00	2,100.00	1,498.00
81	ዶ/ር ግርማ ጎሮ	2,000.00	600.00	1,400.00	1,284.00
82	ዶ/ር ሙሉጌታ በቀለ	2,000.00	600.00	1,400.00	1,498.00
83	ዶ/ር በዛብህ ወልዴ	4,000.00	1,200.00	2,800.00	1,498.00
84	ዶ/ር አለማየሁ በላይ	4,000.00	1,200.00	2,800.00	1,926.00
85	ዶ/ር አመንስሳ ከበደ	4,000.00	1,200.00	2,800.00	1,498.00
86	ዶ/ር ተስፋይ አሰግዶም	4,000.00	1,200.00	2,800.00	1,498.00
87	ዶ/ር ስሳይ መንግስቱ	4,000.00	1,200.00	2,800.00	1,926.00
88	ዶ/ር ሚልዮን መንገሻ	2,000.00	600.00	1,400.00	1,498.00
89	ፕ/ር ያል ኢዶሳ	1,800.00	540.00	1,260.00	3,210.00
90	ዶ/ር ጥላሁን ሆርዶፋ	2,000.00	600.00	1,400.00	1,926.00
91	ዶ/ር ሚካኤል መንክር	4,000.00	1,200.00	2,800.00	1,498.00
92	ዶ/ር መኮንን አያና	2,000.00	600.00	1,400.00	1,498.00
93	ዶ/ር አበበ ሀይሌ	3,000.00	900.00	2,100.00	1,498.00
94	ዶ/ር ተፋ ቱሉ	2,800.00	840.00	1,960.00	1,498.00
95	በቀለ መገርሳ	3,000.00	900.00	2,100.00	1,926.00
96	ዶ/ር አራዓያ መንግሥቱ	2,000.00	600.00	1,400.00	1,926.00
ጠቅላላ ድምር		**264,800.00**	**79,440.00**	**185,360.00**	**162,426.00**

አባሪ 2 <u>የሆኖራሪየም ክፍያ</u>

ተ.ቁ	ቀን	ቫውቸር ቁጥር	የተከፈለ ብር
1	6/4/2009	907	437,069.48
2	22/7/2009	7948	466,395.99
3	6/4/2009	910	126,760
4	19/8/2009	2299	175,219
5	3/4/2009	898	277,536.19
6	13/4/09	1314/09	512,923.06
ድምር			1,995,903.72

አባሪ 2.1 ለማስተርነት ወይም ለዶክተርነት ዲግሪ በሚዘጋጅ የጥናት ምርምር ጹሑፍ ለማመከር የተከፈለ ክፍያ፣

ተ.ቁ	ቀን	የወጪ ማስመስከርያ ቁጥር	የወጪው ምክንያት	የተከፈለው	የገንዘቡ መጠን	ምርመራ
1	08/06/17	2204/09	መምህራን የሁለተኛ ዲግሪ ተማሪዎችን ሪሰርች ወረቀት ያማከሩበት ክፍያ	ለ36 መምህራን	320,898.14	ዋና ግቢ
2	28/10/09	1805/09	‹‹ ››	ለ156 መምህራን	1,059,564.64	ዋና ግቢ ውስጥ ገቢ
3	13/11/16	571/09	‹‹ ››	ለ133 መምህራን	864,800.00	ዋና ግቢ ውስጥ ገቢ
4	29/7/09	1104/09	‹‹ ››	ለ102 መምህራን	530,068.15	ዋና ግቢ ውስጥ ገቢ
5	04/3/09	569/09	‹‹ ››	ለ62 መምህራን	320,129.95	ዋና ግቢ ውስጥ ገቢ
6	29/09/09	4198/09	‹‹ ››	ለ68 መምህራን	346,664.59	ዋና ግቢ መደበኛ
7	22/10/09	1011/09	‹‹ ››	ለ42 መምህራን	51,786.56	አካዳሚክ ምርምር ክላስተር
				ድምር	3,493,912.03	

አበሪ 2.2

ተ.ቁ	ቀን	ቫውቸር ቁጥር	የወጪው ምክንያት	የገንዘብ መጠን	ምርመራ
1	30/10/09	3354	የተግባር ፈተና ለፈተኑት እና ላስተበበሩት	118,738.00	ዋና ግቢ
2	29/10/09	3301	‹‹ ››	234,978.00	ዋና ግቢ
3	10/9/09	2578	ጥናታዊ ፅሁፍ ግምገማ ላይ ለተሳተፉት እና ላስተባበሩት	302,401.00	ዋና ግቢ
4	08/03/09	238/09	ከፈተና ጋር በተያያዘ ስራዎችን ላከወኑ	25,900.00	ህክምና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ
5	07/06/09	555/09	በኮሌጁ ውስጥ በተዘጋጀው የህክምና ተማሪዎች ምረቃ በአል ላይ የተሳተፉ የኮሌጁ ሰራተኞች	29,265.40	ህክምና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ
6	13/05/09	503/09	ብሔር ብሔረሰቦች በአል ላይ ለተሳተፉ የኮሚቴ አባላት ክፍያ	53,919.28	ህክምና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ
7	08/03/09	227/09	የዩኒቨርሲቲው መምህራንና ሰራተኞች ስልጠና ላይ ለተሳተፉ አሰልጣኞች እና የኮሚቴ አባላት	96,280.00	ህክምና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ
8	08/03/09	238/09	ለማስተርስ መርሀ ግብር አማካሪዎች ክፍያ ፣ የማስተርስና መደበኛና የክረምት ፕሮግራም ድርሳን ፈታኞች ክፍያ እና ከፈተና ጋር በተያያዘ የአስተዳደር ስራን በማስተባበር ለሰሩበት	310,065.39	ህክምና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ
9	07/06/09	577/09	ለማስተርስ መርሀ ግብር አማካሪዎችና የፒ.ች.ዲ ፈታኞች ክፍያ	89,553.34	ህክምና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ
	ድምር			1,261,100.41	

አባሪ 3 ዘላቂነት ባለው የስራ ዘርፈ ላይ በቀን ሰራተኝነት የተቀጠሩ ሰራተኞችን በተመለከተ

ተ.ቁ	ቀን	የወጪ ማ ቁጥር	የወጪው ምክንያት	የተከፈለው	የገንዘብ መጠን
1	23/10/09	1785/09	የተለያዩ የእርባታ ክፍሎችን ደህንነት በማታው ከፍል ጊዜ መጠበቅ	ለ227 ሰራተኞች	164,500.00
2	7/10/09	1630/09	<< >>	ለ219 ሰራተኞች	107,485.00
3	25/5/2017	1454/09	የጀበና ቡና ማፊያ ቦታ ማዘጋጀት የውበት ስራ ዎች	ለ38 ሰራተኞች	29,920.00
4	8/10/09	2162/09	<< >>	ለ39 ሰራተኞች	30,240.00
5	30/10/09	275/09	አስተናጋጅ፣ጽዳት፣የጀበናና ቡና አፊ ፣ስጋ ቤት አራጅ፣ ጉልበት ሰራተኛ ፣ምግብ አብሳይ፣ እንጀራ ጋጋሪ፣ ስጋ አታፊ ፣ቦንቦሊኖ ስራተኛ ፣አስተናጋጅ	ለ75 ሰራተኞች	42,602.00
6	23/07/09	991/0	አስተናጋጅ፣ጽዳት፣የጀበናና ቡና አፊ ፣ስጋ ቤት አራጅ፣ ጉልበት ሰራተኛ ፣ምግብ አብሳይ፣ እንጀራ ጋጋሪ፣ ጉልበት ሰራተኛ፣አስተናጋጅ	ለ77 ሰራተኞች	77,052.60
7	16/8/09	1195/09	<< >>	ለ53 ሰራተኞች	40,830.10
8	19/06/17	1678/09	<< >>	ለ58 ሰራተኖች	78,576.80
9	20/06/09	865/09	<< >>	ለ51 ሰራተኞች	49,368.70
10	8/09/09	1343/09	በግብርና ልማት ማስተባበሪያ ስር ያሉ የተለያዩ ምርጥ ዘሮችን መሰብሰብ	ለ239 ሰራተኞች	150,780.00
11	19/08/09	1305/09	በእንስሳት ፓርክ እንስሳቶችን መንከባከብ እና መጠበቅ	ለ147 ስራተኞች	90,050.00
12	30/10/09	1891/09	በግብርና ልማት ማስተባበሪያ የስጋ ከብት መኖ መሰብሰብና ማንከባከብ	ለ257 ስራተኖች	220,785.00
				ድምር	1,082,190.20

አባሪ 4 **አቅራቢዎች ሳይወዳደሩ በቀጥታ የተፈጸመ ግዥ**

ተራ.ቁ	ቀን	የወጪው ምክንያት	የተከፈለው	የወጪ ማስመሰከሪያ ደረሰኝ ቁጥር	የገንዘብ መጠን	ምርመራ
1	13/10/2009	የተሽከርካር ጥገና	ኢ.ት.የሞተርና መሐንድስነት ኢ.ማ.	3095	289,269.54	ዋናው ግቢ
2	28/10/09	የተሽከርካር ጥገና	ኤ.ጂ.ቲኤ.የግል.	3373	214,382.55	ዋናው ግቢ
3	30/10/2009	ሞተር ሳይክል	ማንአለብሽ በቀለ አስመጪ	3927	455,000.00	ዋናው ግቢ
4	30/10/2009	ሞተር ሳይክል	ማንአለብሽ በቀለ አስመጪ	3928	455,000.00	ዋናው ግቢ
5	22/09/09	<< >>	መ.ሲ.ኢ. ኢ.ማህበር	2794	250,192.08	ዋናው ግቢ
					1,663,844.17	

አባሪ 5 አለአግባብ የተከፈለ ውሎ አበል

ተ.	ቀን	ቫውቸር	የተከፈለበት ምክንያት	የገንዘብ	ምርመራ
1	30/12/08	191	ለጥበቃ ሰራተኞች	127,200.00	ዋና ግቢ
2	2810/09	3262	ለማስተርስ ድርሳን አስፈፃሚዎች	143,904.00	ዋና ግቢ
3	28/10/09	3263	‹‹ ››	137,614.00	ዋና ግቢ
4	04/01/17	429	በተለያ የስብሰባ ጊዜያቶች ሲያስተባብሩ ለቆዩ የተከፈለ አበል	24,150.00	አካዳሚክና ምርምር
5	07/10/16	192	ዕሁድ እና ቅዳሜ ለሰሩ የፋይናስ ክፍል ሰራተኞች የተከፈለ አበል	25,492.00	‹‹ ››
6	30/10/09	895	ለፋይናስ ሰራተኞች የአመት ሪፖርት ለሰሩበት ለ9 ሰራተኛ ለአያንዳዳቸው 20 ቀናቶችና 3 ሰራተኞች እያንዳዳቸው 10 ቀናቶች በቀን ብር ከ124 እስከ 206 የሚደርስ የውሎ አበል ተከፈለ	36,700.00	‹‹ ››
7	30/10/09	897	ለስልጠና ለ3 ሰራተኞች እያንዳዳቸው 12 ቀን፣4 ሰራተኞች እያንዳዳቸው 10 ቀናቶች፣ 12 ሰራተኞች እየንዳዳቸውና አንድ ሰራተኛን ጨምሮ ለእያንዳዳቸው ለ7 ቀናቶች በሚታሰብ የውሎ አበል ተመን 171 የተከፈለ	46,902.52	‹‹ ››
8	07/03/09	179	ዕሁድ እና ቅዳሜ ለሰሩ ሪጅስትራር፣ ፋይናንስ፣ዳይሬክተር ወ.ዘ.ተ…	14,976.00	‹‹ ››
9	22/10/09	867	ስልጠና ላስተባበሩ 90 ሰረተኞች እያንዳዳቸው የ5 ቀን አበል ብር 171 እየተሰላ መከፈሉ	76,950.00	‹‹ ››
10	27/10/09	167	seminar paper evaluator ላስተባበሩበትና rabies vaccination and world veterinary day 2017 celebration ላስተባበሩ	16,580.00	የእንስሳት ህክምና ኮሌጅ
11	27/10/09	165	››	24,270.00	የእንስሳት ህክምና ኮሌጅ
			ድምር	674,738.52	

አባሪ ቁጥር 6 ከክፍያው ላይ ያልተቀነሰ እና ለመንግስት ገቢ ያልሆነ ተጨማሪ እሴት ታክስ

ተ.ቁ	ቀን	የወጪ ማስ. ቁጥር	የወጪው ምክንያት	የተከፈለው	የተከፈለው የገንዘብ መጠን	ተቀናሽ ያልተደረገ የተ. እ .ታክስ
1	16/02/09	1567	የስጋ ከብቶች ግዥ	ሀረማያ አካ/ገ/ሀ/ስ/ ዩ ኒን	445,263.00	66,789.45
2	30/01/09	693	‹‹ ››	‹‹ ››	3,140,860.00	471,129.00
3	17/06/09	1676	‹‹ ››	‹‹ ››	460,345.20	69,051.78
4	16/06/09	1568	‹‹ ››	‹‹ ››	394,636.20	59,195.43
5	14/07/09	1751	‹‹ ››	‹‹ ››	390,726.00	58,608.90
6	29/09/09	2177	‹‹ ››	‹‹ ››	370,144.00	55,521.60
7	9/3/2009	933	‹‹ ››	‹‹ ››	361,237.80	54,185.67
8	18/02/09	795	‹‹ ››	‹‹ ››	1,037,290.80	155,593.62
9	3/6/2009	1505	‹‹ ››	‹‹ ››	775,689.60	116,353.44
					ጠቅላለ ድምር	1,106,428.89

አባሪ 7 **በጀት ንጽጽር**

ሂሳብ መደብ	ስራ ላይ የዋለ	የተፈቀደ በጀት/የተስተካከለ/	ከበጀት በላይ ስራ ላይ የዋለ	%
	ከበጀት በላይ የወጣ /ካፒታል/			
6323	417,514,751.10	309,456,500.00	108,058,251.10	35%
ድምር	417,514,751.10	309,456,500.00	108,058,251.10	